
ስብሃት ገብረእግዚአብሄር

# በርጬቅ!



@amharicbooks24 click here

@amharicbooks24 ይሄን ይጫኑ

መጽሐፍት

የተመረጡ አማርኛ ና እንግሊዝኛ
መጽሐፍትን ,ትረካዎችን,ወጎች ያገኛሉ

...

# ቦርጪቅ!

# የደራሲው ቀደምት ስራዎች

- አምስት ስድስት ሰባት
- ሴቱም አይነጋልኝ
- ትኩሳት
- ሰባተኛው መልአክ
- እነሆ ጀግና
- እግረ መንገድ ፩
- እግረ መንገድ ፪
- የፍቅር ሻማዎች
- ባዚ

ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር

# ቦርጨቅ!

መጋቢት - 2004
አዲሳባ

© ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር - 2003

የመጀመሪያ እትም 2004 ዓ.ም.

© መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
All Right Reserved

አሳታሚ - ሄለን (ኩኩሻ) ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር

# ማውጫ


አቤልን ፍለጋ ........ 11

አውራ ዶሮው ........ 19

ጥቁር ምላስ ........ 27

[illegible] ........ 31

በሰባራ ሸጉጥ ........ 41

ዘርና አጋፋሪ እንደሻው ........ 47

ኩሊ! ኩሊ! ........ 57

ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ ........ 59

ቦርጩቅ! ........ 67

ወደ ጠጅ ቤት ........ 73

ቢራ-ቢሮ ........ 95

እያ ድቡልቡሌና አጋፋሪ እንደሻው ........ 103

# መግቢያ

## ሰ[illegible]ጣት ደራሲያን

ማንኛውም ገፀባህሪ (ስትፅፋትም ይሁን ስታነቡት) በደምሳሳው (statistically) ሲፈጠር ምን አይነት እንደሚሆን እነሆ anthropology ከሚባለው ማህበራዊ ሳይንስ፡-

የትም ይሁን መቸም ይሁን፣ ሰዎች ስንወለድ ሶስት አይነት ነን፡፡ ለማስብ እንዲቀል ያህል፣ በሺዎች በሚሊዮናት' ግለሰብ የሚከሰተውን እውነታ ወደ አስር እንጭመቀው እናጭቀውና፣ አስር ሰው ሲወለድ፡-

ሀ. ካስሩ አንደኛው አዛዥ ነው፡፡ መሪ፣ ጄኔራል፣ ንጉስ፣ ኢጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ፣ ጋንግስተር፣ general manager፣ የገዳም አበምኔት፣ ከለማኞች ግብር የሚሰበስብ ለማኝ ይሆናል፣ ወይ መሆን ይመኛል ያልማል ያወራል – ጥቂቱ እድል ቀንቶት የተመኘውን ይሆናል

ለ. ካስሩ ሁለተኛው ለማንም መታዘዝ አይሆንለትም፣ ማዘዝም አይወድም፡፡ ሳይንቲስት፣ አርቲስት (ሰአሊ፣ ቀራፂ፣ ቀጥቃጭ፣ ሸማኔ፣ ባለቅኔ፣ ባህታዊ፣ ፈላስፋ፣ እብድ፣ እና ያ የተለመደው ወዘተ ሊሆን ይችላል)

ሐ. ካስሩ የተቀረው ስምንት "መንጋ" የሚባለው ሲሆን፣ ብዙ ነው፣ ሺዎች ነው፣ ሰፊው ህዝብ ነው። በለስ ሲቀናው መሪ ያገኛል፣ እንደ ጃንሆይ ሀይለ ስላሴ (ከመሪነትም ልቀው አምላክ የሚሆኑ - "ጃ! ራስ ታፋራይ! ሀይለ ስላሲ አይ! Never say die!")

መንጋው በግራ ጐኑ ተነስቶ በለስ ሲደርቅበት ደሞ፣ መሪ ያልሆነ ነጂ ይልከበታል እዝጌርየው - ያን ጊዜ ጓድ ሊቀመንበርና አብዮታውያን ጓዶች "ቀይ ሽብር ይፋፋም!" የሚል መፈክር አንግበው በየማለዳው በየመንገዱ ዳር በጥይት ይረፈርፉታል፣ አብዮታዊት ኢትዮጵያን በአድሀሪያን መቃብር ላይ እየገነቡ "ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር እናደርጋለን" እያሉ ያስፈራሩታል! "እንግዲህ ቀበሌ ሉቅ ተሰልፈን ተፈጥሮን በራሽን ልንቀበል ነው" እያለ እስኪቃዥ ድረስ... የስታሊን በትር ቀጠቀጠው።

እንድያም ሆኖ ግን ሰፊው ህዝብ ባህር ነው። ከምስጢራዊ ጥልቀቱ አሪፍ ተወዳጅ መሪ ያወጣል እስከሚቀጥለው የዘመናት ዙር ድረስ...

**ምርቃት ከዉሴቱ**

Murphy's Law ይባላል

Murphy's Law Number One:

"You do bot understand the situation."

**ሁኔታው የገባህ ይመስልሃል እንጂ - በጭራሽ አልገባህም**

ለምሳሌ አምስት ስድስት ሰባት ሰዎች ወደሚገኙበት ስትመጣ (ለቅሶ ላይ ወይም በርጫ ላይ ፈርሸው ነው እንበል፣ ወይም አገሪቱ ስለምትገኝበት ሁኔታ እየተወያዩ ወይም እየደለቁ

ሊሆን ይችላል።) የሆነውም ቢሆን አንተ ጭብጡን አልጨበጥከውም

Murphy's Law Number Two:

"If anything can get worse, it will"

*ሁኔታው ሊበላሹ የሚችሉ ከሆነ፣ መበላሸታቸው አይቀርም*

Murphy's Law Number Three:

"There is no such thing as Murphy's Law"

የመርፊ ህግ የሚባል ነገር የለም!

# አቤልን ፍለጋ

አዳምና ሄዋን በአንድ መቶ ሰላሳ አመታቸው ጉረምሳና ኰረዳ ይመስሉ ነበር - ይላል መፅሀፈ ፀጋም በ8ኛው ምእራፉ።

፩

ሆነም፣ ሊመሽ ፀሀይ እንዳቆለቆለች፣ ደመናዎቹም በስነ ስርአት ተሰብስበው ቀይ ለብሰው እንድትተኛ እሹሩሩ ሲሉዋት፣ አዳምም እንደ ልማዱ በዋርካ ስር ቁጭ ብሎ በሀሳብ እየተንሳፈፈ ፍዝዝ ብሎ የምእራቡን ቅላት ሲመለከት፣ ከግራው በኩል "እንዴት ዋላችሁ" አለው።

አዳም ዞር ሲል አንድ አስደንጋጭ ነገር አየ፤ ከትከሻው የጉበጠ፤ ዱላ የተመረኰዘ፤ ፊቱ የተጨማደደ፤ አይኑ

ያጮለጮለ፣ ራሱ የተመለጠ፣ የተቀረው ጠጉሩና ጢሙ ነጭ የሆነ።

"ማን ነህ አንተ?" አለው አዳም በፍርሃት እየተነሳ፣ ዋርካውን የሙጥኝ እየተደገፈ።

"እርጅና ነኝ፣ የሞት መልእክተኛ" አለው በሚንቀጠቀጥ ድምፁ "ሞት ነገ በዚህ ያልፋል።"

"ሞት? ምን ይመስላል ሞት?"

"ስታየው ታውቀዋለህ። እኔም አብሬው እመጣለሁ። ደህና እደር" ብሎት፣ በዱላውና በእግሮቹ እየተጉተተ ወደ ፀሀይዋ በኩል ሄደ። እየራቀ እያነሰ ሲሄድ ቀኑም እየመሸ ሄደ፣ ጨለመ። አዳም እዚያው ቆሞ ቀረ። አዳም ይህን ለማንም አልነገረም።

## ፬

በነጋታው ቃኤልና አቤል ወደየስራቸው ሲሄዱ አዳም በናፍቆት አይን ተከተላቸው። አቤል ጥቂት ሄድ እንዳለ ተመለሰና፣

"ምንድነው የሆንከው አባባ?" አለው። አዳም መናገር ስለተሳነው እንቅ አርጎ እቅፍ አርጎ ሳመው። አቤል ወደ ቤት ገብቶ እናቱን "አባባ አንድ ነገር ሆኗል፤ እንዳትለይው" አላትና ወደ እረኝነቱ ሄደ።

ሄዋን አዳምን ሲያለቅስ አግኝታው ወደ ቤት አስገባችውና አባበለችው። አቀፈችው፣ ደረትዋን አንተራሰችው።

"በህልሜ አቤልን የሚመስል መልአክ መጥቶ፣ ሲነጋ የሚፀነሰውን ልጅ ሴት ብለሽ ትጠሪዋለሽ አለኝ።"

አዳም ፍርሃቱን አሸነፈ፣ ሄዋንን እቅፍ አደረጋት፣ ውድድ አደረጋት...

# ፫

ሲመሽ የአዳም ፍርሃት ተመለሰ። ቶሎ ወደ ቤት ገባ። ሄዋን ልክ እንደ ወትሮዋ ወጥ ትሰራለች። በዚህ በኩል ደሞ የምጣድ እሳት ይንቦለቦላል። ፍርሃቱ ተቀነሰለት። ወደ ውጭ ወጣ። ወዲህ ወዲያ ተንጐራደደ። እነዚያ ልጆች አይመጡምን? ወጥቶ ፍለጋ እንዳይጀምር ሄዋንን ብቻዋን መተው ፈራ። ተመልሶ ወደ ቤት ገባ። "ምን ነካቸው ይሆን እነዚያ ልጆች?" አላት።

ዘወር ብላ እንኳ ሳታየው "ሳይመሽ ነው'ንዴ የሚመጡት ዛሬስ?" አለችው። ፍርሃቱን እፍረት አባረረው። ተመልሶ ወጣ። ብዙ ከተንጐራደደ በኋላ ፀሀይዋን አያት። መጥለቅዋ ነው። "የሄዋንዬን ጡት መምሰል ጀምራለች" ብሎ ለራሱ አሰበና ሳቅ አለ። ሄዋን ናፈቀችው። ወይ ዛሬ ቀን! ሮጦ ወደ ቤት ገባ።

እንጉቻውን አውጥታ ተልባ ትነሰንስበታለች - ለአቤል ነው። ድንገት ሆዱን ወጋው ፍርሃቱ። ለአቤል ፈራለት። ወጣ። መሮጥ ጀመረ። ትንፋሽ ሲያጥረው ሲጀምር ፍጥነቱን ቀነሰ። መቼ በዚህ በኩል ሆነ የሚመጡት የአቤል በጎች? አይ ሞኙ! ዞሮ ወደ ቤት በኩል ሮጠ። ቤቱን ሊያልፍ ሲል መተንፈስ እንደ ከበደው አየ። እንዲያውስ ሮጦ የት ሊደርስ ኖሯል? መሽቶ ሊጨልም አይደለም? ዋርካው ላይ ወጣና ዙሪያውን ሲመለከት

በጎቹ ሲመጡ አያቸው። ከመቸኰሉ የተነሳ ከዋርካው ሊወድቅ ነበር። ወርዶ ወደ በጎቹ በኩል ሮጠ።

"አቤል! አቤል ዉ!--ዉ!" ብሎ ተጣራ። መልስ የለም። በጐቹ ብቻቸውን ናቸው።

"እረ አቤል ዉ! ዉ!"

መልስ የለም። ሰማይና ምድር በጭለማ ሊጣበቁ ምንም አልቀራቸውም።

ፍርሃቱ ማጣደፉን ተወው። ልቡ ውስጥ ገብቶ ተመቻችቶ ተቀመጠ።

፬

አዳም በጎቹን አበረታቸው አስገብቶ ወደ ቤት ሲገባ ቃኤል የስንዴ ቆሉ ይበላል።

"ወንድምህ የት አለ?" አለው።

"እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝ?" አለው።

፭

አዳም ቁርጡን አወቀ። ዱላውን ይዞ ወጣ። ሌቱን በጨረቃ ሲፈልግ አድሮ፣ ጠዋቱን በፀሀይ ሲፈልግ አረፈደ። ልጁን ሊያገኘው አልቻለም። ወንዙን ሲሻገር ውሃ ጠማ። በረሃ ለበረሃ ይኳትን ጀመር - ልጁን ፍለጋ። ፀሀይ ከላይ አሸዋ ከታች ጠበሱት። ምድር ምጣድ፣ ሰማይ አከንባሎ ጋገሩት። በውሃ ጥም ጉሮሮው ነቃ፣ ነፍስም ከዳው፣ በቁመናው ፈጣሪ እየቀጣው መሆኑ ታወቀው። እያለቀሰ ልጁን ፍለጋ ቀጠለ። ሲፈልግ ውሎ

መሸ። በጨረቃ በምድረ በዳ ፍለጋውን ቀጠለ። ብርድ ገረፈው ሰውነቱን፣ አሸዋው በረዶ ይመስል ቆረጠው እግሩን።። ቂመኛው ፈጣሪ ቀጥቶ የማይጠግብ መሆኑን አወቀ። በጨረቃ ሲፈልግ አድሮ፣ በፀሀይ ሲፈልግ አረፈደ። እኩለ ቀን ሲሆን ደክሞት ወደቀ። ተደፍቶ ባሸዋ ሲጠበስ ቆየ። ዙሪያውን ሲመለከት ደቃቅ አሸዋው ሜዳ ላይ ረዥም ብቸኛ ድንጋይ አየ። ወደ ድንጋዩ አመራ። አሸዋው ባህር ውስጥ ድንጋዩና እሱ ራሱ ብቻቸውን የሚንሳፈፉ መሰለው። ወደ ድንጋዩ እየቀረበ ሲሄድ የድንጋዩ መልክ እየተለወጠ ሲሄድ፣ ድንጋዩ አሸዋው ባህር ላይ እየተንሳፈፈ፣ አዳም፣ እየቀረበው መጣ። አዳም እየወደቀ እየተነሳ ሮጠ። ድንጋዩ የተጋደመ ሰው እየመሰለው ሮጠ። ወደቀ ተነሳ ሮጠ። ደረሰ ቆመ። አቤል አሸዋው ላይ ተዘርግቶ። አቤል አሸዋው ላይ ተዘርግቶ። አሸዋው ላይ። አቤል። ወደቀ አዳም፣ ሬሳው ላይ ተደፋ።

"አቤል! አቤል! አቤል! አቤል! አቤል!...."

## ፲

አዳም ተነሳ፣ ሬሳውን አነሳ። ሬሳውን ተሸክሞ፣ አይኑ በእንባ ታውሮ፣ ሲሄድ ሲሄድ ሰንብቶ፣ አሸዋው እየጠበሰው፣ ፀሀይ እየጠበሰው፣ ሬሳው እየከበደው እ...! ብሎ ቆመ ድንገት፣ ተረከዙን ትልቅ እሜኬላ እሾህ ስለወጋው። ቀስ ብሎ አቤልን አወረደ። እሾሁን ከእግሩ መንቀል ሲሞክር እሾሁ ተሰበረ። እግሩ ውስጥ ቀረ። እግሩ ደም በደም ነው። ግን የእሾሁ ደም ጥቂት ናት – የአሸዋው፣ የጠጠሩ፣ የድንጋዩ ስራ ነው አብዛኛው ደምና መላላጥ መገሽለጥ። አዳም እግሩን ይዞ ሲሰቃይ ትንሽ ቆየ፤ ዙሪያውን ተመለከተ። አልፎ አልፎ ድንክ፣ እሾህም ቁጥቋጦ አለ። ራቅ ብሎ አንድ ግራር መሳይ ትልቅ ዛፍ አለ።

አዳም ተነስቶ ልጁን አንስቶ ተሸክሞ እያነከሰ መንገዱን ቀጠለ።

አዳም ፈጣሪውን ማናገር ከንቱ ስለሆነበት፣ አቤልንም ማናገር የማይሆን ስለሆነበት፣ ግን መከራው በዝቶ ሆዱ አልችልም ስላለ፣ ሬሳውን ለግራሩ እያሳየ፤

"በዛ! በዛ! እጅግ በጣም በዛብኝ ቅጣቱ" አለ "ሳላውቅ ስለተሳሳትኩ ይህን ሁሉ ፍዳ ለምን ላከብኝ ያ ፈጣሪ?"

አዳም ከዛፉ ስር ተንበረከከ። "ኧረ ተቃጠልኩ በምህረትህ አትርሳኝ" አለ።

## ፲

ያን ጊዜም የየሱስ ድምፅ ተሰማ፣ እንዲህ ሲል "አልረሳህም እምርሃለሁ። ግን ጊዜው ገና ስለሆነ፣ ማቆያ ማበረታቻ ይሆንህ ዘንድ እነሆ ጥላዬን እልክልሃለሁ።"

ያን ጊዜም ከግራሩ ስር ጥላ ሆነ፣ አዳምም ከፀሀይ ቃጠሎው አረፈ። አዳም ልጁን አቤልን ከዚያው ከጥላ ስር ቀበረው። ወደ ቤቱ በኩል ሲሄድም እነሆ፣ ከየዛፉ ስር ከፀሀይ ቃጠሎ የሚያስጥል ጥላ ተዘርግቶ አየ። ፈጣሪም በምህረቱ እንዳልረሳው አወቀ።

## ፲፩

ሲመሽ ፀሀይ እንዳቀለቀለች፣ ደመናዎቹም በስነ ስርአት ተሰብስበው ቀይ ለብሰው እንድትተኛ እሹሩሩ ሲሉዋት፣ ያን ጊዜ አዳም ቤቱ ደረሰ።

ድክም ብሎት ዱላውን እየተመረኩዘ፣ እየተጐተተ በሩጋ ደርሰ፣

"ቤቶች" አለ በቀጥቃጣ ድምፅ፡፡

ወጣች ከቤት ሄዋን፡፡ ስታየው ደነገጠች፡፡

"ማን ነህ አንተ?" አለችው፡፡

"አዳም ነኝ" አላት "አላወቅሽኝምን?"

"ምነዋ ትከሻህ ጉበጠ፣ ምነው ፊትህ ተጨማደደ፣ አይንህ ተጨናበሰ? ጠጉርህስ ምነው ነጭ ሆነ?"

"አረጀሁ መሰለኝ ልጄ" አላት፡፡

ገብቶ ከእሳት ዳር ተቀመጠ፡፡

# አውራ ዶሮው

## እሀዱ
## እትያልታዬና ልጆቻቸው

የትያልታዬ ገብስማ ዶሮ እማሆይ ትባላለች

ጥሬ እያበጠሩም ይሁን እየቆሉ

"እማሆይ! ኩል - ኩልኩል! እማሆይ፣ ነይ'ንጂ የኔ ቆንጆ" ብለው ይበትኑላታል። እሳቸው እህል ሲበሉ ፍርፋሪ አይቀርባትም

አዳሜ እትያልታዬ መሀን ናቸው ይላል፣ ዶሮይቱ ‹እማሆይ› የትያልታዬ ልጅ መሆንዋን የሚያውቁ ግን ብፁእን ናቸው። ምነው ብፁእን አይሆኑ? እትያልታዬን የማወቅ ብቃት

ብፅእና ሊሆን አይችልምን? እስ ደራሲው፣ ለማን እንዳለው ባይታወቅም

ከብፁእኑ እንዱ ፈርኦን ይባላል - የትያልታዬ ብፁ ድመት:: ቆጭ ሲሉ ፈርኦን ዘሎ ጭናቸው ላይ ይሰየማል:: ሲደባብሱት "ክር--ር!" ይላል በትፍስህተ - ገነት

ጭምድድ ያለው የእጃቸው ቆዳ በጥቁር ሰማያዊ ንቅሳት ስማቸው ተፅፎበታል ከሶስት መስቀል ጋር

*አልታዩ ወርቅ ዋንጫ*

እትያልታዬ በስራ ተጠምደው ጉድ ጉድ ሲሉ ፈርኦን ያጫውታቸዋል

"እቶ ልጅ ጌታ ፈርኦን" ይሉታል

"ሚያው!" ይላቸዋል፣ ከእግራቸው ጋር እየተሻሸ

"ይሄ አቶ ልጅ ጌታ አልአዛር ዛሬ ይመጣ ብለኸው?"

"ሚያው!"

"እኔም እንዲያ ይመስለኛል:: ውይ! ፈርኦንዬ፣ እኔ 'ናንተ'ኮ ባንድ ሀረግ ነው 'ምናስበው፣ ባንድ ክር ነው 'ምንሰፋው፣ ባንድ ድስት ነው 'ምንበላው"

"ሚያው!"

"ይህን በአይጥ መጫወቱን ግን ለምን አትተወውም? አያምርብህማ፣ ልጄዋ!"

"ሚያው?"

"አንተን የመሰለ መኳንንት! ሲሆን እንትኖቹን ተዋቸውና አብረን እንብላ እኔና'ንተ። ለሆድህም ቢሆን የበሰለ፣ እሳት ያየው ይሻለዋል። ላፍህስ ቢሆን፣ ጨዉ ቅመሙ። ‹አይ! ያባት ነው። ፈጣሪ ላይጥ ያዘዘላት ሞት እኛ ነን› ካልክ ደግሞ..."

"ሚያው!!"

"ታዲያ ሞትዋን እንዴ ሰጥተህ አሳርፋታ፣ ፈርኦንዬ"

"ሚያው"

"ጉሽ ፈርኦናችንዬ! ሁሌም እሺ ነው አንተ መቸስ። እምቢ አይወጣህ። እሺ እያልክ ብቻ፣ የልብህን ማድረስ!"

ፈርኦን ፀሀይ ውስጥ ተሰጥቶ መሞቅ የሚያዘወትር ሰላማዊ ድመት ስለሆነ፣ ከሙሴ ጋር እንኳን አይጋጭም። ሙሴ የትያልታዬ አውራ ዶሮ ነው፣ የሚያስደንቅ ህብረቀለማት ላባ ተላብሶ የተከሰተ። አንዳንዴ በፈርኦን አጠገብ ሲያልፍ፣ ባንድ እግሩ ቆም ይልና ባንድ አይኑ ይመለከተዋል፣ ደግሞም በሌላው አይኑ ይመረምረዋል። አቤት አንገቱን ሲያዞር የሚታየው የቀለማት እስክስታ፣ ምናልባት ያ የሚነገርለት እውነት ይሆን 'ንዴ? ያሰኛል

ሙሴ ተራ ዶሮ ሳይሆን ልዩ ፍጡር ነው። ከትያልታዬ ልጆች አንዱ መሆኑ ብቻ አይደለም። በዚያች በቀውጢ ሀሙስ ሌሊት ከጌታችን ከራሱ ጋር ተነጋግሯል ይባልለታል።

ከሆነስ ሆነና ምን ተባባሉ ይባላል? የሚከተለውን ታሪክ፣ መቃ ከጥቁርና ቀይ ቀለም እያጣቀስን በብራና ላይ እንፅፍላችሁ ዘንድ መንፈስ መራን

## ከዐሌቱ
## አውራ ዶሮውና ሰውየው

እንደ ልማዴና እንደ ማንም አውራ ዶሮ (አለ ሙሉ ለትያልታዬ ሲነግራቸው) ሰማይንና ምድርን፣ ከዋክብትና ጭለማዎችን አስተያይቼ አመዛዝኜ ሰአቱን ለማወቅና፣ ከዚያም በኋላ

"ኩኩሉኡ!" ብዬ በመጮህ ሰአቱን ለማብሰር ወይም ለማርዳት በማለት፣ ክንፌ ካብ ላይ ወጣሁ

እና በረደኝ በዚህ በማይበርደኝ ሰአት

ብርድ ከየት መጣ? ብዬ ዘወር ዘወር ስል፣ አየሁት። ከካቡ ወዲያ ባለው አጥር ግቢ ውስጥ ሰውየው ተቀምጧል። በፍርሀት ብርድ ተከናንቧል ተጀቡኗል

ዙርያውን ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እዚህም እዚያም እሳት እሳቱን እየከበቡ ከሌሊቱ ብርድና ጭለማ የሙጥኝ ይላሉ

ያ ፍርሀት ያነቀው ሰውዬ ግን ከሞት የሙጥኝ የሚልበት የለውም

"ኩኩሉ!" አልኩት "ገና ሰባት ሰአት ነው፡፡ እኔ ማምለጫውን ላሳይህ፣ ቀስ ብለህ አንጄ ወዲህ ጠጋ በል፡፡ ከዚህ ወደ ውጪ ከዘለልክ እንደ ምንም ብለህ ታመልጣለህ፡፡ ና!"

"ስለደረስክልኝ ተባረክ!" አለኝ ያ ከሞት የሚፋጠጠው ሰውዬ "ሌላውን ስራህን ቀጥል፡፡ እኔ መሞት ስላለብኝ ነው"

"ማምለጥ እየቻልክ?"

"አዎን"

"ሞት'ኮ ሌላ ቀንም ያለ ነው"

"ዛሬ ነዋ እኔ መሞት ያሰብኩ"

"ለምን ግን?"

"ሌሎች ይድኑ ዘንድ"

"ማናቸው ሌሎቹ?"

"ፍጡራን ሁሉ። አንተም ጭምር"

"ሞተህ እኔንም ጭምር ከሞት ልታድነኝ?"

"አዎን"

"ይልቅ አሁን አምልጥ"

"አይሆንልኝም። ተባረክ" አለኝ

ተመልሼ ትዝታንና ሌሎቹን ሚስቶቼን ተጠጋሁ። ታድያ ያን ወትሮ የማውቀውን እንቅልፍ በየት ላግኘው? ያ ሁሌም ሳልጠራው ራሱ መጥቶ ሸፍን ያረገኝ የነበረው እንቅልፍ አሁን የለም። የሰውየውን ፍርሃት እያሰብኩ ቆየሁ፣ እስከሚቀጥለው የብስራት - የመርዶ ሰአት። መሎሂያዬ ላይ ወጣሁ።

የእሳቶቹ የነበልባል ዘመን አልፎ፣ የፍም ዘመን አልፎ፣ በበረዳቸው ሰዎችና እንስሳት ተከበው፣ አብዛኛው ሰው ተጋድሟል። ኮከቦቹ ግድ የላቸው፣ እንደ ወትሮ እየተጠቃቀሱ በፀጥታ ይቀጥላሉ።

ሰውየው ግን አሁንም ነገ እንደሚገድሉት አውቆ እየፈራ ነው።

"ኩኩሉ! አንተ ሰው፣ አሁንም ለማምለጥ ትችላለህ፣ ና ሂድ ኧረ ባክህ!"

"መሞቱን መርጬው ነው፣ አይዞህ ለኔ አትፍራ"

"አንተ ስትፈራ እየሰማሁህ!?"

"ሞትን ካልፈራሁትማ ምኑን ሞትኩላቸው?"

"ግን ለምን አትተውላቸውም? ራሳቸው ሞታቸውን ይሙቱት"

"እሱማ አይቀርላቸውም"

"እንግዲያማ?"

"ሂድ ተኛ፣ ተባረክ!"

"እዚህ እንደዚህ ትቼህ ሄጄ እንዴት እተኛለሁ?"

"እኔ ሞቼ ለነሱ የዘላለም ህይወት ልገዛላቸው ነው"

"ይህ እንዴት ይሆናል?"

"ሲሆን ታየዋለህ፡፡ በል ሂድ ተኛ"

"እዚችው ልቆይልህ፡፡ ብቻህን ስለሆንክ"

"ሚስቶችህስ?"

"ምንም አይሆኑም፡፡ እኔ ካልደረስኩባቸው ከእንቅልፋቸውም አይነቁ"

ፈገግ አለ ሰውየው፡፡ ፈገግታው ከፍርሀቱ ይበልጣል ሲጠራህና ሲያበራልህ

እስከ ማለዳውና መጨረሻው ጩኸቴ ሰአት እዚያው ካቡ ላይ ተኮራመትኩ፡፡ እንቅልፍማ ከየት?

ለሰውየው ሩብ ሰአት ሰርቄ ጊዜውን አዘገየሁለት፡፡ ጨለማዎቹ እየሸሹ ብርሃኖቹ እየተከማቹ ዘብ ሲለዋወጡ ሲሉ

"ኩኩሉ! ኧረ ባክህን አንተ ሰው ተነሳ እምልጥ! አሁንም ጊዜ አለ" አልኩት፡፡ ፈገግታው ከበፊቱም ይበልጥ አበራ ልበል?

"ሞት ላይቀር?" አለኝ

"ባይቀርም'ኮ ቢዘገይ ይሻላል"

"ሞትን ይህን ያህል ትፈራዋለህ?"

"ምነው አልፈራው?"

"እንግዲያው አይዞህ አይደርስብህም፡፡ ፈርቼ ሳለሁ ደርሰህልኛልና፣ በፍርሃትህ ልድረስልህ፡፡ ላንተ ሞት የለም፡፡ እመለሳለሁ፡፡ ሞትን ድል ነስቼው ስመለስ፣ መምጣቴን የምታበስር አንተ ትሆናለህ"

ሲነጋ ሊገድሉት ወሰዱት፡፡ በሶስተኛው ቀን ማለዳ ሴሊት ሰውየው ከሞት ተመለሰና፣ በህልሜ ይሁን በራዕይ ይሁን ወይም በምን አላውቅም

"ይኸው፣ እንዳልኩህ ተመለስኩ" አለኝ

የምስራቹን ጮህኩ

"ሌላ ጊዜ ስመለስም አንተው ነህ 'ምታበስረው" አለኝ

## ሰለስቱ
# አውራ ዶሮውና አድባርዋ

በመግደላይት ወንጌል ተፅፎ እንደምናገኘው፣ ኢየሱስ ሐዋርያቱንና ደቀ መዛምርቱን "እንግዲህ ሂዱና አስተምሩ" ብሉ ሲልካቸው፣ ከሞት ያስነሳውን አልአዛርንና አጋንንት ያወጣላትን ማርያም መግደላይትን ወደ ስምንታገር ሄደው እንዲያስተምሩ አዘዛቸው:: ለማርያምም አውራ ዶሮውን ሰጣት::

ይህ አውራ ዶሮ መግደላይት ቤተክርስቲያን ጓሮ ሲኖር ሲኖር ቆየና፣ አንድ ቀን ማንም ሳያዘው ወይም ሳይመራው ወደ እትያልታዬ ቤት መጣ

"የማነህ ቆንጆዬ ባክህ?" ሲሉት

"ያንቺ ነኝ ከ'ንግዲህ" አላቸው

"ምክንያቱስ?"

"አድባር ስለሆንሽ"

እትያልታዬ ፈገግ ሲሉ ወርቅ ጥርሳቸው ታየ

## ጥቁር ምላስ

አንድ ቀውጢ ቀን እማማ ትማስ ወርቅ ጧት ተነስተው ከአሮጊት እናታቸው ጋር ተላከፉው ይነታረካሉ። አለሚቱ የአራት አመት ልጃቸው "እማማ ራበኝ" አለቻቸው።

"ቀበሮ ይብላሽ ዛሬ ቀን እንዷለ!" አሉዋት

አሮጊቷ "ትፍትፍ በይባት ልጅቱን። እንዲህ አይነት ክፉ እርግማን አትርገሚያት ልጅቱን። የኛ ቤት ውቃቢ እርግማን ይደርሳል፤ ይይዛል፤ አይለቅም ልባርጊ" አሉዋቸው።

"እንዲህ ነው እንዴ? እንግዲያው ሁለታችሁንም ራብ የጠናበት ቀበሮ ይብላችሁ!" አሉና ከንዴት የተነሳ እያለቀሱ ወደ ገበያቸው ሄዱ እማማ ትማስ።

ገበያ ውለው በርዶላቸው ሲመለሱ፣ ለናታቸው ሎሚ አመጡላቸው፣ መታረቂያ። አሮጊቷ በዘራቸው ሲያረግዙ ያለ ምክንያት መነጫነጭ እንዳለ ቢያውቁም፣ ሳያዝኑ አይቀሩም የገዛ ልጃቸው "ቀበሮ ይብላሽ" ሲሉዋቸው። አይ እማዬ! ሆዴ ግን እንዴት እንደሚሆንልሽ ብታውቂ! እያሉ እያሰላሰሉ፣ በግማሽ ልቡና በግማሽ ጭለማ የውጭውን በር ሲያልፉ፣ ገፍትሮአቸው ሩጫውን ለቀቀ አንድ ትልቅ ውሻ። ሴት ውሻቸውን ሊያሸት የመጣ መሰላቸው እማማ ትማስ።

እበር ደረሱ "እማይ" እያሉ

ዝም

በሩ ተከፍቷል

ገቡ "አንቺ እማይ" እያሉ

ዝም

"አለሚቱ"

ዝም

እማማ ትማስ ሊፈሩ ጀመሩ።

"እስቲ ጨዋታው ይቆይ ኩራዙን አብሩት"

ዝም

"አሁንም ዝም ካላችሁኝ ጨኸቴን እለቀውና ቤቱን የሰፈር መሳቂያ ታረጉታላችሁ፣ ዋ!"

ዝም

"አንቺ እማዬ!"

ዝም

"ሉሚ አምጥቼልሻለሁ"

ዝም

"ኡ! ኡ! ኡ!" ለቀቁት ጨኸቱን እማማ ትማስ

ጐረቤት ደረሰ፤ ኩራዝ ተለኮሰ። ቤቱ አዲስ የተጋጋጠ አጥንት ተንጠባጥቦበታል።

"ስአሊለነ ቅድስት!" አሉ ሰዎቹ

"ምን አራዊት ወርዶ ሁሉቱንም ቁርጭምጭም አርጎ በላቸው በል?" አለ እያ ዘመድሁን፣ ይኸ ጅሉ።

"እ--ርርርር--ሪ!" ለቀቁት አሁንም ጨኸቱን እማማ ትማስ።

"እኔ ነኝ ተርቼ ያስበላኋቸው። በሉ ምን ትሆኑ? ሂዱ ወደየቤታችሁ።"

ጨርቃቸውን ሳይጥሉ እፍፍ ብለው አበዱ። ከእብደቱም ተመልሰው አያውቁ እማማ ትማስ።

"እማይ፣ የኔ እርግማን ይደርሳል፣ ምላሴ ጥቁር ነው። ቀልድ እንዳይመስልሽ" ይላሉ ለብቻቸው ሲያወሩ።

# [illegible]

## ተረት ተረት
## የመኪና ጋራዥ

በየነ የተባለ ሰይቸንቶ ነጂ ነበረ፡፡ የተወለደባትን ትንሽ መንደር ለቆ ትምህርት ፍለጋ በአስራ አራት አመቱ ወዳዲሳባ መጣ፡፡ ትንሽ ከተማረ በኋላ ስራ ያዘ፡፡ እጅግ ትሁትና ታዛዥ ሰራተኛ በመሆኑና የወንደላጤነትን ሞቅታ ባለማዘውተሩ ጥቂት ጥሪት አጠራቀመ

ግን በየነ ጨቅጫቃ ሰው ነበረ፡፡ ከበላዮቹ ሳይሆን ከእኩዮቹና ከበታቾቹ "ንዝንዝ ንትርክ" ያበዛል፤ በሁለት ወይም በሶስት አመት ውስጥ ከሰዉ ሁሉ ጋር ስለሚኳረፍ ሌላ ስራ ለመፈለግ ይገደዳል፡፡ የበላዮቹም ትጋቱንና ታዛዥነቱን

ስለሚያውቁለት ሌላ ስራ ለማግኘት ይረዱታል። እንዲህ ሲል፤ ካንድ ስራ ወደ ሌላ ስራ ሲዞር እጅግ ስለበዛበት፤ አስቦ አውጥቶ አውርዶ አመዛዝኖ ሲያበቃ "ታክሲ ነጂ ብሆን፣ አብሮኝ የሚሰራ ሰው ስለማይኖር፣ ሰውን ማስቀየሜም ይቀራል፣ የጨቅጫቃነት ልማዴም ይተወኝ ይሆናል" ብሎ ተነሳ። ንብረቱን ሸጦ ሁለት አመት ያገለገለች ሰይቼንቶ ገዛ

ጥቂት ሳምንት እንደሰራ ብቸኝነቱና ድካሙ ስራውን በጣም አስጠላው። መኪናይቱ ደግሞ በትንሹም በትልቁም እየተበላሸች ብዙ ገንዘብ በላችው። ለካስ ሳያውቅ ከዚህ በፊት ተጋጭታ ሞተርዋ አጉል የሆነ መኪና ኖሯል የገዛው። ቁርሱም፣ ምሳውም፣ እራቱም ብስጭት ሆነ። እያደር ያየው ሰው ሁሉ ያበሽቀው ጀመር። አንዳንዴ ቀይ መብራት በርቶ፣ አዲስ ቆንጆ መኪና ከፊቱ ቆማ እያብለጨለጨች እንቁልልጭ የምትለው ይመስለውና፤ ሊገጫት ጭርምትምት አድርጉ ሊያሳርፋት ይመኛል። ወይ ሰይጣን! ብሎ ዘወር ሲል ትራፊኩን ያየዋል። ሰይጣኑ የባሰውን ይመጣበታል "ሺ ጥይት ጉራሽ መትረየስ በኖረኝና... በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! እክህደከ ሰይጣን!" ብሎ እርኩስ ሀሳቡን ያባርራል

ይህን የብስጭት ሁኔታውን እያሰበ "ምን አባቴን ብሆነው ይሻለኝ ይሆን?" እያለ ማሰላሰል ሆነ። አንድ ቀን ከመርካቶ ወደ ድሮው ቄራ ሙሉ ሰው ሲወስድ፣ አንዲት አሮጊት "ይገርማል የቁልቢው ነገር" አሉና የሚከተለውን ተናገሩ

"ይኸውላችሁ፣ አንድ ባልና ሚስት ቁልቢ ሄደው በየበኩላቸው ስእለት ተሳሉ፤ አለኝ እያ ወልደገብሬል ሲያጫውተኝ

"ባልየው ወንድ ልጅ የሰጠኸኝ 'ንደሆነ እድሜዬን ሙሉ በየአመቱ ቁልቢ ድረስ እየመጣሁ፣ ቸግሯቸው ልጅ አዝለው

ላየኋቸው ሀምሳ ሴቶች በስምህ አንድ አንድ አዲስ ብር እሰጣለሁ፣ ብሎ ተሳለ

"ሚስቲቱ 'ንግዲህ እናቷ እሷን ሲወልዱ ነው የሞቱት። አያትዋም እናትዋን ሲወልዱ ነው የሞቱት። በዚህ ላይ ደሞ 'መልኳም ጠባይዋም አኳኋኗም ቁርጥ እናትዋን' ይሏት ነበር። እና፤ እኔም በወሊድ እሞታለሁ የሚል ሃይለኛ ፍርሃት ነበረባት። ስለዚህ እሷ ለቁልቢው ‹ልጅ አትስጠኝ አደራህን። ለሚፈልጉ ስጥ፣ አንተ ሃያል ሊቀ መላእክት። አደራ ልጅ አትስጠኝ! ሳላረግዝ አመትህ በደረሰ ቁጥር ሊሊቱን ከድሬዳዋ በእግሬ መጥቼ፤ ቀኑን ተንበርክኬልህ እውላለሁ። አደራህን› ብላ ተሳለች።

"ይገርማል'ኮ የሰው ልብ! ይገርማል የሊቀ መላኩ ርህርሄ ቸርነት። ሴቲቱን ማራት፣ መሀንነት ሰጣት። እንግዲህ ወደ ሀምሳ አመት ሊሆናት ነው ይላሉ፤ እስካሁን አልወለደችም"

"ሰውዬውስ?" አሉ ሴሎቹ

"ሰውየውማ በተሳለ በአስራ አንድ ወሩ፤ ልክ ለታህሳስ ገብርኤል ወንድ ልጅ ዱብ! ከውጭ"

ሴሎቹ ተሳፋሪዎች ይገርማል! ይደንቃል! ሲባባሉ

በየነ በንዴት "ምኑ ነው 'ሚገርመው? የውሸት ታሪክ ምኑ ይገርማል?" አለ

ይህ ያልታሰበ ንግግር ያስደነገጣቸው ይመስል ዝም አሉ ተሳፋሪዎቹ

"ተው ልጄ፣ የሊቀ መላኩን ታምር ውሸት አትበል" አሉት አሮጊቷ

"እርስዎ ምነው ቢያስቡ፣ እቴ? እንግዲህ ሞትዎ ተቃርቧል። ይህን በመሰለ ውሸት የሊቀ መላኩን ስም ባያጠፉ ምን ቸገረዎት?"

"ውሸት መሆኑን በምን አወቅህ?"

"ያስታውቃላ! ወለል ብሎ ይታያል። ደሞ ስራ አጥቶ ገብሬል ይህን ሲፈትል ሲውል"

"ኸረ ፈትል አይደለም ልጆ። ኸረ በስማም በል"

"እዚህ ነው ደርሰናል"

እነሱ ወርደው፣ እሱ ገንዘቡን ተቀብሎ መኪናውን እንዳዞረ

አንድ የተከናነበ ሰውየ እጁን አውጥቶ አስቆመውና የሚሄድበትን ሊናገር አፉን ሲከፍት፣ በየነ ቀድሞት

"ወዴት ነው ጌታው?" አለው በሽሙጥ ድምጽ

ነገር ነገር ሸቶታል እንደተለመደው

"ፒያሳ"

"ሀምሳ ይከፍላሉ?"

"መልካም" ብሎ እፊት ወንበር ገባና በሩን ሊዘጋ ሲል

"ቀስ!" አለው በየነ፣ በድምጹ እያካለበው። ሰውየው በሩን ተወለት። ተንጠራርቶ እሱ ራሱ ዘጋውና "እኛ ስናውቅ ወይ ሙሽርነት ወይ ገዳይነት ነው መሸፋፈን" ሊለው ሲል

"ታዲያስ ሎተሪ! የእድል በር ከፋች!" አለ አንድ ጠንጋራ ወጣት

በየነ "ሂድ ከዚህ! ደሞ አንተን ብሎ እድል ከፋች" አለውና መኪናውን አስነሳ

ትንሽ እንደሄደ ሁለት ወፍራም ሴቶች "መርካቶ" አሉ

"ቦታ አይበቃም" አላቸውና እልፍ ብሎ ቤንዚን አስቀዳ፡፡ ገንዘብ ተቀባዩ ሌላ ሰው ሸኝቶ ሲመጣ

"ወይ ጉድ! ገንዘባችንን ለመክፈል ደሞ እንለማመጣችሁ?" አለው

"ምነው?"

"ተወው ወንድሜ! ተወው!" አለውና አስነስቶ ወደ መንገዱ ሲገባ ሲል፣ አንድ ይሻገሩ የነበሩ ሽማግሌ ድንገጥ ብለው ደፋ ደፋ እያሉ ሲያልፉ

"አጎት፣ እያዩ ነው እንጂ" አላቸው በመንቻካ ዜማ

አንድ በጣቶቹ ሲጻራ የያዘ መልከ መልካም ባለ "አፍሮ" ጉፌሬ አቆመውና "ሰንጋ ተራ" አለው

በየነ "አንተም ከሰንጋ አትሻል!" አለውና አለፈው

ቴዎድሮስ አደባባይ ሊደርሱ ሲሉ ሶስት ሰዎች አቆሙትና መርካቶ አሉት፡፡ የመኪናዋን ማርሽ በንዴት እየለወጠ

"ዛሬ መርካቶ ብቻ ነው" አለ

ተሳፋሪው ላይ አሽሙር ጣል ማድረጉ ነበር፣ የገባው አይመስልም ሰውየው

"ምን ይገባዋል? ለራሱ ገደ-ቢስ ጉደሉ፡፡ እሰይ የኛ ሽፍንፍን!" እያለ እያሰበ በአደባባዩ ወደ ቀኝ ተጠምዝዞ ትንሽ

ሄዶ፤ አንዲት የተሾረበች፣ ግማሽ ጭንዋ እየታየ የቆመች፤ ረዘም ያለች ቀጠን ያለች ወጣት አስቆመችውና

"ቀጨኔ" አለችው

በንዴት የመኪናዋን ቤንዚን ረግጦት ዳገቱን እየጮኸች ስትወጣው

"ቁመሽ ቅሪ" አሳት ውቢቱን አልሰማችውም::

በየነ "ምን አባትዋን ትሰማለች? ለራሷ ልቧ አብጦ:: አይ ብልግና!" እያለ በልቡ እያሰበ፤ ከመርካቶ የመጡትና ቸርቺል ጐዳናን የወጡት መኪናዎች የፒያሳን መንገድ የሚሻሙበት መገናኛ ላይ፤ አንዱን ሌላ ሲይቼንቶ ቦታውን እየነጠቀው "ቶሽ! አለው

"እብድ!" አለው ያኛው

"እብድስ አንተ! የእብድ ዘር! ስነ ስርአት የማያውቅ ውዳቂ..."

በየነ ተሳፋሪውን በሽርደዳ

"ለመሆኑ ጌታዬ፣ ብር ነው ወይስ ሳንቲም የያዙት?" አለው

"ብርም ሳንቲምም ነው" አለ ተሳፋሪው

በየነ ገንዘብ ተቀባይ እጁን እየዘረጋ

"ሀምሳ ሳንቲምዋን ወዲች!" አለ፣ በንቀት ድምጽ

"ስንደርስ ነዋ" አለው ተሳፋሪው

"እሱስ ግድ የለም እንደርሳለን፣ አምጣ"

"በፊት እንድረስ"

"እዚያ ቆመን ጊዜ ከምናጠፋ ብዬ'ኮ ነው"

"ታዲያ'ንደሱ አትለኝም? ምን እንደ አሽከርህ ታዘኛለህ?"

"የለፋሁበት ገንዘብ ነው፡፡ ባዝህስ ምናለበት?"

"እኔም የለፋሁበት ገንዘብ ነው፡፡ አልታዘዝበትም"

"እሺ በል አትጨቅጭቀኝ!"

"የጨቀጨቅከኝስ አንተ፡፡ እዚህ ነው 'ምወርደው"

በየነ መኪናውን እያቆመ

"ምነው? ትንሽ አልባለግከም?" አለው

"የባለግክስ አንተ፡፡ እኔ ከተሳፈርኩ 'ንኳ ስንቱን ሰው ሰደብክ፤ የስንቱን ውሉ አበላሸህ!" ብሎ በሩን ከፍቶ ወጣ፣ ቆመ

በየነ አሁንም እጁን እየዘረጋ፤ የመኪናው ጣራ ስለከለለው ጉምበስ እያለ

"ካልክስ አንተ እርኩስ ገደ-ቢስ ነህ፡፡ በል ስጠኝ ገንዘቤን" አለው

"አልሰጥም"

በየነ በንዴት በሩን ከፍቶ ሊወጣ ሲል

"ፍሬን አልያዝከም" አለው ሰውየው እየሳቀ፤ በሩንም ከፍቶ ተመልሶ እየገባ

በየነ በንዴትና በመደናበር ብዛት ዝም ብሎ ሲያየው፣ ሰውየው ፊቱን ገልጦ ፈገግ አለ

የበየነ ንዴት ድንገት ጠፋ

"የሚካኤል የስእለት ልጅ አይደለህም?" አለው እንግዳው ሰውዬ

"ነኝ"

"ቅድም ታክሲህን ባልሳፈር ኖሮ፤ በኋላ ያገኘናቸውን ሰዎች አሳፍረህ ወደ መርካቶ ስትሄድ ከጭነት መኪና ጋር ተጋጭተህ ትሞት ነበር። ቀጥታ ገሀነም ትገባ ነበር። ግን ዛሬ ሚካኤል ነውና፤ አንተም የሚካኤል የስእለት ልጅ ነህና፣ ከመርካቶ መንገድ እንዳስቀርህ ተገለጸልኝ"

"ለምን?"

"ንስሀ ትገባ ዘንድ፤ ትድን ዘንድ። በል ልሂድ የታዘዝኩት ሌላ ስራ አለኝ"

"ቆይ እስቲ። ከመቼ ወዲህ ነው መልአክ በሽማ ተከናንቦ በታክሲ 'ሚሄደው?"

"መልአክ ነኝ መች አልኩ?" ብሎት ወጣ ከመኪናው ገባ ወደ ቡና ቤት

በየነ ግራ ገብቶት ትንሽ እንደቆየ፤ አንድ ሀሳብ ብልጭ አለበት

"ዛሬ ልሞት ነበር። መቼ ልሞት ይሆን?"

መኪናውን ከፍቶ ሮጦ ገባ ወደ ቡና ቤቱ። የለም እዚያ ሰውየው

"ሰው ጠፋብዎት?" አለችው አንዷ ባለፈገግታ

"ሽማ የለበሰው የት ሄደ?" አላት

"የቱ?" አለችው

"ባለጐፈሬው"

"የምን ጐፈሬ?"

"አሁን አሁን የገባው"

"እርስዎ ነዎታ"

"እረ ከኔ በፊት"

"ማንም አልገባም እረ"

"ቢገባስ መች ገባ ትላላችሁ?" እያለ ወጣ

"ወይ ጉድ! አሁንም አሸሙር! አሁንም ጭቅጭቅ! አይለቀኝም ማለት ነው በቃ:: ተቆራኝቶኛል ማለት ነው" እያለ እያሰበ የሰይቼንቶውን በር ሊከፍት ሲል

"ይሄዳል?" አሉት አንዲት ቀጭን ቋንጣ መሳይ ሴትዮ

"ወዴት?" አላቸው

"ወደ ቂራ"

ገቡ:: መኪናውን ሲያስነሳ በሀሳቡ "ቂራዎች፣ ቋንጣ ይዘን መጣንላችሁ!" አለ "...አይለቀኝም በቃ:: ተቆራኝቶኛል"

## በሰባራ ሽጉጥ

እንግዲህ ጌቶች በወንድ ልጅ ደንብ እሰው ፊት ጉራቻቸውን የነፉ እንደሆነ፣ እሜቴ ንቀት ለማሳየት ሲሉ፣ ውብ ረዥም ባለንቅሳት አንገታቸውን ወደ ላይ ምዝዝ እያደረጉ፣ በቅንድባቸውና በትናጋቸው "ቅ!" ይሉና "አለቅን በሰባራ ሽጉጥ!" ይላሉ። ጌቶች ጭስስ እርር ቅጥል ድብን ሲሉ፣ እሜቴ አንጀታቸው ቅቤ ጥጥት!

ጌቶች በልባቸው "በዚህ ውብ አንገትሽ ሹል ማንቁርት ይብቀልብሽ!" ብለው ይረግሙዋቸዋል "ከስሩ ስልቻ 'ሚያህል እንቅርት ይንጠልጠልብሽ! የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይለጥፍብሽ! አፍረሽ ፈገግ ስትዪ አራት ጥርስሽ ተሸርፎ አፍሽ የእባብ ዋሻ ይምሰልብሽ! አሜን አሜን አሜን!"

እሜቴ እንደሆኑ አንገታቸው የበለጠውን እያማረበት ይሄዳል እንጂ፣ እንኳን ማንቁርት እንቅርት ቀርቶ ብጉር አያውቃቸውም

ጌቶችና እሜቴ ቤታቸው ፎቅ ነው። አሽከር ምድር ቤት ይተኛል፣ ገረድ ፎቅ (ይህ የምድርና የፎቅ ነገር እየተስተዋለ)

እንግዲህ ጌቶች የለየላቸው ቅንዝረኛ፣ የወጣላቸው ሀጅ ነበሩ። ሰዎች እራት ይጋብዙና፣ የገዛ እንግዶቻቸውን ሚስቶች የሰላምታ እያስመሰሉ ይስሙዋቸዋል፣ የቀልድ እያስመሰሉ በጆሮዋቸው የቅንዝር የምንዝር ይነግሩዋቸዋል። ሴቶቹ በሞቅታ ያስካካሉ…

***

…ከቅብጠት እለታት አንድ የቅሌት እለት፣ ጌቶች እግራቸውን ተሰበሩ በመኪና አደጋ። ደግነቱ ሲምራቸው ያን ጊዜ ብቻቸውን ናቸው። ሴት ይዘውማ ቢሆን ሌላ ነገር ነበር

ጌቶች ስድስት ወር ሙሉ ካልጋ ሳይወረዱ

ቀን ቀን እሜቴ ያክስቴ ልጅጋ ግሮሰሪ ጭቅና ፍለጋ፣ እንትናጋ ምናምን ፍለጋ፣ እያሉ ያለ የሌለ ምክንያት እየተናገሩ ይዞራሉ (ቁጭታቸውን ለመወጣት ሊሆንም ይችላል) በዚህ መሀል፣ የጓደኛ ሚስት መጠበቅና ማፅናናት ወግ ነው ሲባል፣ ከጌቶች ጓደኞች ሶስቱ እሜቴን ይሻሙዋቸው ጀመር፣ ዘመነ ሽሚያ አልፎ ዘመነ ጋርዮሽ ተተካ። ይሽ ሁሉ ሲሆን ሶስቱም አንድ አንድ ምሽት እየመጡ ጌቶችን ይጠይቁና እሜቴን ሸኘን'ንጂ እያሉ፣ መሸኛኛቱ ላይ ቀጠሮ እየተቀባበሉ፣ ጌቶች ሚስታቸውን ለሶስት ሲያበስሉባቸው ሲያበሳስሉባቸው ይሰማቸዋል። ተመካክረው ሳይሆን፣ እያንዳንዳቸው የግል ቂማቸውን ለመወጣትና የግል ጉምጅታቸውንም ለማርካት።

"ወይኔ እቶ ጌቶች!" አሉ ጌቶች፡፡ ተበሳጭተው ሳይሆን እንዲያው ለወጉ ለማእረጉ

ጌቶችስ ምናቸው ሞኝ ነው? እሜቴ ምናምን አሰብኝ ብለው ሲወጡ፣ እሳቸው ገረዲቱን ጠርተው ምናምን ማለት፡፡ እሷ መቅበጥ መንቀባረር ስትጀምር፣ በልባቸው "ምነው መሽኰርመምሽ እንደ በሬ ሻኛ" ይሉና፣ በሰራተኛ አስተዳደር ደንብ (ግን በምስጢር) የሶስት ወር ደሞዝዋን ሰጥተው "ሂጂ፡፡ ነገ ሌላ ስራ ታገኚያለሽ፣ የሶስት ወር ደሞዝ አተረፍሽ" ይሉዋታል፡፡ ላይ ላዩን በቁንጥና በቅጥ እየተንቀባረረች እየተኰሳተረች፣ ውስጥ ውስጡን ግን ሳቅ ሳቅ እያለች፣ ውልቅ እንደ ቤት ኪራይ

አዲስ ገረድ ስትቀጠር ያዩዋታል፡፡ ለወጉ ለስርዓቱ ነው እንጂ ጌቶች እንደሆኑ ማንም ሴት ብትመጣ እንጣጣሪ አይናቸው ውበቷን ጉልጉል አድርጎ ወለል አድርጎ ጉላ አድርጎ ያሳያቸዋል፡፡ ተራው ወንድ አስቀያሚ ናት ብሎ የሚያልፋትን ሴት ጌቶች የውበት ጉልላት አድርገው ይጐመጁዋታል፣ በልዩ ጥበብ ስለሚያዩዋት፡፡ በዚህ አኳኋን በስድስቱ ወር ውስጥ የሰባት ገረድ ውበት አዩ

ጌቶች እግራቸውን ከመሰበራቸውም በላይ ከ'ሜቴ ጋር በስጋ እጅግም አይጣጣሙ፡፡ ስለዚህ እሜቴ ማታ ማታ ታች ይወርዳሉ፡፡ ወጥ ቤቱን እቃ ቤቱን ለማስተካከልና ሌላም ስራ ለመስራት፣ በጭለማ ካሽከርየው ጋር| ዝም፡፡ ጭጭ፡፡ አንድ ማታ ጌቶች እያነከሱ ሄደው ገረድን አንዴ ብለው ተመለሱ፣ እንዲያው ለጨዋታው፣ እሜቴን ለመብለጥ ለዚች ማታ፡፡ እሜቴ ታች የወጥ ቤት ስራቸውን ሰርተው ተመልሰው ተጣጥበው እፎይ ብለው ጋደም፡፡

ሁለቱም ፍጥጥ

ሁለቱም ድንገት መሳቅ!

"ብዙ ብዙ የሚያስቅ ነገር አለ" ተባባሉ እየተሳሳቁ

ጌቶች ጨዋታው ስለጣማቸው አሁንም እሜቴን ለመብለጥ አሉና አሽከርየውን ጠርተው "እንወራረድ በመቶ ብር አሉት "ገረድን የተኛሀት እንደሆነ መቶ ብር ላንተ፣ ያቃተችህ እንደሆነ ተረታህ፣ መቶው ብር ቀረብህ"

አሽከር ገረድን አስር ብር ከፍሎ ትኝት! ዘጠና ብር አተረፈ

"በሌላ መቶ ብር እንወራረድ ፍቅር አታስይዛትም" አሉት፡፡ በዚህ በጌቶች ብልሃት የተነሳ ሌሊት ሌሊት አብረው በድብቅ አሽከር ቤት ማደር፡፡

አንድ መዘዘኛ ሌሊት እሜቴ ሳት ብሏቸው አሰኝቷቸው፣ ተነስተው በጭለማው ወደ አሽከር ቤት፡፡ እንደተለመደው በሩን በመዳፋቸው አሻሹት፣ ድምፅ በሩቅ እንዳይሰማ፡፡ አሽከር ዝም፡፡ በጥፍራቸው አከኩት በሩን፡፡ አሽከር ዝም፡፡ አንኳኩ በቀስታ፡፡ ዝም፡፡ በሃይል አንኳኩ፡፡ ጭጭ

እሜቴ ተናደው "እንዴት ጠገበ ይኼ ጨምላቃ!" እያሉ እያጉረመረሙ ወደ መኝታ ቤት ሲገቡ፣ ጌቶች ሳቃቸው እንዳያመልጣቸው ትራሱን ነክሰው ይንፈራፈራሉ

ገባቸው እሜቴ፡፡ ብልጭ አለባቸው፣ እሳት ለበሱ እሳት ጉረሱ እሳት ሆኑ፡፡ ሽጉጡን ከጌቶች ራስጌ ከፍራሹ ስር ላጥ አረጉና፣ ጌቶች ጭንቅላት ላይ እያነጣጠሩ

"በል አሁን ሳቅ!"

ጌቶች ትራሱን ወድያ ብለው ሳቃቸውን ለቀቁት - "ቂቅ ቂቅ ቂቅ!"

እንካ ቅመስ! ሽጉጥ በሌሊቱ አስተጋባ

ጌቶች ፍንግል!

እሜቴ ድንግጥ!

ታሪኩ እልቅ! በቃ

"ኧረ ተው አይበቃም ነገሩ ይቀጥል፣ በምትወደው ታቦት ይዘንሃል ቀጥልልን" ካላችሁም ይኸው

እሜቴ ደንግጠው እየተርበተበቱ ጣታቸውን እያንቋቁ "ወይኔ በሞትኩት! ሰውየው ፍንግል አለ። ምን ይሻለኛል ምን ልሁን ምን ላድርግ?" እያሉ ሲደጋግሙ፣ ጌቶች ከተፈነገሉበት

"ልብስ በሻንጣ ገንዘብ በቦርሳ፣ ወደ ባቡር ጣቢያ!" አሉ

እሜቴ "እውነትም እውነትም! ዤከተፍ - ዤከተፍ - ዤሹዜም! እያልኩ ወደ ጂቡቲዬ። እዚያ ማን ይደርስብኛል?" እያሉ ገንዘብ በቦርሳ ልብስ በሻንጣ አርገው ሊወጡ ሲሉ

"ጅብ እንኳ አያስፈራም፣ ማጅራት መቺ እንዳይበላሽ" አሉዋቸው ጌቶች ከተፈነገሉት ሳይነሱ

"ይብላኝ በቃ። እንክት አርጉ ይብላኝ። ኧረ መብላት ቀርቶ ይዋጠኝ! ዋጥ ስልቅጥ ያርገኝ!! አንተ ምን አገባህ?" ብለዋቸው ሊወጡ በሩን ሲከፍቱ

"ለምንድነው 'ምትሄጂው?"

"እህ? ሰውየው አብዷል 'ንዴ? ባሌን በሽጉጥ ገድዬ ሳበቃ ታድያ፣ ፖሊስ እስኪመጣ ቁጭ ብዬ ልጠብቅ?"

"አልሞትኩም'ኮ"

"እሱን ተወው! አታለህ ልታስይዘኝ? መስሎሃል! ሞኝህን ፈልግ" አሉዋቸውና ወጥተው ሄዱ

ጌቶች ከተፈነገሉበት ሳይነሱ "አበደችላችሁ ሴትዮዋ!" ብለው በደስታ ሲስቁ ሲስቁ ሲስቁ - ቢያዩ ጊዜ አይነጋም...

# ዘርና አጋፋሪ እንደሻው

አጋፋሪ እንደሻው የትም ቢሄዱ የሳምንት ስንቅ ተጭኖ የሚከተላቸው፣ ስንቁ የሚሉት በቅሉ ነበራቸው። አጋፋሪ እንደሻው ካደባባይ ሲመጡ፣ ወይም ከቤተስኪያን ወይም ከጉዞ ሲመለሱ፣ ገና ከጠጂቱ ከጭን በቅሎዋቸው ሳይወርዱ፣ የቤት አሽከሮቻቸውን

"ሰፈር ደህና ነው?" ይሉዋቸዋል

"ደህና"

"ሁሉም ደህና ነው?" ይላሉ (ለማረጋገጥ ለማስመሰል...)

"ደህና"

"በሰፈሩ የሞተ የለም?" (...አዳሜ አዲሳበቤ ይምሰለው ብለው ነው 'ንጂ፣ እሳቸው 'ንደሆኑ ሞትን መፍራት ከተዉ ቆይተዋል...)

"እረ የለም"

"የታመመም የለ?" (...ከዚያች ከጠላ ትንታ ወዲህ፣ ስለሞት ሲያስቡ፣ ፈገግታ 'ንጂ ፍርሀት ከየት መጥቶ?...)

"የለም"

"መርዶም አልተሰማ?"

"የለም"

"በሰፈሩ አንድ ሀሙስ የቀረውም የለ?"

"እረ አላየንም?"

"ብታዩስ የት ታስተውላላችሁ? እውር ሁሉ! በሉ ስንቁ ተሰናድቶ ደጃዝማች ግቢ ድረስ እንዲላክልኝ"

"እሺ"

"ደህና ሁኑ" ይሉና ውልቅ! አጋፋሪ እንደሻው

ውሽማቸው ወይዘሮ እገሊት ቤት ይሄዱና፣ ከበቅሎ ወርደው ልጓሙን ለገብሬ ሰጥተው፣ አንድ ሁለቴ ተገላምጠው መንገዱን ቃኝተው፣ ማንንም ስለምንም ሳይጠይቁ ጥልቅ!

የወይዘሮ እገሊት ፈገግታ ብቅ!

ሰውየው ሴትየዋን አፈፍ! እቅፍ! ጭምቅ!

በፍቅር በቅንዝር እንቅ - እንቅንቅ!... እቅፍቅፍ ጭንቅንቅ!

(ይህ ሲሆን ሳለ፣ ገብሬ ከጠጂቱ ላይ ኮርቻውን አገሎ፣ ዳውላውን አራግፎ፣ ለሷና ለስንቁ ውሃና ሳር ሰጥቶ፣ ለራሱ

ጥቂት አርፎ ሲያበቃ፣ ስንቁን እየጐተተ ወደ ደጃዝማች ዳኛቸው ቤት ይሄዳል፣ ያጋፋሪን ስንቅ ለማድረስ)

ሲመሽ ሲል፣ ወይም በነጋታው፣ አልያም በተነገ ወድያው፣ አጋፋሪ ከወይዘሮ እገሊት ቤት ይወጡና ወደ አንዷ ቤት ያመራሉ:: ወይም ወደ ሌላዋ ቤት:: የቀጠረቻቸው ሴት ከሌለች ወደ እማማ ማዋይሽ ቤት ያዘግማሉ

***

እማማ 'ማዋይሽ ባላቸው ሽማኔ፣ እሳቸው ራሳቸው ደሞ ፀጉር ስሪት ናቸው:: ለይህ ነው አጋፋሪ የተጠጉዋቸው:: እማማ 'ማዋይሽን መጠጋት፣ ብዙ ሴቶችን ለማየት... ለመተያየት... ለመፈቃቀድ... ለመጠቃቀስ... ለመቀጣጠር ያመቻል በማለት

እንግዲህ ከዚያች ሞትን ለጥቂት ካመለጡዋት የጠላ ትንታ ወዲህ፣ አጋፋሪ እንደሻው ሳይታወቅባቸው፣ የወጣላቸው የተዋጣላቸው ሀጅ ውጥኗቸው ነበር:: እንዲያውም ሞትን የሚሽሹ እያስመሰሉ ሴት ሲያሳድዱ ነበር እሚውሉት... ሴት ሲያጣጥሙ ነበር እሚሰነብቱት... ሴት ሲቀማምሱ ሴት ሲጕራርሱ፣ ሴት ሲጠጋገቡ ነበር እሚከርሙት:: (አይ! እሱማ እውነት ነው፣ ሴት አይጠገብም፣ አንዳንዴ ሰውነት ካላረፍኩ ብሎ ይለግማል 'ንጂ፣ ከፋቱ ምቀኝነቱ!!)

አጋፋሪ እንደሻው ሴት አያማርጡም:: ካገኙ እሜቴንም አይለቁ፣ እንኩዬንም አይምሩ:: ለአይናቸው ወላድ መስላ ከታየቻቸው ሳዱላዋም ታንገበግባቸዋለች፣ ጨምዳዳዋም ታስጐመጃቸዋለች "ዘቢብስ ጨምዳዳ አይደለ?" ይላሉ ውቃቢያቸው ውብ አሮጊት ያሳያቸው እንደሆነ "ያብርሃም ሚስት ሳራስ በሰማንያ ስንት አመትዋ ወልዳ የለም?..."

ሆኖም አጋፋሪ ሴት ሲሄዱ ለዘር ብለው ይሂዱ 'ንጂ በህይወታቸው ሙሉ የማትጣፍጥ፣ ልብ የማታጠፋ ሴት ከቶ አጋጥሟቸው አያውቅም "ሴት እጣዬ ነዋ!" ይላሉ ለራሳቸው ወይም ለጓደኛቸው "ሌላ ምንድነው?"

አጋፋሪ ሴት ሲያዩ፣ ክርስቲያን አይሉ እስላም፣ ሀበሻ አይሉ ባእድ፣ ዘመድ አይሉ ባዳ፣ ጋለሞታ አይሉ የሰው ሚስት፣ እመቤት አይሉ ገረድ፣ ሸርሙጣ አይሉ መነኩሲት፣ ጉፈሬ አይሉ ሹሩባ፡፡ ሴት ስትባል ሁሏም ቅድስት የህይወት ምንጭ በመሆንዋ

አጋፋሪ ሴት ካገኙ፣ ቀን አይሉ ማታ፣ ፆም አይሉ ፍስክ፣ ውርጭ አይሉ ሀሩር፡፡ ሴት ካለች ማንኛውም ሰአት ገንታዊ የዘር መዝሪያ ሰአት በመሆኑ

አጋፋሪ ሴት ሲያቅፉ፣ ወፍራም አይሉ ቀጭን፣ ረጅም አይሉ አጭር፣ ቀይ አይሉ ጥቁር፡፡ ይሄ ሁሉ ሴትነትዋን ቅድስትነትዋን የማይለውጠው በመሆኑ

"መዝራት ነው!" ይላሉ ለራሳቸው "መዝራት - መዝራት መዝራት!... አልፎ አልፎ መብቀሉ ይቀራል? ቂ-ቂ-ቂ-ቂቅ!"

እንዲህ ሲሉ፣ አጋፋሪ እንደሻው ሞትን የሚሸሹ እያስመሰሉ ያዲሳባን ሴቶች ሲያሳድዱ፣ ሰባ ሰባት አመት ሆናቸው፡፡ ደግነቱ ያጋፋሪ ሰውነት ያን የሚፈልገውን እረፍት ያገኛል፡፡ ምን ጠፍቶ? ጤፉ ከአድአ ይጫናል፣ ማሩ ከጎጃም ይመጣል፣ ምስጋና ይግባውና!

ኧረ ፈጣሪ የሰጠውን ሰው ቆጥሮ መቼ ይዘልቀዋል? ያውም በአህዝና በፈደላት ሊቆጠር ያጋፋሪ ፀጋ!? እንዲያው በደፈናው "ተሰጥቷቸዋል" ብለን እናልፋለን

አጋፋሪ ገላቸው ከደከመ፣ እሳቸው እንደሚሉትም ከሰገመ፣ ወደ ጓደኛቸው ቤት ይሄዱና አንድ ወይ ሁለት ቀን ያርፋሉ፣ እየተመገቡ፣ እየጠጡ ጠጁን፣ እያወጉ ወጉን፣ እየደረደሩ በገናውን፣ እያስላሰሉ ስልቱን የሴቱን፣ ሞትን ማሸነፊያ ምስጢር የተደበቀበትን የሴቱን ብልቱን፣ የሴቱን ድንቅ ተአምራቱን፣ እያሰላሰሉ እያሞጋገሱ...

***

...ቡሄ አርብ የዋለ እለት፣ አጋፋሪ እንደሻው ሞተው፣ ሴቶች እየተላቀሱ እንባ በሽክና እየተራጬ ሊቀብሩዋቸው እንደ ድፎ ዳቦ በኮባ ቅጠል ጠቅልለው ባገልግል ውስጥ አኑረው ሲወስዱዋቸው

አጋፋሪ ድንገት ኮቦውን ገለጥ ገለጥ አርገው ብድግ ይሉና፣ ያገልግሉን ክዳን በርግደው ሲወጡ

ሞት የቡሄ ጅራፍ እያዞረ ሊገርፋቸው ሲቃጣ

እሳቸው ባገልግሉ ክዳን እየመከቱ ሲሸሹ

እሱ እያሳደደ ደጋግሞ ጅራፉን ሲያንጉድባቸው

እሳቸው ከመሬት የቆረጥን ጥምጥም አንስተው፣ እባቡን በጅራቱ ይዘው እንደ ጅራፍ እያዞሩ ዞረው፣ ሞትን አርባ ሊገርፉት ሲጠጉ

እሱ ፈርቶ "አይ! በእባብ አይሆንም! አይ እምቢዮ!" እያለ ሲሸሽ

እሳቸው "አይዞህ እባብ አይደለም፣ ልጥ ነው" እያሉ ሲያሳድዱት

ዙሪያውን የቆሙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ነብስ-ጡር ሴቶች "እልልልል! እንደሻው ድል ነሳው! እልልልል! እንደሻው የልጁ አባት! እልልልል!" ሲሉ

ሞት እልልታውን ሰምቶ ዙሪያውን ሲገላመጥ፣ እና ከአድማስ እስከ አድማስ አገሩን ሙሉ እርጉዝ ሴት ሞልቶት ሲያይ... ምናልባት ችሎ አጋፋሪን ራሳቸውን ቢገድልም እንኳ፣ ዘራቸው ምድርን ስለሞላት፣ ያን ሁሉ ዘር ችሎ ባንዴ እንደማያጠፋ ሲገባው፣ ሞት በዚህ ተናዶ ጥርሱን ሲያፋጭ... የቅንዝራም ልጅ ቅንዝራም ነውና፣ ያ ሁሉ ዘራቸው ደም በየተራው ብዙ ብዙ ዘር እንደሚያፈራ ሲታየው፣ በብስጭት ነጭ ፀጉሩን ሲነጭ... ያ የዘራቸው ዘርም ራሱ እንደገና ሌላ ብዙ ብዙ ዘር እንደሚተካ... የመባዛት መባዛት መባዛት እየሆነ ነገሩ ማለቂያ እንደሌለው ሲገነዘብ... እና ይህን ሁሉ አስቦ አስቦ ሲታክተው ስልችትችት ሲለው፣ ብስጭትጭት ሲልና ተስፋ ቆርጦ መሬት ተቀምጦ እድሉን እያማረረ ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ፣ እና --

ይሄ ሁሉ ሲሆን፣ የገደል ማሚቶ የሴቶቹን እልልታ ተቀብላ ወስዳው ኖሮ፣ ከጋራ ጋራ እያቀባበለች፣ ከተራራ ተራራ እየወረወረች፣ ከገደል ገደል እያንከባለለች፣ ምድረ ሀበሻን አዳርሳ ተመልሳ መጥታ፣ በዚያ ሁሉ ሴት ድምፅ "እልልልል! እንደሻው ድል ነሳው! ድል ነሳው! ድል ነሳው!" ስትል

ሴቶቹ እንደገና በህብረት "እልልልል!" ሲሉ

የድምፁ ሞገድ ብርታት የዘሩን ብዛት ሲያመለክት

ሞት ሀሞቱ ፈሶ ስሜቱ ደንዝዞ፣ ራሱን ደፍቶ ከተቀመጠበት እልልታውን እየሰማ፣ አጋፋሪ ከበላዩ ቆመው በእባቡ አርባ ሲገርፉት፣ ሲገርፉት፣ ሲገርፉት፣ ሲገ --

ብንን ብለው ይነቃሉ አጋፋሪ እንደሻው ዘብሄረ አዲሳባ

ቂቂቂቂቅ! ባናሸንፈውም አስፈራርተነዋል! ቂቂቂቂቅ! ለዚያውስ ማን ያውቃል? እናሸንፈው ይሆናል'ኮ ቂቂቂቂቅ!

***

እንዳጋጣሚ ሆኖ፣ አጋፋሪ እንደሻው ጓደኛቸው ቤት አድረው ይህን ህልም አይተው ነግቶ ሲነሱ፣ ገብሬን ልከው አስጠይቀው በከተማው ተላላፊ በሽታ መግባቱን ስለሰሙ፣ ስንቃቸውን አስጭነው ወደ እንጦጦዋቸው ሸሹ:: እና እንደ ልማዳቸው አፋፉ ላይ ቆመው አዲሳባቸውን በሩቅ መነፅር ቁልቁል ሲመለከቱዋት "የእገሌት ቤት ያውና፣ እግዜር ይባርከው! የእንቶኒት ቤት ደሞ ያው እዚያ ወድያ፣ ያን ቤት ክፉ አይንካው!" እያሉ ሲመለከቱ ሲመለካከቱ

ድንገት አንድ ሀሳብ አስደነገጣቸው:: የከተማው ቤቶች ከመጠን በላይ ተጠጋግተዋል:: ተላላፊ በሽታ ቢገባ አብዛኛዎቹን ሰዎች ሊለክፋቸው ይችላል! ገዳይ በሽታ ከሆነም ሊፈጃቸው ይችላል::... እግረ መንገዱን ያጋፋሪንም ዘር ሙልጭ አርጎ ሊጨርስ ይችላል:: ያን ሁሉ አመታት በተስፋና በትጋት ሲዘሩ ኖረው ኖረው፣ አቶ ሞት ሆዬ ብቅ ብሎ እንደ ቀልድ ባንድ ወራት ዘራቸውን ሊያጠፋ? እንዲህ በቀላሉ ሊያሸንፋቸው?

"አይሆንም" አሉ አጋፋሪ ለብቻቸው "ካዲሳባ ውጭም መዝራት ይኖርብኛል:: እንዲያውም በሃገረ ሀበሻ ሁሉ እየዞርኩ ዘሬን ካልዘራሁ አይሆንልኝም! እኔ እንደሻው!... ምንስ ቢሆን የበልሁ ልጅ አይደለሁም 'ንዴ? ሆ! ዘራፍ! እንደሻው በልሁ ወሰንየለህ! ዘራፍ!?"

ከዚያ ቀን ወድያ አጋፋሪ እንደሻው በልሁ ወሰንየለህ የሳምንት ስንቅ ሳይሆን የወር ሸንቅ እያስጫኑ ከከተማ መውጣት አመጡ…

***

አንድ ምሽት በደጃች ዳኛቸው እልፍኝ በጠጅ ሞቅታ ሰአት ጓደኛቸው በዚህ እየቀለዱባቸው

"እንግዲህ ጠቅላይ ግዛቶቹን ሁሉ እንዴት ብለህ ልታዳርስ ይሆን?" አሉዋቸው

"ጠቅላይ ግዛቶቹን ሁሉ አንድ በአንድ ባላዳርስ ምን አለ በለኝ"

"ያዬ አገር'ኮ ሰፊ ነው፣ እንደሻው"

"ሰፊ መሆኑ መልካም!"

"እሺ። እድሜና ጤና ሰጥቶህ አገሩን ሙሉ አዳረስክ እንበል። ከዚያ በኋላስ?"

"እከልሰዋለሁዋ! ቀጥዬም እሰልሰዋለሁ። ቀጥዬም…"

"አይ እንደሻው! አንተስ ከንጉስ ሰለሞንም ባስክ"

"እንዳፍህ ያርግልኝ፣ ልጄ!" አሉና አጋፋሪ እንደሻው፣ ባለ ስምንት ጆማት በገናቸውን አንስተው ይደረድሩላቸው ጀመር

*"ጎዳና… አንተ ጎዳና፣ መንገድ… አንተ መንገድ፣*
*ሰው እንዳይሄድ የለምና… ሰው እንዳይሄድ!*
*ጎዳና… አንተ ጎዳና፣ መንገድ… አንተ መንገድ፣*
*እኔም ልነሳ፣ ተከትዬህ ልሂድ… አንተ መንገድ!"*

***

በሴት የመጣ አጋፋሪ እንደሻው እንደ ትጉ አትክልተኛ እየሆኑ ሄዱ። ገና የሶስት አመት ጨቅላ አይተው፣ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ ምን አይነት ውብ ሴት እንደምትሆን ይገምቱ፣ በግምታቸውም ይደሰቱ ነበር። ውስጣዊ አይናቸውን ወደ ነገ በኩል አንጣጥረው፣ ያችን ከዚች ልጅ የምትበቅለውን ውብ ሴት እያዩ ያደንቁ ነበር።

ሴት ልጅ ገና ባለ ኮልኮሎ ሆና ቅልቦሽ ወይም ድብቆሽ ስትጫወት ወይም ስትዘል፣ የኮልኮሎዋ ዛጉል ሲወዛወዝ ሲንቀጫቀጭ፣ አይ ደስ ማለትዋ ከነሽራፋ ፈገግታዋ! "አይ አንቺ የነገ ተስፋ!" እያሉ በልባቸው

"የማነሽ ልጅ፣ እምዬ?" ይሏታል አጋፋሪ

ባለ ኮልኮሎይቱ ልጅ በመሆንዋ ቀና ብላ በእምነት ፈገግታ ታያቸውና "ሴት ልጅ ትክ ብላ ሰው አታይም" ሲሉ ያስታወሰች ይመስል ወድያውኑ እያቀረቀረች

"ያባባ እገሌ" ስትላቸው

"ቆንጆ ልጅ ነሽ! ታድለው አባትሽ! ያሳድግሽ። ትፍ-ትፍ-ትፍ! እደጊ እምዬ! ደህና ሁኚ" ይሏትና ፈገግታዋን ተሸልመው እያለፉ

"የዛሬ ሃያ አመት ሰው ይበለን እምዬ!" ይሏታል፣ ውስጡን "ምናልባት እኔ ባይሆንልኝ፣ ልጄን ወይም የልጅ ልጄን አስተናግጂልኝ አደራ!" ሲሉ ይማፀኗታል። ማን ያውቃል? ፀሎታቸው ይደርሳት ይሆናል

***

እንዲህ ሲሉ አጋፋሪ እንደሻው፣ ሞትን የሚ
እየመሰሉ ሴትን በትጋት ሲያሳድዱና ዘራቸውን በተስፋ ሲዘሩ
ስማንያ ስምንት አመት ሆናቸው

እና፣ ያ ሁሉ ስራቸው ተጠራቅሞ በቁና ተሰፍሮ
ቀድሞዋቸው ተከምሮ ሲጠብቃቸው ቆይቶ ኖሮ፣ ከአስታት እን
አርብ ቀን፣ ከሶስት ወር ጉዞ ሲመለሱ ቂጥኝ አውጥተው መጡ።
ያውም ምስሬ ቂጥኝ ሳይሆን፣ ማጭዴ ቂጥኝ - ይሄ ከንፈር
'ሚቆራርጠው፣ አፍንጫ 'ሚጎማምደው፣ አጥንት 'ሚያበ
ብሰው፣ አእምሮ 'ሚያሳብደው ቂጥኝ

## ኩሊ! ኩሊ

"አቤት እመቤቴ። ልሸከማ።... አዎን፣ ኩሊ ነኝ... እርስዎ ከእግሬ ምን አሉት? እንኳን አንድ እግር ለምን ግማሽ እግር ብቻ አይኖረኝም? እርስዎ 'ሚፈልጉት ሸክሙ 'ዚያ መድረሱን... እሜትዬ፣... ያገሩን ዋጋ ይከፍሉኛላ፤ ሌላ ምንድነው?...

በዚህ በኩል ነው?... ሀምሳ ሳንቲም?! ይቅርብኝ፣ እሜትዬ። ባለሁለት እግሮቹ ሁለቴ ይሸከሙት መስሎት 'ንዴ የድካሜን ግማሽ ዋጋ ብቻ 'ሚከፍሉኝ? ኧረ ጭቦ ነው!... ኧረ 'ንዲህ ዓይነቱ ነገር ቀርቷል። እንደ ድሮ እንዳይመስሎት! ማን ነው እሱ የስራህን ግማሽ ዋጋ ብቻ ከፍዬህ ይብቃህ 'ሚለኝ? ድሮ ቀርቶ!... እግዜር ይስጥልኝ፣ እሜትዬ! እንዲህ እየተዛዘኑ ነው ኑሮ ማለት። ልጅዎን ያሳድግሎት!"

# ኤሲን ድንጋይ ያለበስክ

የአሮጊት ድምፅ "ተመልከት! አንተ ሰው ተመልከት! ወደኋላ ተመልከት!" አሳቸው አቶ ወንዳፍራሽን፡፡ ዘወር ብለው ቢያዩ

ግሬያ ጥድፊያ ነው መንግስተ ሰማያት ለመግባት፡፡ የአቶ ወንዳፍራሽን ታላቅ ወንድም ጋሼ መላኩን ሰዎች እየቀደሙዋቸው ያልፋሉ፡፡ ጋሼ መላኩ በንዴት

"አቶ ናደው አንጋደደው!" ብለው ጮሁበት፡፡ ሳያይ ረግጧቸው የቀደማቸው አንካሳ ሰማእት መሳይ ሳይሰማቸው አለፈ፡፡ "ስንት ጉድ አለ አናንተ! ኧረ አሳልፉን ያመናል፣ ፀልየናል፣ መፅውተናል!" እያሉ እያጉረመረሙ፤ እየተጓሸሙ፣ ትልቁ በር ደረሱ ጋሼ መላኩ

መዝገብ አንባቢዎች አትገባም አሉዋቸው

"ምነዋ?"

"ልጅህ ረግሞሀል"

"ምናባቱ ቆርጦት?"

"እንጃባቱን!"

"እኮ ቀስ አትሳደብ! ልጄ ዱዳ ነው፡፡ ምን ብሎ ረገመኝ?"

"መሬት አትቀበልህ! ፈጣሪ አይማርህ! ብሎ"

"ዱዳ ነው እያልኳችሁ!"

"እናውቃለን ዱዳ ነው፡፡ ደንቆሮም ነው"

"እኮ 'ንዴት አባቱን ብሎ ረገመኝ?"

"እሱ አዝኖ አለቀሰ፡፡ አዋቂዎች ሀዘን ለቅሶውን ወደ ቋንቋ ተረጉሙት፡፡ መልአክ በመዝገብ አሰፈረው"

"ሀሰት"

"ሀሰት? ይህ ደፋር!"

"ያዘው! ጣለው!" ተባባሉና፣ ይዘው ከገደሉ አፋፍ ወደ ገሃነም ቢወረውሩዋቸው፣ ጋሼ መላኩ "ኡ ኡ ኡ!" እያሉ እየጮሁ ሲወድቁ፣ ሲወድቁ፣ ሲወድቁ... ብንን ብለው ነቁ አቶ ወንዳፍራሽ፣ እኚህ ፍራሽ አዳሽ

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ እክህደከ ሰይጣን!" አሉ አቶ ወንዳፍራሽ፣ እያማተቡ በሌሊቱ

በውድቅቱ። እንደተጋደሙ ስለዚህ ህልም እያሰቡ ረጅም ጊዜ ቆዩ። ወንድማቸው ጋሼ መላኩ ከሞቱ ሰባት አመት አልፏቸዋል። ዛሬ መምጣታቸው ምን ይባላል? ደሞስ የምን ዱዳ ልጅ ነው እሱ?

ጋሼ መላኩ አልወሰዱ። ምን ማለት ይሆን?

እንዲህ እያሰላሰሉ ቀስ በቀስ እንቅልፍ ወሰዳቸው.... ሌላ ህልም አዩ

ጋሼ መላኩ ባህታዊ ሆነው፣ ከስተው መንምነው አጥንት ብቻ ቀርተው፣ በዘንጋቸው ወደ ዋሻቸው በኩል እየጠቆሙ "ና ልንገርህ፣ ወንዳፍራሽ" አሉዋቸው

አቶ ወንዳፍራሽ ፈርተው "እምቢ" ሲሉ ፈሰጉ። ጋሼ መላኩ እየጐተቱ ወደ ዋሻው አስገቡዋቸው።

እንደገቡ አሁንም የአሮጊት ድምፅ "ስማ አንተ ሰው፣ ስማ፣ ወደ ኋላ ስማ" አላቸው "ፈጣሪም ሴት ልጁን ሕይወትን ለሞት ዳረለት። ሞትም ሰይጣንን ሚዜ ሁነኝ አለው..."

እርጅና ጨምዳዳ አፉን እያጣመመ ወደ አቶ ወንዳፍራሽ በኩል ሲመጣባቸው ሲሸሹ ዘወር ቢሉ፣ ጋሼ መላኩ የዋሻውን በር በትልቅ ድንጋይ ድፍን ሲያረጉባቸው፣ እርጅና ሲይዛቸው እጁን ሰደድ አርጐ አፈፍ ሊያረጋቸው ሲል... ብንን አሉ አሁንም ከእንቅልፋቸው

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አክህደክ ሰይጣን!" አቶ ወንዳፍራሽ ሌላ ህልም እንዳያዩ ፈሩ።

ተነስተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ከቅዳሴ በኋላ ወደ ቤታቸው ሲያዘግሙ፣ ድንገት ድንግጥ አሉ፣ ስሰሰሙት ያንን

ያሮጊት ድምፅ፣ በህልማቸው 'አንተ ሰው ተመልከት! አንተ ሰው ስማ' ያላቸውን

የጀመሩትን እርምጃ ሳይጨርሱ መሀል ቤት ድርቅ ብለው ቀሩ

ያ ያሮጊት ድምፅ በዝግታ በቀስታ እንዲህ ይላል "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ፣ እውር አሞራን የምትመግብ አምላክ፣ ዮናስን በአሳ ሆድ ያኖርክ የጠበቅክ አምላክ፣ እኔንስ አለሁ አትለኝም ወይ? ምሳዬን አትጥልልኝም ወይ?"

አቶ ወንዳፍራሽ በፍርሃት እየተርበተበቱ ወደ ድምፁ በኩል ዘወር አሉ:: ከስልክ እንጨት ስር አንዲት አሮጊት ቁጭ ብለው ይለምናሉ:: እውር ናቸው:: የአላፊ አግዳሚውን ኮቴ ሲሰሙ "ስለማርያም ስለመብርሃን!" ይላሉ ጮክ ብለው

አቶ ወንዳፍራሽ ቀስ ብለው ከመንገድ ወጥተው አሮጊቷ አጠገብ ቆሙ:: አላፊ ሳይኖር አሮጊቷ እንደገና ፈጣሪን በዝግታ ሲያነጋግሩት ይቆዩና፣ የሰው እግር ሲሰሙ ጮክ ብለው "ስለመብርሃን ጣድቃኖቼ! ማርያም አለሁ ትበላችሁ! እምዮቼ ስለአዛኚቷ!" ይላሉ::

ሰው በማያልፍበት ጊዜ ደግሞ ፈጣሪን እንዲህ ይሉታል "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ፣ እውር አሞራን መጋቢ፣ ጫጩትን እንቁላል ውስጥ ያስፈረክ፣ እኔንስ ረሳኸኝ ወይ? ስጠራህ አለሁ አትለኝም ወይ? አቤት ባይ፣ ስጠኝ ባይ በዛብህ ወይ?

"ስለ ማርያም! ማርያም ትለመናችሁ ጣድቃኖቼ!" ሲሉ አቶ ወንዳፍራሽ ኪሳቸው ገቡና መጀመሪያ እጃቸው የያዛትን ፍራንክ አወጡ - ስሙኒ

"እንኩ 'ማማ"

ደንገጥ አሉ አሮጊቷ፡፡ የተዘከራቸው ሰው አብሯቸው የቆመ መሆኑ ተሰማቸው፡፡ እጃቸው ስሙኒውን አወቀው፡፡ ዝም ብለው ቆዩ ቆዩና

"ማን ነህ?" አሉ በለስላሳ ድምፃቸው፡፡ ዝም አሉ አቶ ወንዳፍራሽ

"ማን ነህ 'እንኩ 'ማማ' ብለህ ስሙኒ የሰጠኸኝ?"

"እኔ ነኝ፤ ቆሜ ስሰማዎት ነበር"

"ሰማኸኝ?... እህ" አሉ ለብቻቸው እንደሚያስላስሉ አይነት፡፡

"እንዴት ነው እዚህ የደረሱት?" አሉ አቶ ወንዳፍራሽ፤ አሮጊቷ አጠገብ ድንጋይ ላይ እየተቀመጡ፡፡ የጧት ፀሀይ ደስ ትላለች

"አዩ ልጄ! የኔማ ታሪክ እንደ ተረት ነው"

"ይንገሩኝ 'ስቲ"

"ይኸውልህ፣ ሰባት ወለድኩና ሰባቱም ሞቱ፡፡ ስምንተኛ እንደወለድኩ አዋቂ ቤት ሄድኩ፡፡ አዲሳባ 'ሚሉት አገር ሂጂ፣ እዚያ ሞት የለም፣ አሉኝ፡፡ አንድ ቀን ሳልውል፣ ስንቄን ጨርቄን ሳልል ተነሳሁና ወደ አዲሳባ መንገዴን አቀናሁ፡፡ ሞት እንዳይደርስብኝ፣ ልጄን እንዳይወስድብኝ፣ ስሄድ ሰንብቼ ስሄድ ከርሜ፣ ምግቤንም መጠጊያዬንም እየለመንኩ ስሄድ ከርሜ፣ ሰኔ ሚካኤል ካገሬ የወጣሁ ለህዳር ተክለሃይማኖት አዲሳባ ገባሁ፡፡"

"እንደተባለውም አዲሳባ ሞት የሌለበት አገር ሆነና፣ ልጄ አደገልኝ፡፡ እንጨት ከጫካ እየለቀምኩ፣ ጠላ ከገብስ እየጠመቅኩ፣

እንጀራ በጉልት እየሸጥኩ አሳደግኩት። ሰው ሆነ። ለሰው ወግ ደረሰ፤ ሚስት አገባ"

"ከዚያስ?"

"ዋ ልጄ! ከዚያማ ሚስት ሳትፈልገኝ ቀረች። ከንግዲህ ምን ልረባ? ለራሴ አሮጊት! ቤት ከማጣበብ፣ እንጀራ ከመፍጀት አልፌ ምን ልጠቅማት? አልፈጭላት፣ አልጋግርላት። አንድ ወለደችና፣ ባል ልጁን መውደዱን እርግጠኛ ከሆነች በኋላ፣ እቺን አሮጊት ካላስወጣህልኝ ፍታኝ አለችው"

"እና አስወጣዎት?"

"እኔ ወጣሁለት 'ንጂ። ለምን ላስኩንነው? የልጅ ፍቅር አይደል አገሬን፣ ጉረቤቴን ጥዬ እንድኮበልል ያደረገኝ? እሱንም የልጅ ፍቅር እናቱን እንዲያባርር ያረገዋል እልኩና፣ የገዛ እናቱ ሀጢአት ኩነኔ ከምሆንበት ብዬ፣ ወጥቼ ጠፋሁ"

ልጃቸውን ሞት እንዳይበላው ካገራቸው ከወንዛቸው ኮበለሉ፣ ገሃነም እንዳይበላው ደሞ ከልጃቸው ከራሱ ኮበለሉ "እውነትም የናት ፍቅር" ብለው አሰቡ አቶ ወንዳፍራሽ

"ታድያ ፈጣሪዬ ጥሎ አልጣለኝም" አሉ አሮጊትዋ "እሷ መሰላት 'ንጂ፣ እኔስ ይኸው የሱን ፀሀይ እሞቃለሁ፤ ይኸው ከሰው ጋርም እጫወታለሁ"

ዝም ብለው ጥቂት ጊዜ አለፈ። አቶ ወንዳፍራሽ በዝግታ ድምፅ "ኤሲን ድንጋይ ያለበስክ አሉ፣ ከዚያ ምን ነበር?"

"እውር አሞራን መጋቢ፣ እንኮይን በገደል የተከልክ፣ ደመናን እንደ ጥጥ ሰብሳቢ፣ ረሳኸኝ ወይ? እለዋለሁ። አቤቱታ በዛበት፣ የሚጠራው፣ የሚለምነው በዛ። እሱስ ምን ያርግ ብለህ

ነው? ስንቱን ይስማ? ግን ይቆይ ይቆይና አስሁ ይለኛል። አይዞሽ ይለኛል፣ ረስቶ አይረሳኝም"

"እንደዚህ 'ንደ አሁኑ ይሰጠኛል። ባንተ እጅ ሆነ 'ንጂ ስጪው እሱ ራሱ ነው። ማደርያም ሰጥቶኛል። አንድ አረብ አለ፣ እርጅናዬንና የሰው አገር ሰው መሆኔን አይቶ መጠጊያ ሰጥቶኛል። የሰፈሩ ሴቶች ደም ቡና ያጠጡኛል፣ የሚቀመስ ይሰጡኛል። እሱው ይመስገን፣ የጐደለኝ የለም። መሪ 'ንኳ ሳይቀር ሰጥቶኛል። እዚህ ሰፈር ተረኛ የሆኑ ሁለት ፖሊሶች እሱ ቧት ወደዚህ ወደ ልመናዬ መርተው ያመጡኛል። እሱ አልተወኝም። ይኸውልህ፣ እንዲያው አንዳንዴ ብቸኝነት ሲሰማኝ አነጋግረዋለሁ 'ንጂ፣ በደምብ ይጠረኛል። ምስጋና ይግባው። ዛሬ ደሞ ከሰው ጋር መጫወት እንዳማረኝ አይቶ ይኸው አንተን ላከልኝ። እንደዚህ ነው የሱ ነገር"

አቶ ወንዳፍራሽ ካሮጊትዋ ጋር ሲጫወቱ አርፍደው ወደ ቤታቸው ሲያዘግሙ፣ አንድ መልስ የሌለው ጥያቄ እየተመላለሰ መጣባቸው። አሮጊትዋን ዛሬ ጧት ሲያገኙ፣ የአሮጊትዋን ድምጽ በትላንት ማታ ህልም መስማታቸው ምን ማለት ይሆን?

@amharicbooks24 click here

@amharicbooks24 ይሄን ይጫኑ

መጽሐፍት

የተመረጡ አማርኛ ና እንግሊዝኛ
መጽሐፍትን ,ትረካዎችን,ወጎች ያገኛሉ
...

# ቦርጨቅ!

አቶ ዘነበ ሀብትም ሆነ ሹመት ወይም ዝና በምኞታቸው ገብቶ አያውቅም ነበር:: አግብቶ፣ ልጆች ወልዶ አሳድጎ፣ አስተምሮ፣ በስተርጅና ጧሪ ደጋፊ ማግኘት፣ በልጆችና በልጅ ልጆች ተከበ መድሀኔአለምን ተመስገን እያሉ መሞት:: ይኸ ነበር ያቶ ዘነበ ምኞትና ተስፋ::

ግን እግዜር ሳይለው ቀረና፣ ባንድ መስሪያ ቤት የቢሮ ተላላኪነት ተቀጥረው፣ ካመት አመት ሚስት አገኛለሁ እያሉ ተስፋ ሲያደርጉ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ካመት አመት ሳይሳካላቸው ሲቀር፣ ካመት አመት ጊዜ ትከሻቸው ላይ እድሜ ሲቆልል፣ እድሜው እየከበዳቸው እየጎበጡ ሄዱ:: ተስፋቸው ከወጣትነታቸው እኩል እየመነመነ ሲሄድ፣ መድሀኔአለምን እየተሳለሙ "አንተ አምላክ ሳላውቅ በድዬህ ይሆን? ማረኝ ይቅር

በለኝ እያሉ በልባቸው ሲለምኑ፣ ሲፆሙ ሲፀልዩ ሲሰግዱ፣ እንዲህ ሲሉ ስድሳ አመት ሲሆናቸው ተስፋ ቆረጡ። ያ ሲያስጎመጃቸው፣ ሲያስጨንቃቸው የነበረ ተስፋ ጥሎአቸው ሲሄድ ጊዜ ቀለል አላቸውና ልባቸው አረፈ። መድህኔአለምን እየተሳለሙ "አንተ ታውቃለህ እንጂ እኔ ምን አውቃለሁ? አንተ እንዳልከው ይሁን" ብለው እድላቸውን በሙሉ ልባቸው ተቀበሉ።

በዚያን ሰሞን አንድ ጨካኝ ባለጌ አለቃ ተሾመባቸውና እያመናጨቀ፣ ክብራቸውን እየነሳ ያስጨንቃቸው ጀመር። "ወንድ ልጅ ወልጄ ቢሆን ኖሮ በስተእርጅናዬ ሰው እንደዚህ ይጫወትብኝ ነበር?" ብለው "አንተ ከንቱ የተሰበረውን ወፍ የምትጠብቅ የምትጠግን አምላክ፣ ለደከመ መንገደኛ የዛፍ ጥላ የምትሰጥ አምላክ፣ ለኔስ ብስተርጅናዬ ሰላም አትሰጠኝም?" አሉት።

ሁለት አመት ያህል እንዲህ ከተበሳጩ በኋላ፣ ያ ጥላ-ቢስ አለቃቸው ወደ ሌላ ተዛወረና አንድ ወጣት አለቃ ተሾመላቸው። እሱም አቶ ዘነበን በጨዋ ደንብ ክብራቸውን ጠብቆ ከማዘዙም በላይ፣ በስራው እሳት ስለነበረ በጣም ያደንቁት ጀመር። ልባቸው እንዳረጀ ወፍ ብር ብሎ ሄዶ "መድህኔአለም ባይለው ነው እንጂ ይህን የመሰለ ሳተና ሊሰጠኝ ይችል ነበር" የሚል ሀሳብ ላይ ያርፍ ጀመር።

እንዴት እንደሆነ ሳይታወቃቸው በአለቃቸው ኩራት እያደረባቸው፣ ቀስ በቀስ እንደ ልጃቸው ሲወዱት ይሰማቸው ነበር። አንዳንዴማ ከሌሎቹ የመስሪያ ቤቱ ተላላኪዎች ጋር ሲያወሩ "የኔ አለቃ ዘንድ የተመራ ዶሴ ፍፃሜውን ሳያገኝ ያድራል ማለት ዘበት ነው" እያሉ መፎከር አመጡ። ልባቸው አለቃቸውን እየወደደ በሄደ መጠን ፍርሀት እየተሞላ ሄደ። ይኸ ነው የማይባል፣ መነሻው የማይታወቅ ፍርሀት። መድህኔአለምን

እየተሳለሙ በልባቸው "አንተ አምላክ፣ የልቡን ደግነት እያየህ ጠብቀው" ይሉ ነበር።

ታዲያ አንድ ሰሞን ይህ አለቃቸው ስራውን እንደ ድሮው ማቀላጠፍ ትቶ፣ ከቢሮው አስር ጊዜ እየወጣ አስር ጊዜ ይመለስ ጀመር። የስራ ሰአት አሳልፎ የመምጣት በሽታ ተጋባበት፣ አልፎ አልፎም ጺሙን ሳይላጭ መግባት አመጣ። አንድ ወር ያህል ሌላ ሰው ሆኖ ትልቁ ጠረጴዛው ላይ በሃምሳ የሚገመት ዶሴ ተወዘፈ።

የመድሀኔአለም እለት አቶ ዘነበ ወደ ቤተስኪያን ሄደው እየተሳለሙ በልባቸው "እንካሳ እድሌን እዚህ ልጅ ላይ አጋብቼበት ይሆን? አታረገውም አንተ መድሀኔአለም! ይህንንስ አታረገውም" አሉ። በነጋታው ጧት ወደ አምስት ሰአት ላይ አለቃቸው አይኑ ቀልቶ ፀጉሩ ተንጨፍርሮ ያስር አመት ስካራም መስሎ መጣና እጅ ሲነሱት እንዴት አደሩ እንኳ ሳይላቸው ወንበሩ ላይ ዘጭ አለ። ራሱን ዴስኩ ላይ ደፋ። አቶ ዘነበ ተጨነቁለት። ግን አለቃቸውን መድፈር ስላልፈለጉ፣ እና ቢደፍሩትም ልባቸው ውስጥ ያለውን ሽብር ለሱ መናገር የማይቻላቸው ስለሆነ፣

"ጫማዎን ለሊስትሮ ልስጠው?" አሉት

"እ?" ብሎ ደንግጦ ከዴስኩ ቀና ብሎ አያቸውና «እርስዎ ነዎት 'ንዶ?» አላቸው።

"እኔው ነኝ ጌታዬ። ምን ላድርግልህ?" አሉት፣ አንተ ማለታቸው ሳይታወቃቸው። ተስፋ የራቀው የፈገግታ መልክ እያሳያቸው፣

"ቤተክርስቲያን ይስማሉ?" አላቸው።

"አዎን"

"ማንን?"

"መድሀኔአለምን"

"እንግዲያውስ ለመድሀኔአለም ያስታውሱኝ"

"ሁልጊዜ ነው 'ማስታውስህ"

"ምን አሉኝ?"

"በፀሎቴ ሁል ጊዜ አስታውስሀለሁ"

ቶሎ መልሶ ራሱን ደፋ:: ሲያዩት ትከሻው ይንቀጠቀጥ ጀመር:: ከዚያ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ::

አቶ ዘነበ የሚጨብጡትን የሚቆሙበትን ስላጡ "እረ ጌታዬ አታልቅስብኝ! ምን በወጣህ ታለቅሳለህ? ይቅር ተወው ይቅር:: በቃ ተወው ይቅር:: ተወው በቃ" እያሉ አለቃቸውን ሳይሆን በልባቸው ያለውን ልጃቸውን ያባብሉት ጀመር::

ለቅሶው ፋታ ሲሰጠው አለቃቸው ቀና ብሎ፣

"ቤተሰብ አለዎት?" አላቸው::

"ብቻዬን ነኝ"

"እኔም ብቻዬን ነኝ:: አይገርምዎትም?"

መልስ አላገኙለትም::

"መጣሁ" አላቸውና እየተጣደፈ ወጣ:: አቶ ዘነበ ግራ ገብቶአቸው ሲጨነቁለት ሲቁነጠነጡ ደጋግመው ወደ ላይ እያዩ "አንተ መድሀኔአለም ምን ማድረግ ይሻለኛል?" ሲሉ ብዙ ከቆዩ በኋላ አለቃቸው በሩን በርግዶ ገባና ቁልፎት ሲያበቃ

"እነሆ" አሏቸው በላስቲክ የታሰረ ገንዘብ።

ተቀበሉት ሲልካቸው መስሎአቸው። "አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር ናት። ትንሽ ቦታ ተመርተው ትንሽ ቤት ይስሩባት። ሲያረጁ ማረፊያ ትሆንዎታለች። እና ለመድህኔአለም ያስታው ሉኛል"

አቶ ዘነበ ከመደንገጣቸውና ከመገረማቸው የተነሳ አልተናገሩም። አልተንቀሳቀሱም።

አለቃቸው እንደገና በሩን በርግዶ ወጥቶ ብዙ ቆየ። ካሁን ካሁን ይመለሳል ብለው ሲጠብቁ ሰባት ሰአት ሆነና፣ ቢሮውን ቆላልፈው ገንዘቡን ይዘው ቤታቸው ሄዱ።

በዘጠኝ ቢሮውን ከፍተው ዶስኩን ወልውለው፣ የተቆለሉትን ዶሴዎች አይተው ራሳቸውን በሀዘን ነቅንቀው፣ ዝናብ መትቶአቸው ስለነበረ ፀሀይ ሊሞቁ ወጡ። ወደ አስራ አንድ ሰአት ላይ ወሬው ደረሳቸው። አለቃቸው መኪናውን ጭቃ አዳልጦአት ገደል ገብቶ ሞተ።

በልባቸው ውስጥ፣ ከጥልቀቱ የተነሳ ማንም ሊሰማው ወይም ሊጠረጥረው የማይችለው ጥልቀት ውስጥ "ልጄን! ልጄን! ልጄን!" ብለው አለቀሱ።

ጠዋት ተነስተው ለቀብሩ ሲሄዱ ድንገት የልብሳቸው መናኛነት ታያቸውና "እንዴት አለቃዬን በመናኛ ልብስ እሸኝ ዋለሁ?" ብለው በፍጥነት ተመልሰው ከሃያ አመት በፊት ያሰፋዋትን የክት ገበርዲን ልብሳቸውን ከሳጥናቸው አውጥተው ከጎረቤት ካውያ ለምነው ተኩሰው፣ ወጣ ብለው ከሱቅ አዲስ ሸሚዝ ገዝተው፣ በሚገባ አጊጠው ወጡ። ሊቀብሩ ሳይሆን ሊሰናበቱ።

ጊዜም እንዳያልፍባቸው፣ ለጊዜው አባርቶ የነበረው ዝናብም እንዳይደርስባቸው በታክሲ ለመሄድ ቆረጡ:: ሁለት ታክሲ ሞልቶ አልፎአቸው ሶስተኛውን ሲጠብቁ፣ አንዲት ፈጣን ቆንጆ መኪና እንደ ወንዝ እየፈሰሰች መጣችና—— ቦርጨቅ! አለፈች::

ውሀው ከመንገዱ ተወርውሮ ተለጠፈባቸው:: ገበርዲና ቸውን ጭምልቅልቅ አደረገባቸው:: የተቆረጠውን ትንፋሻቸውን ገና ሳይቀጥሉትና መተንፈስ ሳይጀምሩ፣ ከርካሳ መኪና ስትንገጫገጭ መጥታ—— ቦርጨቅ! ደገመቻቸው:: አለፈች::

"ገበርዲኔን! አዲስ ሸሚዜን! አለቃዬን!" እያሉ እየጮሁ ጎምበስ ቢሉ ድንጋይ አጡ::

"አንዲት ድንጋይ እንኳ ብትሰጡኝ ምን ቸገራችሁ ነበር? አንዲት ድንጋይ፣ ገበርዲኔን የምበቀልባት?" እያሉ እያስቀሱ፣ በእግር መንገዳቸውን ቀጠሉ:: ትንሽ ቆይተው "ገበርዲን ጊዜው አልፏል:: ቆሻሻ ውሀ ካልደረቡበት አያምርም ተብሏል" እያሉ፣ ሌላም ልዩ ልዩ ንግግር እየተናገሩ፣ ሊወርድባቸው የጀመረውን ሃይለኛ ዝናብ ሳያስተውሉ ቤተክርስቲያን ደረሱ::

አለቃቸው ሲቀበር እየሳቁ ለብቻቸው ያጉረመርሙ ነበር "ማዘን አያሻም:: እሱ መች ሞቶ መሰላችሁ? ተሻግሮ ነው:: እዚያ እንግዲህ የወርቅ ቢሮ ይሰጡታል:: በል እንደ ልማድህ ስራውን አቀላጥፍልን! ይሉታል:: የሚረባ ተላላኪ ካልተመደበልኝ ልሰራ አልችልም! ሲላቸው፣ ምረጥ ይሉታል:: ዘነበን ስጡኝ ሲላቸው፣ እዚያኛው አለም ነው ይሉታል:: ላኩበት ይላቸዋል! አለቃህ ይፈልግሀል፣ ልጅህ ልኮብሀል በሉት::"

አቶ ዘነበ የብርድ በሽታ ያዛቸውና እያተኩሳቸው እያንቀጠቀጣቸው በሶስተኛው ቀን አረፉ::

# ወደ ጠጅ ቤት

## ክፍል አንድ

ውብ የሆኑ የተነቀሱ ሴትዮ፣ አይናቸው የፈራ፤ ጥርሳቸው የጠራ፤ እግራቸው አንካሳ፣ በብዙ ልዩ ልዩ ምሳሌ የሚናገሩ፣ እመት አበሻነሽ የሚባሉ፣ አባ ቀጥቅጥ ሰፈር “ልጠጣ ልደሰት” የሚሰኝ ጠጅ ቤት እየመሸ፦ ይኖራሉ፣ ምን አንካሳ ቢሆን የሰው ልጅ መታገሉን ጠጅ መጣሉን አይተውምና

የመት አበሻነሽን ጠጅ እንኳን ሀበሻ ፈረንጅ እያንዶቀዶቀ ይጠጣዋል። የመት አበሻነሽን ጠጅ ያስወደደው ጥራቱና ንፅህናው ብቻ ሳይሆን፣ ከመት አበሻነሽ ከናፍር የሚፈልቁት ምሳሌዎች ጭምር ናቸው። ሲባል ሰማን 'ንጂ እኛ እንኳን የእመት አበሻነሽን ጠጅ እስከ ዛሬ አልቀመስነውም

"ማን ይመሰክራል የሰማ፣ ማን ያፍራል ያማ" እንዲሉ አክስቶች

የሆነ ሆኖ፣ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ በእርግጥ የእሁድን እረፍት ስለሚያስከትል፣ አቶ ብርሃነ በትንሽ መኪናቸው ከጓደኛቸው ከአቶ ጥላሁን ጋር ወደ እመት አበሻነሽ ጠጅ ቤት ሲሄዱ፣ እመንገድ ዳር የቆሙ ሶስት ሰዎች በእጃቸውና በገፃቸው የማሳዘን "እምጵፅ!" ምልክት እያሳዩ፣ አንገታቸውን እየቀለሱ "ሊፍት" ቢለምኗቸው፣ አቶ ብርሃነ ኮስተር ብለው ሰውነታቸውን ነፋ አድርገው፣ ጀግና አትንኩኝ ባይ ፈረሰኛ መስለው አለፉ

"ሊፍት?!" አሉ በመገረም "የምን ሊፍት? ፈረንጅ መሰልናቸው?"

"ሀበሾችን አምነን ሊፍት የምንሰጥ?" ብለው አሟሉ አቶ ጥላሁን "ወይስ የስምንተኛው ሺ አብረሀምን ለምሳ አዝለህ ውሰደን የሚሉ ስላሴዎች የሆኑ መሰላቸው'ንዴ ምናልባት?"

"እፍረት የለንም መሰላቸው?" ሲሉ ጠየቁት አቶ ብርሃነ መላውን ፍጥረት

"አፍሬ ልሞት! ጥፍሬ ገባሁ! ይላሉ ወፍራሟ እመት አያህሉሽ" አሉ አቶ ጥላሁን፣ ኑሮን በምሳሌ እያስጌጡ፣ ምሳሌን በኑሮ እያደሱ፣ በመኪና እየተጓዙ

"አብረሀምን ብትጠራ ግመሉ መጣ" አሉ አቶ ብርሃነ "ግመል በፅድቅ ብዛት በመርፌ ቀዳዳ ማለፍ ባትችልም ወፍራም ሴት በእፍረት ብዛት እጥፍሯ መግባት ትችላለችና"

አቶ ጥላሁን "ሀበሻ ከሆነች" አሉ፣ የሃገራቸውን ልጆች ከነብሳቸው እኩል ይወዱ ስለነበረ

አቶ ብርሃነም ልባቸው በሃገር ፍቅር እያበጠ "እንዴታ! ኧረ እመት አበሻነሽ ራሳቸውም ሳይችሉ አይቀሩም" አሉ

"እሱማ የታወቀ የደቀቀ ነው። ያን የመሰለ ጠጅ ከጣሉ በመርፌ ቀዳዳ ማለፍ ምን ያቅታቸዋል?"

"እህሳ! ላይኛው አገር ጠጅ ይጥላሉ ብለህ?" አሉ አቶ ብርሃነ

ከጎን መንገድ መጥቶ ሊገባ ይቃጣ የነበረውን አዲስ ረጅም ሰፊ ሽንጣም ቆንጆ የባለፀጋ መኪና፣ አቶ ብርሃነ ቀጭን ጡሩምባቸውን በሀይለ ቃል ነፍተውበት አቁመውት እያለፉት

"የኛ ተራ ነው" አሉ

"በስርአት ይንዱ" ሲሉ ቀጠሉ አቶ ጥላሁን

"አሊያም በህግ ይጠየቁበታል" ሲሉ ጨመሩ ከሳሽ አቶ ብርሃነ

"ህግ በርስዎም ላይ ቢሆን ስልጣን አለውና" አሉ መምህር ጥላሁን

ደጃዝማች ብርሃነ "ልለፍበት ብያለሁ ጌታዬ፣ በሀብትም አይመኩ" ሲሉ አስጠነቀቁ

"ነገ ማን ሀብታም እንደሚሆን አይታወቅም። ቢያስቡበት ይሻላል" ሲል አስታወሰ ነቢዩ ጥላሁን፣ የነገ ምስጢረኛ በመሆኑ

"ብልፅግና አንድም ከዳተኛ፣ አንድም ወረተኛ፣ አንድም ሽርሙጣ መሆንዋን መዘንጋት ከሞኝነት ያስቆጥራል" ብለው አስፈራሩ ሊቀ ሊቃውንት አባ ብርሃን ፀጋ

ፋኖው ጥላሁን "ዋ!" ብሎ አስፈራራ

"ቂል ካፒታሊስት! እንደ ሌላ ሰው መስለነው መብታችንን ሊገፈን:: እኛ እንደሆንን አንገፋም:: እንኳን ካፒታሊስት ፋሺስት አልገፋንም:: ብርሃኑና ጥላሁን መሆናችንን ማን በነገረው!?"

"ይኸው ቀመሳታ! ሁሉም ይገፋልኛል መስሎታል!"

ሁለቱ ጓደኞች በዚህ አኳኋን በመተባበር ግፈኛውን ካፒታሊስት ልክ ልኩን ነግረውት ልክ አግብተውት ሲያበቁ፣ መንገዳቸውን ቀጠሉ

አቶ ብርሃኑ "ላይኛው መንግስት ካፒታሊስት ይገኝ ይሆን?" አሉ

"ምን አባቴን አውቄ ብለህ?"

"አታውቅም? እንግዲያው እኔም አላውቅም:: በል ምን ትሆን?"

"እኔማ ምን እሆናለሁ? ላንተ ይብላኝ 'ንጂ"

"እያ ጅበ፣ ሳታማህኝ ብላኝ፣ አሉ እመት አበሻነሽ"

"እይ እመት አበሻነሽ! አሁን እሳቸው 'ሚጥሉትን ጠጅ ማን ጥሎት ያውቃል?"

"ገረዶቻቸው!"

"እ! አውቀሃል! እንዲያውስ እሳቸው ራሳቸው ጠጅ ይጥላሉ ብለህ?"

"ምን አባቴን አውቄ?"

"አታውቅም?"

"አላውቅም"

"ቆይ፣ አሁን ውስጥ እግርህን ሲገርፉህ ይገለጽልሃል። ቷ! ተናገር"

"ኧረ እኔ አላውቅም"

"ቷ! ተናገር"

"እሺ ልናገር"

"ቷ! እመት አበሻነሽ ጠጅ ይጥላሉ ወይስ አይጥሉም?"

"ይጥላሉ - ይጥላሉ - ይጥላሉ!"

"ቷ! መጣላቸውን እንዴት አባክ አወቅክ?"

"ቷ! ባፍንጫዬ አየሁዋቸው"

"አንተ'ኮ ትገረፋለህ'ንጂ አትገርፍም። ለምን ቷ ትላለህ?"

"ስፈልግስ? ሲያምረኝስ? ሲያስፕኝስ?"

## ክፍል ሁለት

እንዲህ እየተጫወቱ ጥቂት እንደሄዱ፣ አቶ ጥላሁን መስተዋቱን ዝቅ አድርገው "እክ!" ብለው ወደኋላ 'ሚጎርፈው አስፋልት ላይ ለጠፉበት

"ይኸ ጉሮሮዬ አስቸገረኝ" ሲሉ ይቅርታ ጠየቁ

አቶ ብርሃነም "አይዞህ! አንድ ሁለት ብርሌ ሲያጥበው ልክ ይመጣል" ብለው አፅናኑዋቸው

አቶ ጥላሁን "ክትፎ በሚጥሚጣ ሲጨመርበትማ!" ብለው አሻሻሉትና፣ ወዲያው አከታትለው "የሀረገወይን ፈገግታ ሲታከልበት ደግሞ!" በማለት አበለጡት

አቶ ብርሃነ ፍፁም ሲያደርጉት "እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ፣ ሀረገወይንም ፈገግ አለች" አሉ

"መናፍቅ! አርዮስ! እክህደክ! ገዝቼሃለሁ!" አሉ አባ ጥላሁን በመንፈሳዊ ተግሳፅ "መጭ በላት ይልቅ ፈረሲቱን"

"የሀረገወይን ፈገግታ ከሩቅ እያንፀባረቀ ጠራህ?" አሉ አቶ ብርሃነ መኪናቸውን እያፈጠኑ "እይ አንተ! በስተርጅናም ኮረዳ ያሮጥሃል!"

"በስተርጅና? ጉሮሮዬ የሻከረ 'ንደሆነ አረጀሁ ማለት ነው?"

"ስድሳው አመትስ?"

"ስድሳ አመት? ምን መሰለህ ስድሳ አመት? አያቴ በሰማንያ አምስት አመታቸው ሴት አታመልጣቸውም ነበር። ገና በዘጠና አመቴ ሳሳድድ ታየኛለህ፣ እኔ ወንድምህ!" ሲሉ መጪውን ጊዜ በአጉቦ ለመኑት እንዳይቀንሳቸው።

"መቼ አጣሁት እባክህ? ስቀልድ ነው 'ንጂ" ሲሉ አቶ ብርሃነ ጓደኛቸውን፣ በዚያውም ራሳቸውን አፅናኑ "ድሮውንስ ልብ ነው 'ንጂ መች አመት ነው?"

"ወኔ ነው 'ንጂ!"

"ሀሞት ነው!"

ቀዩን መብራት አይተው ፍጥነት ሲቀንሱ፣ ድንገት ካጠገባቸው ብቅ ያለውን ሰይቼንቶ "ቶሽ!" አሉት አቶ ብርሃነ

"አሳርፍ ያለች ጣት አትሁንብን ጎሽ" አሉት አቶ ጥላሁን

"አንተ ስሙኒ ብታሳድድ እኛ ደግሞ 'ምናሳድደውን እናውቃለን"

"እንዴታ! ከጠጅና ከስሙኒ?"

"ከሀረገወይን አይንና ከትራፊክ አይን?"

"ኧረ የትና የት?! ማንም የጨዋ ልጅ 'ሚያውቀውን!"

ሰይቼንቶው ውስጥ የሀበሻ ልብስ የለበሱ ቀጭን ጠይም ሞጋጋ ሴትዮ፣ ትልልቅ መጥረቢያ ጥርሳቸውን እየፋቁ፣ ጎሪጥ አይናቸውን ወደነ አቶ ጥላሁን አነጣጠሩባቸው

"ተበላሽህ ጥላሁን!" አሉ አቶ ብርሃነ

"ሊበላህ ነው ጭራቁ!" አለ ልጅ ጥላሁን

"ተው አይሆንም! ወኔየን ታስነሳብኛለህ" አለ ፋኖው ብርሃነ

"በኋላ ለወሬም አይመች" አሉ አቶ ጥላሁን

"ለወሬም አይመች ያንቺስ ነገርሽ፣ አለ ሰውየው! እንደ ሀረገወይን ያለች አጋጥማው'ኮ ነው"

"ተወኝ ብየሃለሁ የሷን ስም አታንሳብኝ፣ ሰይጣኔን ትቀሰቅስብኛለህ!"

ሰይጣን መቸም ሲጠሩት ከተፍ ባይ ነውና፣ ከመቅፀበት መጥቶ የአቶ ጥላሁንን ሃሳብ በከርካሳ ትሬንታ-ኳትሮ ጭኖ ወስዶ ሀረገወይን ጭን ላይ አራገፈላቸው፡፡ ሀሳባቸውም ስጋዋ እየሞቀው እየለሰለሰው እየተመቸው እየተፍታታ እየተዝናና ስለሄደ፣ ተመለስ ቢሉት አሻፈረኝ ብሎ እዚያው እንደተጋደመ ቀረ

አቶ ብርሃነ የትራፊክ መብራቱን አልፈው የትና የት ከሄዱ በኋላ፣ ከፊታቸው ድንገት እየሮጠ ያቋረጠውን ባላገር በቀጭን ጥሩምባቸው "አትሄድም ከዚህ!" ብለው ቀልቡን አሳጥተው ካስደነበሩት በኋላ፣ በልሳነ ሀበሻ "ክልፍልፍ የርጎ ዝንብ! ድሃ እናትህን ከምታሳዝን እይተህ አትሻገርም?" አሉት። ባይሰማቸውም ቅሉ፣ አቶ ብርሃነ ኅረቤታቸውን ገስፀዋል፣ ከጥፋት መንገድ እንዲመለስ መክረዋል፣ የክርስቲያን ተግባራቸውን ፈፅመዋል፣ ህሊናቸው አይወቅሳቸውም

አቶ ጥላሁን ዝምታቸውን ሲያዙት ጊዜ አቶ ብርሃነ አይናቸውን ጣል አደረጉባቸው። አቶ ጥላሁንም የወዳጃቸውን አይን ባያዩትም ስለሰሙት

"ምን አልከኝ?" አሏቸው በግማሽ ልብ

አቶ ብርሃነ በፈገግታ "ሀሳብህ ቀድሞን ደረሰ መሰለኝ" አሏቸው

"እህሳ!"

"ተወው አትጥራው፣ እዚያው ይቆየን፣ እንደርስበታለን" አሉ አቶ ብርሃነ

ከሀሳቦቻቸው ጋር እንጂ እርስ በርሳቸው ሳይነጋገሩ ከተማውን አልፈው፣ አባ ቀጥቅጥ ሰፈር፣ ዛፎች እንደ ቤተክርስቲያን አፀድ ከበው ያጠለሉት ደስ የሚል ስፍራ ደረሱ። ከመኪናቸው ሲወጡ የ"ልጠጣ ልደሰት" ግሩም ሽታ እስከ ውጪ ወጥቶ እየተቀበላቸው

"እንኳን ደህና መጣችሁ ጌቶቼ! ግቡ ግቡ! ቤት ለንግዳ!" አላቸው

"እንገባም እንቸኩላለን" አሉት አቶ ጥላሁን የጠጁን ሽታ

"እረ በማርያም ግቡ! ታስገድሉኛላችሁ። የሚቴን ቆጣንኳ እንደ ምንም በቻልኩት፣ ሀረገወይን ታዝንብኛለች። እረ ግቡ በስላሴ!" እያለ ከመኪናው ወደ በሩ ሲጎትታቸው

አቶ ብርሃነ "እሺ መጣን ቅደመን" አሉትና፣ ጓደኛቸውን ዝቅ ባለ ድምፅ "ሀረገወይን ስትወጣብህ እኔ ደግሞ እመት አበሸነሽን ልምክራቸው ላገላብጣቸው ይሆን?" አሉዋቸው

አቶ ጥላሁን "ሂ ሂ ሂ" ብለው እየሳቁ መልስ ሊሰጡ ሲሉ

"እሰ መፅሀፍ ትምህርት የያዘ ጠቃሚ ምክር ያዘለ ቁምነገር የተመረኮዘ!" አላቸው ወጣቱ ባለቆሻሻ ቆብ፣ ተማሪ የነበረ፣ ምናልባትም የማታ ትምህርት የሚማር

"እንገዛም"

"እናነብም" ብለው አፍ አፉን ካባረሩት በኋላ፣ አቶ ብርሃነ

"ሳልነግርህ!" አሏቸው

"ምን?"

"የሆንኩትን። ሽንታችንን እየሸናን ልንገርህ። ይኸውልህ፣ ከእለታት አንድ ቀን ከቢሮ ስመለስ፣ መቼም መንገድ አቃጣሪ አገናኝ ነውና ‹እናት ኢትዮጵያ› የሚል መፅሀፍ አይቼ

"እስቲ ቁጠርልኝ፣ እነማንን ወለደች? እያልኩ እያሽሟጠጥኩ ገዛሁትና ኪሴ ከተትኩት፣ እሱ ለሚነግረኝ ደግሞ የነሱ ገንዘብ ማትረፋቸው እየገረመኝ። ማታ ለብቻዬ መብራቱን አብርቼ ትራሴን አመቻችቼ ‹አሁን እኔና'ንተ ብቻችንን ነን። በላ ንገረኝ፣ እነማንን ወለደች?› አልኩት

"እሱም ‹ተራራ ሸንተረርዋ፣ የሶስት ሺህ አመት ክርስትናዋ› እያለ ለትንሽ እንደተንተባተበ፣ ስለቾኙና ‹በል ዝም በል አርፌ ልተኛበት› ብዬ መጣፉን አጥፌው መብራቱን አጥፍቼ ተኛሁ።

ታዲያ በሕልሜ "ሃገርህን ውደድ!" አሉኝ አንድ ትልቅ ሰው ካባ ለብሰው

"ለምን ብዬ ነው አገሬን መውደዬ?" ልላቸው ፈልጌ "ለምን - ለምን - ለምን" እያልኩ እየተንተባተብኩ ነቃሁ። የኑሮ ነገር እንዲህ ነውና፣ በውን ያመለጡት በህልም እየደረሰ"

## ክፍል ሶስት

እውጪው በር አጠገብ አጥሩ ላይ የተለጠፈ ነጭ ቆርቆሮ



ብሎ አስተዋወቃቸው

"ለኛ ነው 'ምትነግረን?" አሉት አቶ ብርሃን "ለናትዋ ምጥ አስተማረች። በል ይግባህ፣ እኔው ነኝ በዚች እጄ የፃፍኩህ"

"ተፅፏልና እንዲል መፅሀፉ" ሲሉ ቀጠሉ መምህር ብርሃን "ፅሁፍ ለልዩ ልዩ ምክንያት ይፃፋል። እንደምን ቢሉ፣ አንድም ለማሳወቅ፣ አንድም ለማስደነቅ፣ አንድም ለመሳለቅ፣ አንድም ለማሳቀቅ ይሷል

"ንህነሰ ኢንዕህፍ ለአድናቆት፣ ለሰቀቆት፣ ለአስህቆት፡፡ አላንፅህፍ ለማወቆት፣ ወለመፅደቆት!"

መምህር ብርሃነ ደቀመዝሙራቸውን ጥላሁንን እንደዚህ እያስተማሩት ወደ ቅፅር ግቢው ሲገቡ ሲሉ

"ታዲያስ ሎተሪ! እድል ጠሪ ድህነት አባራሪ

ነገ 'ሚወጣ አለ ሎተሪ!" አላቸው፣ ከሩቅ ከመቅደላ የሚጎሰመውን ያዔ ቴዎድሮስን ነጋሪት የመሰለ ወፍራም ድምፅ

አቶ ብርሃነና አቶ ጥላሁን እኩል "እንገዛም" እያሉ ዘወር ብለው ቢያዩት፣ ቁምጣና ጃኬት የለበሱ ባለሻኛ ሽማግሌ ናቸው፡፡ ረዣዥም ቀጫጭን ቅልጥማቸው ለጎን ወይም ባህር አጠገብ የሚኖር ወፍ አስመስሏቸዋል፡፡ በነጋሪት ድምፃቸው፡-

"አለ ዜሮ ቁጥር አሻሚ
ስድሳ ቁጥር አሸካሚ
ብልጥግና ሸላሚ!" አሉ

አቶ ጥላሁን "ተዉኝ አባቴ፣ ለሀብታም ሸጡት፣ ላለው ነውና 'ሚጨምርለት" አሉዋቸው

አቶ ብርሃነ ሽማግሌው ባዶ እጃቸውን መሆናቸውን ስላስተዋሉ

"ለመሆኑ የታለ ቲኬቱ?" አሉዋቸው

"ቲኬትስ አልያዝኩም" አሉ ባለሻኛው

"ታዲያ ምንድን ነው 'ሚሉን?" አሉዋቸው አቶ ጥላሁን

"እንዲያው ለነገሩ ማለቴ ነው 'ንጂ..." አሉና ማልቀስ ጀመሩ ሽማግሌው

"ምን ያስለቅሶታል?"

"አልቃሽ ከተገኘ 'ሚያስለቅስ መች ይጠፋል?"

"አይ! እንዲያው ምን ደረሰብዎት ማለቴ ነው 'ንጂ"

"እሱማ ምን ይደርስብኛል?"

"ታዲያ ለምን ያለቅሳሉ?"

"ሳስበው ነዋ!"

"ምኑን?"

"እንዲያው በጠቅላላው"

"በሉ እያሰቡት እያለቀሱ ይቆዩን። እኛ እዚች ገባ ብለን እንመለሳለን"

"እምባዬ ቢያልቅስ?"

"ግድየሉትም እንተካሉታለን"

ሽማግሌው በፈገግታ "እሺ'ንግዲያው" አሉ "እዚች ዛፍ ስር ቁጭ ብዬ እያለቀስኩ እቆያችኋለሁ"

"ይሁን"

"ተባረኩ ልጆቼ"

"አሜን"

አቶ ብርሃኑና አቶ ጥላሁን ቶሎ ብለው ሸሹ። ወደ ጠጅ ቤቱ ሲገቡ የፊት በሩን አለፉ። በቀኝ በኩል ከባህር ዛፍ አጠገብ እተቆፈረው በቆርቆሮ እተከበበው ሽንት ቤት በር ላይ ቆሞ እየለ

አዝማሪው ሽንቱን ሲሸና ቆይቶ ኖሮ፣ መሽኛውን አራግፎ ሸንቶ ሱሪውን እየቆለፈ ዘወር ሲል ጊዜ

አየለ አዝማሪው አይደለም ሌላ ሰው ነው

"አይ ክፋትህ! አስመስለህ አለማስመሰልህ!" አሉ ሊቀ-ስነቃል ጥላሁን

ሶስት ንቦች በቋንቋቸው እየተጫዋወቱ ይሁን እየተጨቃጨቁ መጥተው፣ አቶ ብርሃነንና አቶ ጥላሁንን ሁለት ጊዜ ከዞሩዋቸው በኋላ፣ ለእመት አበሻነሽ አጋፋሪነት ያደሩ ይመስል ወደ ጠጅ ቤቱ መግቢያ እየመሩዋቸው፣ "ግቡ! ቤት ለ'ንግዳ!" አሉዋቸው "ቀረብ ብለን ስለተመለከትናችሁ ይቅርታ። ጆሮ ጠቢ ከገባ አየለ አዝማሪው እንደ ልቡ ስለማይዘፍንልን ነው"

አቶ ጥላሁን "እረ ግድ የለም ይገባናል ጉዳዩ" ሊሉ ሲሉ፣ አእምሮዋቸው "ንቦቹ ራሳቸው ጆሮ ጠቢ 'ንደሆኑስ?" ቢላቸው፣ ሊናገሩት የነበረውን ውጠው ዝም አሉ

ሽንታሙ ሰውዬ እየተንገዳገደ ቀድሞአቸው ገባ። ልክ አየለ አዝማሪውን ይመስላል ከኋላው

"አየለ አዝማሪው ይሆን 'ንዴ?"

"አይመስለኝም"

"እኔ ይመስለኛል"

"አይ፣ እንግዲህ እኔ ከኋላውና ከድምፁ ነው'ማውቀው"

"እኔም በፊቱ 'ማውቀው ብርሌ ወደ ላይ ደግኖ ራሱን ወደ ኋላ ቀልብሶ ያየሁት 'ንደሆነ ብቻ ነው"

"አዝማሪ አፉን ከፍቶ ያየሁ 'ንደሆነ ዘፈኑ ይበላሽብኛል"

"እኔም"

"ቅዳሴም ቢሆን ያው ነው"

"እኔማ ቄሶችን ካንገት በላይ አላያቸውም ሲቀድሱ!"

"እኔ እግራቸውንም ማየት አልወድም ሲወርቡ ሲያሽበሽቡ:: አለልህ ያንዳንድ ሰው እግር፣ ከመንሻፈፉ የተነሳ ከሰውየው ስር ሁለት ተረከዙ ገጥሞ ቀጥ ያለ መስመር የሚሰራ:: እልፍ እምአእላፍ የሙጀሌ ሰራዊቶች ስሪት ታዘውበት፣ ስጋውን ሙጥጥ አርገው በልተው ጨርሰውት፣ አጥንትና የጥፍር ጉቶ አስቀርተውለት፣ ተረግሞ የደረቀ በለስ አስመስለውት፣ ተሸንፎ ተስፋ ቆርጦ፣ ሁለቱ እግሮች እርስ በርሳቸው ተመካከረው "አብረን መኖር አልቻልንም ኮከባችን አልገጠመምና፣ ምንም ብንዋደድ ብንላመድ..." ብለው አልቅሰው እንባ በእንባ ተራጭተው፣ ተሳስመውና ተሰነባብተው እንደ አብርሃምና እንደ ሎጥ "እንዳንገናኝ አንተ ወደ ቀኝ እኔ ወደ ግራ እንኮብልል" ተባብለው ተስማምተው ለመሄድ ተነስተው... ያስፈራኛል ሳሳበው፣ ሰውየው ተገምሶ ወደ ሁለት ቦታ ሲሄድ... ቅዳሴው ሲቋረጥ፣ ይሄ ጉድ ነው ወይስ ተአምር? ተብሎ ሲተች፣ መፃህፍት ሲጠቀሱ፣ ደባትር ሲወጋገዙ፣ ቀሳውስት ሲገዛዘቱ፣ በመቋሚያ ሲደባደቡ፣ ሲፈናከቱ... ሰይጣን ይህን እያየ በሳቅ ሲንተከተክ! እክህደክ ሰይጣን!"

አቶ ብርሃነና አቶ ጥላሁን እንዲህ እየተጨዋወቱ እጠጅ ቤቱ ሲገቡ፣ ፀሀይዋ ጠፋችና ሀረገወይን ብቅ አለችላቸው:: አቶ ጥላሁን ወደዚያው አመሩ

አቶ ብርሃነም የተነቀሰውን የመት አበሻነሽን ብርሌ አንገት ለማድነቅና ምሳሌ ለመስማት የሚመችበት ስፍራ መርጠው ተቀመጡ

መጀመሪያ የሰሙት ምሳሌ "ነገር ቢበዛ ባህያ 'ይጫንም" የሚል ነበር። ግን ምሳሌውን የተናገሩት እመት አበሻነሽ አልነበሩም። እንዲያውም እዚያ አልነበሩም እመት አበሻነሽ

ሸንታሙ ሰውዬ መጥቶ እነ አቶ ብርሃነ አጠገብ እየተቀመጠ "አንድ ታሪክ አለኝ፣ ዋጋው አንድ ብርሌ" አላቸው

"የታሪኩ ርእስ?" አሉት

"እመት አበሻነሽ ከቶ የት ደረሱ?"

"እሺ አራት ብርሌ" አሉት

"አንድ ብርሌ። ታሪኩ ከዛ በላይ አውጥቶ አያውቅም" አላቸው

"አራት ብርሌ ተኩል። ለመት አበሻነሽ እንዴት ከዚህ በታች እንከፍላለን?"

"እሺ ለናንተ ስል አንድ ብርሌ ተሩብ" አላቸው

"ተው አራት ብርሌ ይሁንልህ"

"አንድ ተኩል"

"ይልቅ በል እርግጠኛውን ዋጋ ተቀበል"

"እሺ ሁለት ብርሌ"

"እሺ። ንሺ አንቺ ልጅ፣ ሶስት ብርሌ" አሉዋት አንገትዋ ብርሌ የሚመስለውን አሳላፊ፣ ጡትም ቂጥም ሳይኖራት ለምን እንደተፈጠረች እየገረማቸው

ሶስት ብርሌ አምጥታ አንዱን አቶ ብርሃነ ፊት አንዱን አቶ ጥላሁን ፊት ሌላውን ሽንታሙ ሰውዬ ፊት አኖረች

"ቅጂ" አሉዋት

"ልቅዳ?"

"ቅጂ!"

"በኋላ ይቆጫችኋል"

ሽንታሙ ሰውዬ "ይልቅ ቅጂ! ቂንጥራም!" አላት

"አንተ ቂንጥራም 'ንደሆንክ ተናገር 'ንጂ እኛስ በዘራችንም የለብን!" አለቻቸው በኩራት እየተነፋች

አቶ ብርሃነ "አትቆጪ የኔ'ህት፣ አንቺን ለማስቀየም ያልነው አይደለም" ብሰው አባብሰው ጠጁን አስቀዱዋትና፣ በልባቸው ደግሞ "ቂንጥርም የላት! ለምን ተፈጠረች ይሆን? ስላሴ ቤተስኪያን ሄጀ አባ ሀብተ ማርያምን መጠየቅ አለብኝ" ብለው እያሰቡ

"እሙት አበሻነሽስ?" አሉት ሽንታሙን ሰካራም

"ብቻ በኋላ ክሱ ለማን እንዳትሉ፡፡ ምስክርነት መጠራት አልፈልግም፡፡ እዚያ ፍርድ ቤት ጠጅ የላቸውም አሉ"

"በሆዳችን እንይዘዋለን፡፡ አይዞህ ተናገር"

"ማሉልኝ"

"ያንተን ስጋ!"

"ደሜስ?"

"ያንተን ደም!"

በስጋ ወደሙ ሲምሉለት ጊዜ ሰካራሙ ድንገት ከስካሩ ወጥቶ የሚከተለውን ነገራቸው

***

በህማማት ሰሞን እሙት አበሻነሽ ማለዳ ተነስተው ልጆቻቸውን አስከትለው ቤተስኪያን ሊስሙ ሲያዘግሙ፣ ከአቋራጭ መንገድ ከተፍ አሉ ፈረንጅ ሴቶች እየተሽቀዳደሙ፣ እየተጋፉ፣ ኮተት ተሸክመው እያስከለሉ፡፡ አልፈው ወደኋላ እየተገላመጡ

"ይሩጡ 'ንጂ አንቱ ሴትዮ!" አሉዋቸው "ይድረሱብን 'ንጂ! ኧረ ይሩጡ ባክዎትን! ጊዜ ቆሞ አይጠብቅም ይሩጡ!.... ሩጪ 'ንጂ ሴትዮ! ሲነግሩዋትም አትሰማ? እኛ በሩብ ሰአት አራት ጋሻ እናቋርጣለን፡፡ እንዲህ እየተንቀረፈፍሽ ልትደርሺብን አትችይም፡፡ ደግሞስ ምነው ተዝናንተሽ መራመድሽ? ይሉኝታም አትፈሪ? ባይሆን አንድ ሁለት ድንጋይ፣ አንድ ሁለት ግንድ ተሸከሚ 'ንጂ ለቤት መስሪያ"

ይህን እያሉ ቀልባቸውን ሲያበሳጩባቸው፣ እሙት አበሻነሽ መቼም ቢሆን ሰው ምን ይለኛል እያሉ የሚኖሩ ጨዋ ሴት ናቸውና፣ ሲፈሩ ሲቸሩ ከፈረንጆቹ ሴቶች ኋላ ኋላ መሮጥ ጀመሩ

ረጅም ቀሚሳቸው ጠልፎ ቢጥላቸው፣ ጎበዝ ልጃቸው ተፈሪ ጉትቻቸውን ለፈረንጆቹ ሴቶች በማስያዝ የዛገ መቀስ ተውሶ ቀሚሳቸውን ቆርጦ አሳጠረው፡፡ በዚያውም ሶስት አጣና አሸከማቸው

ተነስተው ከፈረንጆቹ ሴቶች ኋላ ኋላ ኩስ ኩስ ሲሉ፣ ተክለ ሃይማኖት የተባለው ልጃቸው "ኧረ ራቁትሽን ወጣሽ እማማ! ደሞስ የምን አጣና መሸከም ነው? የምንኖርበት ቤት ምን አለንና ነው?" ቢላቸው

ታላቅ ልጃቸው ተፈሪ በዛገው መቀስ አስፈራርቶ ዝም አሰኘውና "ሩጪ እማማ! ሩጪ ተከተያቸው:: እልፍ እንዳልን ጫማ ያውሱንና በጫማ ትሮጪያለሽ" ብሎ ሲገፋፋቸው ሲወተውታቸው

ተክለ ሃይማኖት ለራሱ "ያልለመደችው ጫማ ይከብዳታል 'ንጂ መች ያግዛታል?" ብሎ አጉረመረመ፣ ጮሆ እንዳይናገር መቀስ በመፍራቱ

እንግዳሸት ትንሹ ልጃቸው "እማማ፣ ከኋላሽ 'የመጡ 'ያለፉሽ ሄዱ:: ደሞ አጣናዎቹ ተዛብተዋል፣ በደምብ ያዥያቸው" ሲላቸው ጊዜ፣ ተፈሪ እንዴ በኩርኩም ብሎ ዝም አሰኘው

ሩጫው ቀጠለ:: ተፈሪ የመት አበሻነሽን ሀብልና እልቦ አስይዞ ጫማ ተዋሰላቸው:: ጫማው ሾካራና ከባድ ከመሆኑም በላይ፣ ግራ እግሩ ጠበባቸው ቀኝ እግሩ ሰፋቸው:: ያልለመዱት ስለሆነም እግሮቻቸው እየተማቱ ተላላጡ:: ቢቸግራቸው ጫማዎቹን አውልቀው በእጃቸው ይዘው ሩጫውን ቀጠሉ

ተፈሪም "አይዞሽ!" አላቸው "ይኸ ጫማ ቆዳ ስለሆነ ነው:: እንደ ምንም ብዬ ሸራ ጫማ 'ዋስልሻለሁ"

ክንፉ የተባለው ልጃቸው "ኧረ ይሄ ሁሉ ሩጫ ወዴት ነው? ቤተስኪያኑ ያለው ወዲያ በቀኝ በኩል" አለ:: ወንድሞቹ ሁሉ ሳቁበት እንደ ልማዳቸው፣ እብድ ስለሆነ

እመት አበሻነሽ ሩጫቸውን ቀጠሉ፣ ባዶ ሆዳቸውን ከፈረንጆቹ ሴቶች ኋላ ኋላ ሱክ ሱክ እያሉ፣ የግምባራቸው ላብ እየወረደ፣ የእግራቸው ደም እየተንጠባጠበ...

ስካራሙ ታሪኩን አቋርጦ ብድግ አለ "እግዚሄር ጠጅን ፈጥሮ ሸንትንም አብሮ መፍጠሩ ልክ አይደለም" እያለ ሲወጣ ሲል

"ታሪኩ ሳያልቅ?" አሉት አቶ ጥላሁን

"ሸንቴን እስክሸና እናንተው ጨርሳችሁት ቆዩኝ" አላቸው

"እኛ አናውቀውማ"

"እኔስ ብሆን መች አውቀዋለሁ? መናገር ስትጀምሩ እሱ አውቆ ይመጣላችኋል"

ልክ እሱ ሲወጣ፣ እመት አበሻነሽ ፈልሰስ እያሉ ገቡና "ወይ ጊዜ!" አሉ

"ምነው እሜቴ?" አሉዋቸው አቶ ብርሃነ

"ጃንሆይን አወረዱዋቸው አሉ"

"ኧረ የስላሴ ያለህ! እንዴት አርገው አወረዱዋቸው ይላሉ?"

"እንዲያው እንደ ተጣደ ድስት ብድግ አርገው አወረዱዋቸው አሉ"

አቶ ብርሃነ "ወይ ተአምር! ሀሬገወይን፣ እስቲ ቅጂልን ልጂ" አሉና፣ እመት አበሻነሽ ካሁን አሁን አንድ ሁለት ቀንጆ ምሳሌ ይናገራሉ ብለው ቢጠብቁ፣ እመት አበሻነሽ ዝም፡፡ አልፎ

አልፎ ብቻ ለገዛ ራሳቸው "እንደ ተጣደ ድስት! ወይ አንቺ 'ምዬ ማርያም!" ይሉና ዝም።

እኛም ዝም፣ ድስት እንደ ተጣደበት ጉልቻ።

***

አቶዎች ብርሃነና ጥላሁን ከጠጅ ቤቱ ሲወጡ ባለ ሻኛው ባለ ሎተሪ ቁጭ ብለው አባራው ላይ ቅልቦሽ ሲጫወቱ አገኙዋቸው

"ማልቀሱን የተዉት ይመስላል" አሉዋቸው አቶ ብርሃነ

"ይመስላል፣ ነውም። ልጅ ስትናፍቀኝ ማልቀሱን እተውና ቅልቦሽ እጫወታለሁ"

"ልጅ አለቻታ!"

"ብትኖረኝ'ኮ ነው 'ምትናፍቀኝ" አሉ ቅልቦሻቸውን እየተጫወቱ

"ባለሻኛ ናት?"

"እረ 'ኋ! ሲያልፍም አይነካት! ፈጣሪ ሲቀርፃት የዋለ ውቢት ናት ብታዩዋት... መልኳ ደም ቁርጥ የኔን እናት። በዘራችን ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፣ ሴቶቻችን ሻኛ የላቸውም"

"ወንዶቹስ?"

"ወንዶቹ ሁላችንም ባለሻኛ ነን። ሚስቶቻችን ሲወልዱ ከነሻኛው ከነቃጭሉ ዱብ ነው"

"እንዲያው ዱብ!" አሉ አቶ ብርሃነ አንድ ብር ጠጠሮቹ ላይ እየጣሉ

"ከነሻኛው ከነቃጭሉ!" አሉ አቶ ጥላሁን አንድ ብር ዱብ እያደረጉ

ተሰናብተዋቸው ወደ መኪናቸው ገብተው አቶ ብርሃነ ሞተር ሲቀሰቅሱ፣ አቶ ጥላሁን "ሰማይ ቤት ባለሻኛዎች ይኖራሉ ብለህ?" አሉ

"ምናባቴን አውቄ?"

"አታውቅም?"

"አላውቅም"

"ቆይ አሁን ውስጥ እግርህን ሲገርፋህ ይገለፅልሃል። ቷ!..."

## ቢራቢሮ

ቢራቢሮ እንደ ደብተር ተከፍታ ደረቷን ለጧት ፀሀይ ሰጥታለች። ደስ ማለቱ! የጧት ፀሀይሙቀቱ!

ሽው ብሎ በላይዋ ላይ አለፈ - አስደንጋጩ የድምቢጥ ጥላ ክንፏ ዝግት! ጸጥ!

ከነድምቢጥ ሆነ ከሌሎቹ የሞት መላእክት ራሷን የምትከላከልበት አንድም መሳሪያ የላት። ወላ ጥርስ - ወላ ቀንድ - ወላ መርዝ - ምንም!

ምክር ፍለጋ ዶክተር ኤሊ ዘንድ ሄደች። ዶክተር ኤሊ ጥንት ከነቢዩ ኤልያስ ጋር ነበሩ። የመፃህፍትና የአበው ጥበብ በድንጋይ ልብሳቸው ሙሉ ተጽፏል እየተባለ ይነገርላቸዋል

ቢራቢሮ ፍርሀቷን ነገረቻቸው፡፡ ፈጣሪ ዘንድ አቤቱታ አቅርቢ አሏትና መንገዱን አመላከቷት፡፡

ቢራቢሮ ጓደኛዋን ሱፍ-አበባን ልትሰናበታት ሄደች፡፡ ሱፍ-አበባም እንዲህ አለቻት

"አንቺማ ታድለሻል፡፡ ብር! ብለሽ ሄደሽ 'አቤት' ትያለሽ፡፡ እኔ እንዳንቺ ክንፍ ቢኖረኝ ገና ገና ድሮ ሄጄ ነበር፣ ፀሀይዬ አጠገብ ለመሆን፡፡ አቤት ደስታ! ፀሀይን መጠጋት! ፀሀይን መንካት! ለኔ መንግስተ ሰማያት ነበር! ዳሩ ምን ይሆናል? እኔና ፀሀይ ከሩቅ መፈላለግ ብቻ ሆነ እጣችን፡፡ የአይን ፍቅር የምትሉት ይመስለኛል - አይን ስለሌለኝ ሊገባኝ ባይችልም"

ቢራቢሮ ለጓደኛዋ አዘነችላት

"ለምን አትልኪኝም?" አለቻት "ፈጣሪን ሳገኘው ምን ልበልልሽ?"

"ቀን ቀን ባለሁበት ተተክዬ ፀሀይን ስከተል እውላለሁ፡፡ ሌሊት ሌሊት ባለሁበት ተደፍቼ ፀሀይን ስናፍቅ አድራለሁ፡፡ እባክህን እዘንልኝ፣ ራራልኝ፣ ርህሩህ ነህ ይባላል፡፡ ላንድ ቀን፣ ላንድ ሰአት፣ ላንድ ቅፅበት ፀሀይን የማይበት አይን ስጠኝ በይልኝ"

"እሺ" አለችና ቢራቢሮ፣ ሱፍ-አበባ ለስንቅ የሰጠቻትን ወለላ እስኪበቃት ጠጥታ ተሰናብታ በረራዋን ቀጠለች

ፈጣሪ ዘንድ ስትደርስ በቢራቢሮ ስርአት ሰገደችለትና ጉዳይዋን ተናገረች፡፡

"ይህን ሁሉ መንገድ ስትመጪ፣ እነድምቢጥ ወይም ሌሎች እንዴት ሳይበሉሽ ቀሩ?" አላት

"እኔ'ንጃ። ባያዩኝ ይሆናላ!"

"እንዲህ በአበባ ቀለማት አሸብርቀሽ እንዴት አላዩሽም?"

"እኔ'ንጃ። ምናልባት የበረራዬ አይነት ይሆናል። ቢራቢሮ ሳልሆን፣ የረገፈ በነፋስ የሚውለበለብ ቅጠል መሳይ ነገር መስያቸው እንደሁ?"

"ሆነ። በይ ያውልሽ ያ ትልቅ ቅርጫት። ከውስጡ የፈለግሽውን ሁሉ መሳሪያ ውሰጂ"

አሁንም በቢራቢሮ ባህል እጅ ነሳችና ወደ ቅርጫቱ በረረች እየተውለበለበች። አቤት የመሳሪያዎቹ አይነት! መምረጥ እስኪያስቸግራት ሆነ።

ከብዙ ማመንታት በኋላ ሶስት መሳሪያ መረጠች -- የሾሉ ሹላሹል ጥርሶች፣ እና ሲሾል የኖረ ሹል ጦር፣ እና ጨኸት። አስፈሪነቱ ከአንበሳ ጩኸት ሰባት ጊዜ የሚያስደነግጥ ጩኸተ ጩኸት።

እንግዲህ ውልብልቢት ቢራቢሮ በምናብ እነ አዳሜ ድምቢጥን በጩኸተ ጩኸቷ አስበርግጋ ስታበቃ፣ እድሜ ልኩን ሲሾል በኖረው ጦሯ ከመሬት ሰማዩ ጋር ስፍታቸው ስታበቃ፣ እንዲያው ለምርቃት ያህል ደሞ በሹላሹል ጥርሶቿ ስትበጫጭቃቸው -- ይህንና የመሳሰለውን ደጋግ ሀሳብ እያሰበች እየበረረች ወዳገሯ ስትመለስ፡-

ራባት

ከፈጣሪ ስትሰናበት ጀምሮ ያበባ ወለላ የጠማት ቢራቢሮ፣ አይኗ እያነጣጠረ ስትበር፣ አንዷ ፈጣሪ ሲያስውባት የከረመ፣ በደማቅ ቀለሟና በተአምራዊ መአዛዋ ትጣራለች

"አበባን የፈጠርክ ፈጣሪ! አቤት አፈጣጠሩን ስታውቅበት! ኧረ ተመስገን!" እያለች ቢራቢሮ አበባዋ ላይ አረፈች

ወለላውን ልትጠጣ ብትሞክር ታድያ፣ በየት በኩል? ጥርሶቿ - እንዲያ በጥንቃቄ የመረጠቻቸውና እንዲያ ስትመካባቸው የቆየች ጥርሶቿ፣ አላስጠጣ አሏት፡፡ ይባስ ብለው ደሞ ያችን የጠራቻትን አበባ በሚጨቋት እነዚያ ባይተዋር ጥርሶች!

ቅፅበታዊ ውስጣዊ ፀጥታ -- ክንፏ ፀጥ እርጥ እስኪል ድረስ...

"እንዲያውስ ጥርስ ምን ሊያረግልኝ ኖሯል? የኔ ምግብ እንደሆነ አይታኘክ፡፡ ለሳቅ ለፈገግታ እንደሆነ፣ የኔ ሳቅ ፈገግታዬ ክንፌና በረራዬ ውስጥ ያበራሉ፡፡ ሌላው ትርፍ ሸክም!" አለችና፣ እነዚያን የሾሉ ሹላሹል ጥርሶች ወድያ አሽቀንጥራ ጣለቻቸው (እዝጌርን ስትጉብኝ በስውር ሲስልላት የነበረው ዲያብሎስ እንኳ ወደ ገሀነብ መቀመቅ ያን ያህል አልተወረወረም!)

ከአበባዋ ወለላዋን ጠጣችና ጉዞዋን ስትቀጥል "ሆ! ኧረ 'ንኳንም ጥርስ አልፈጠረልኝ!" አለች

በሚቀጥለው ምእራፍ (ማለቴ በረራ) ቢራቢሮ ሲሾል የኖረ ሹል ጦሯን ወደ ሰማይ አሾለች አመቻቸችና፣ ክንፎቿን እስከ ሚፍ ፀርግታ ደረቷን ለፀሀይ ሰጥታ ስታበቃ

"እነሆ በረከት! እነሆ ቢራቢሮ ለምላ!" አለች፣ በክንፎቿ ክፍት ክድን የቢራቢሮ ሳቅ እየሳቀች

ሸው! ብሎ ወረደ -- ለቢራቢሮ ሞትን የሚነ ድምቢጥ! ከሰማይ ያመጣችው ጦር ጥልቅ ሲልበት፣ ከህመሙ ይልቅ መገረሙ፣ መደንገጡ ብሶበት እዚያው ክንችር አለ

"አይ አቶ ድምቢጥ! ለካ የተጫንከው የኔን ሳይሆን የራስከን ሞት ኖሯል! ተመስገን!" እያለች ቢራቢሮ ሆዬ፣ ጦሩን ከድምቢጥየው ራሳ ላይ ለመንቀል ብትሞክር ብትፍጨረጨር፣ እሷ ትቦጨቅ እንደሆነ እንጂ ጦሩ የማይነቃነቅ ሆነ:: 'ደሞስ የደሙ ክርፋት!

"እንዲያውስ ጦር ምን ሊያረግልኝ ኖሯል? ገድያቸው እንዲህ ከሚገሙኝ፣ እንዲህ እንደ ሰይጣን ፊስ ከሚከረፉኝ፣ ብቅ ሲሉ ክንፌን እጥፍ አድርጌ አልሰወርባቸውም? ይሻለኛልም ይቀለኛልም" አለችና ጦሩን እዚያው ለድምቢጡ "ማስታወሻ ይሁንህ፣ ትቼልህለሁ" እያለች ወደ ሰፈሯ ሄደች (ማለቴ በረረች)

***

ሌላ የቢራቢሮ ምእራፍ (ማለቴ በረራ) እነሆ:-

ውድቅት ነው:: ፍጡራን እንደየ ፍጥርጥራቸው በየፊናቸው ሲመገቡ አርፍደው፣ እንደየአይነታቸው ውሀቸውን ጠጥተው፣ በየስፍራቸው እፎይ ብለው በማረፍም በማንቀላፋትም ላይ ናቸው::

ይህን ጊዜ ቢራቢሮ አበባ ላይ ተመቻችችና እዝጌር የሰጣትን፣ ከአንበሳ ጩኸት ሰባት ጊዜ ጉልቶ የሚጮኸውን እዲስየውን ጩኸቷን ለቀቀችው!

ፍጡራን ከመበርገግ የባሰ በረገጉ፣ ብዙ ሯጮች ወለም አላቸው፣ በርካታ በራሪዎች ክንፋቸውን ቅርንጫፍ አቆሰላቸው

ፍጡር ሁሉ በየበረገገበት እንደየፍጥርጥሩ አደፈጠ:: ብዙ ብዙ ቆይቶ በየፊናው አደጋውን ለማየት እዚህም እዚያም ተገላመጠ:: ማንም የለም:: ቀስ በቀስ ወደየስፍራቸው ተመለሱ

"እኔ ብቻ ሳልበረግግ" አለች ቢራቢሮ

"እሱን ተይው! ያልበረገገ የለም" አሉዋት

"ከኔ በስተቀር"

"እረ ባክሽ? አሁንስ አንጎልሽም እንደ በረራሽ አበደ'ንዴ አንበሳ ራሱ በርግጓል እንኳን አንቺ"

"ሽረሪት ትጠየቅ" አለችና ቢራቢሮ የውልብልብ እየበረረች ሄደች...

...እንግዲህ ሽረሪት ስትበረግግ መብረር ወይ መሮጥ ሳይሆን፣ ጥልቅ! ድብቅ! ሽፍን! ነው በዚያ በድርዋ - የምግብ ማግኛ መሳሪያዋ -- ልብሷ - ቤትዋ - እንቁላል መጣያዋ - በጥበቧ ከገዛ ውስጧ የፈጠረችው ድርዋ። የምን ከንቱ ልፋት? ጥበቡን ሰጥቷታል።

እና ከተሸሸገችበት ቀስ ብላ ብቅ ብትል፣ ቢራቢሮ ሆዬ አበባዋ ዙሪያ እየበረረች፣ ራሷን በራሷ እያባረረች በሳቅ ትንከተከታለች -- የክንፍ ሳቅ

"በረራሽ የእብድ መሆኑን አይቻለሁ" አለቻት ሽረሪት። "ግን ፍጥረትን በሙሉ የሚያስበረግግ ጩኸት ሲያስቅሽ ሰባቱ ነው ያበድሽው፣ አንዴም አይደለ"

"ያላስበረገገኝ ምክንያቱ የሙሀኩት እኔ ራሴ ስለሆንኩ ነው'ኮ!" አለቻት - ቀለማት ክንፎቿን እያክነፈነፈች

"እየባሰብሽ ሄደ። አሁንማ ሰባ ጊዜ ሰባት አበድሽ!"

ቢራቢሮ በረራዋን ትታ አበባዋ ላይ ቆመች - ተቀመጠች - ተሰየመችና፡-

"አንቺ ተአምራዊ ድር ሊኖርሽ ከቻለ፣ እኔ ሃያል - መርእድ - መደንግጽ ጩኸት ሊኖረኝ ለምን አይችልም? ወይስ የተፈጥሮን ምስጢር ሁሉ ታውቂዋለሽ?"

ሸረሪት ብዙ ስለማትንቀሳቀስ በጥሞና ለማሰብ ጊዜ አላት። ያውም ከድርዋ እኩል ተአምር የሆኑ ሀሳቦች። እርጋታ አለ ሸረሪት ቤት (ማለቴ ድር) ተረታችን ውስጥ፣ የመነኑት ባህታውያን እርጋታን ለመማር ወደ ሸረሪት ያተኩራሉ፣ ለሰባት ሙሉ ሰአት! (ያሬድ ማህሌታይን ሰባት አመት እናስታውሳለን)

ስለዚህ ሸረሪት በእርጋታ "አሳምኚኝ" አለቻት ቢራቢሮን፣

"አዳሜ ፍጡሬ ከብርጎጋዋ ተመልሳ በየስርፋዋ ታርፋለች፣ እማደል? ያን ጊዜ ትኩር ብለሽ እዪኝ። እጮህለሁ፣ ይበረግጋሉ። አንቺ ግን ስጮህ እያየሽኝ ስለሚሆን አትደነግጪም"

እንደተባባሉትም ፍጡር ሁላ እንደየድፍረትዋ፣ በየተራዋ በየስርፋዋ ተመልሳ አረፈች።

ቢራቢሮ ለምናልባቱ ሸረሪትን ለማስጠንቀቅ ጥቂት በራረረች-- አበባዋ ላይ አረፈች -- እና ድምፁን - ጩኸቱን - ከፈጣሪ ቤት ያመጣችውን (እና፣ እብድም ይጠነቀቃልና፣ በጥንቃቄ የክንፏን ቀለም አስመስላ ክንፏ ላይ ለጥፋ ደብቃው የነበረውን ጩኸት) አነሳችና፡-

አንድ ጊዜ ስትጮኸው ጊዜ፣ ፍጡሬ አዳሜ እንደ ቅድሙ አልበረገገላችሁም!?

ቢራቢሮ እየበረረች ባበባዋ ዙሪያ በክንፏ ስትስቅ -- ስትስቅ - ስትስቅ --

"እሽ! እስቲ ዝም በይ አንዴ" አለቻት ሽረሪት "ሳይመለሱ ስሚኝ፣ ሲመለሱ ምንም እንደማናውቅ እናስመስል፡፡ በኋላ በየስርፋቸው ሲያርፉ ጨኸትሽን ስጪኝና አንዴ ልጨኸው"

"እኔ ገና አልጠገብኩትማ!"

"ተይ ተይ ተይ! እንዴ ብቻ? እሺ እንለዋወጥ፡፡ ያንቺን ጨኸት ላንዴ ብቻ ስጪኝ፣ የኔን ድር ጥበብ አስተምርሻለሁ፡፡ አቤት አንዴ ብትወዘውዢ! በኔ ድር! ሽረሪት በሆንኩ! ትያለሽ፡፡"

"እሺ" አለቻትና ተለዋወጡ፡፡ ቢራቢሮ በሀር ክር ጥቂት ከተወዛወዘች በኋላ ሰለቻትና "እንቺ ድርሽን፡፡ እኔ መሄዴ ነው" አለቻት

"አንዴ'ንኳ ሳልጮህባቸው? ያውም እሺ ብለሽኝ?"

"እረ አስር ጊዜ ጨሂ ተፈለግሽ! ጨኸቱን መርቄልሻለሁ"

"ገና አልጠገብኩትም አላልሽም?"

"አሁን ጠገብኩታ" አለችና ቢራቢሮ፣ የውልብልብ እየበረረች ሄደች "ደሞ ጨኸት ምን ያረግልኛል?" እያለች ለራሷ "ትርፉ ሸክም!"

ሸረሪትም "ቢራቢሮን ያሳበድክ ተመስገን!" እያለች ጨኸቱን ለእንስሳቱ እያከራየች እጅጉን ከበረች፡፡ ምን መክበር ብቻ? ሚሊየኔር ሆነች

ለፈጣሪ ምን ይሳነዋል? እያለች

# አያ ድቡልቡሌና አጋፋሪ እንደሻው

(አጋፋሪ እንደሻው ፉከራቸው "እንደሻው አባ መኩት! ሸሽት ጋሻው ከሞት ይመክት" መሆኑ እየተስታወሰ)

አጋፋሪ እንደሻው በስድሳ ስድስት እመታቸው የሳምንት ስንቅ የተሜኘ በቅሎአቸውን አስከትለው ከቤቱ የወጡ፣ ሞትን ሲሸሹ፣ ከሞት የሚያስጥል ድግምት፣ እፅ፣ ወይም የሆነ ነገር ሲፈልጉ፣ ወይም ሞት የማይደርስበት ስፍራ ሲፈልጉ፣ ምድረ ሀበሻን ሲያዳርሱ፣ ሲከልሉና ሲሰልሉ ሰላሳ ሶስት አመት ካሳለፉ በኋላ... በዘጠና ዘጠኝ አመታቸው ወደ አዲሳባ ተመለሱ።

በየአውራጃው፣ በየወረዳው፣ በየገዳሙ፣ በየደብሩ (በሹክሹክታ እንንገራችሁና - በየጠንቋይ ቤቱ፣ በየመጣፍ ገላጩ በየኮከብ ቆጣሪው እና በየጠጠር ጣዩ ሳይቀር) ከሞት ማምለጫ

ሲፈልጉ ሰላሳ ሶስት አመት ካሳለፉ በኋላ፣ የመጨረሻ አዋቂ የተባለው ምን ይነግራቸዋል፦

የሞት መድሀኒት ሊገኝ የሚችለው ባዲሳባ ከተማ በተረት ሰፈር መግደላይት ቤተስኪያን መቃብር ቤት ከሚኖሩ አባ ሽንኩርት ከሚባሉ ባህታዊ ጋር በመመካከር ሊሆን ይችላል።

"እንሮዬ ያለውን ፍለጋ አገሩን አዳረስኩት!?" አሉ አጋፋሪ ለራሳቸው። ብቻ ያ ሁሉ ጉዞአቸው ምንም ያህል አልቆጫቸው። እንዲያው ለምናልባቱ ሞትን ማምለጥ ቢያቅታቸው በማለት (ለመጠባበቅ ያህል) በየሄዱበት ዘራቸውን ዘርተዋል። ከነዙት ሺና ሺ ዘር ስንቱ በቅሎ እንደሆን ባያውቁም ቅሉ፣ መዝራቱ ራሱ እጅግ በጣም አስደሳች ስለነበር፣ ብዙው ባይበቅልም ያን ያህል አያሳሳባቸውም

አጋፋሪ እንደሻው ተረት ሰፈር ደርሰው፣ ሴጣን ቤትን እንደ ወዲህ ትተው፣ የጆሮ ቆራጩን ቤት አልፈው (ጆሮአቸው እንዳይታይ ቀጭን ኩታቸውን በጥንቃቄ ተከናንበው ነው መቸስ የታወቀ ነው) የጭራቁን ግቢ አልፈው፣ መግደላይት የት እንደሆነች ለመጠየቅ ሰው ሲፈልጉ፦

አዩት ዛፍ ስር ራቁቱን ተጋድሞ፣ አላፊ አግዳሚው እንዳያየው ነጠላውን ወደ መንገድ በኩል ጋርዶ። አጋፋሪ ግን በበቅሎ በመሆናቸው ቁልቁል አዩት

"ቤቶች!" እንዳይሉ ነጠላ ነው "ነጠላዎች!" እንዳይሉም ስድብ ሊመስል ይችላል። ስለዚህ "እንዴት ዋላችሁ!?" አሉ ባጭሩ

"እንደነገሩ" አላቸው እሱ በበኩሉ

"እንዴት ማለት እንደነገሩ?" ቢሉት

"እንደሚያዩት ነዋ"

እንግዲህ "ወጉሳ ማእረጉሳ" ሊለኝ ነው ብለው እያሰቡ "እንደማየውማ ነጠላውን መልበስ በተሻለ" አሉት

"ውስጡን ለማያውቅማ ይመስለዋል"

"ውስጡ ከውጪው የተለየ ነው?"

"ከመለየትም አልፎ ተገላቢጦሽ ነው"

"እንዴት ነው የተገላበጠው?"

"እሱንማ ለማወቅ ተረቴን እውነቴን በእርጋታ መስማት ያሻል"

"ረጋ በልና ልስማዋ፣ ንገረኝ"

"ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ" አላቸው::

ውስጡን "እሱን ለሌላ ንገር!" እያሉ "በጄ!" አሉት

"እሱስ ምንም አልበጀ:: ብቻ ልቀጥልልዎ:: ግን እውነቱ ተረቴ ረዘም ያለ በመሆኑ፣ ከበቅሎዎ ወርደው እዚች ጥላ ስር አረፍ ብለው ቢያደምጡኝ ይሻል ይመስለኛል"

ወረዱ አጋፋሪ፣ ልጓሙን ገብሬ ተቀበለ:: መጋረጃውን ነጠላ አልፈው "ሰውዬው" አጠገብ ተቀመጡ:: ነጠላው ካላፊ አግዳሚው ጋርዷቸዋል

"ሰውዬው" ታሪኩን እንዲህ ሲል እንደገና ጀመረ:: "ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ:: ማክሰኞ የወላጆቼ ሰርግ ተደገሰና ጠላው ተጠምቆ፣ ሰንጋው

ተጥሎ፣ ሲበላ አደግድጌ ሳሳልፍ አረፈድኩ። እየተጠጣ ሲዘፈን ብዙ ከቆየ በኋላ ያ የደምቡ ሆነና ነው መሰል "ብራምባር ሰበረልም" ብለው መዝፈን ሲጀምሩ ጊዜ እንደማፈር አልኩ። እውነት ብራምባሩ ገና አሁን ከተሰበረ፣ እኔ ገና አልተወለድኩም የለሁም ማለት ሊሆንብኝ ሆነ። ቢበዛ ህልም ነኝ፣ ያውም የማን ህልም እንደሆንኩ እንኳን እንጃ ማለት ሊሆንብኝ ሆነ። ምናልባት እኔ እውነት ተወልጄ ከሆነ ደግሞ፣ ዘፈኑ አባቴን ውሽታም ወይም ውርደታም ወይም ሞኝ ሊያረግብኝ ሆነ። እናቴንም ውሽታም ነውረኛ ሊያረግብኝ ሆነ። ሲጨንቀኝ ቀስ ብዬ ከዳሱ ወጣሁ

ልክ እኔ ስወጣ እረኛችን ከወድያ መጣና ከሁሉ አብልጬ እምወዳት ላማችን መጥፋትዋን ነገረኝ። ፍለጋ ተነሳሁ። አገሩን አዳረስኩ። ትልልቁ ዛፍ ላይ እየወጣሁ ዙሪያውን ብቃኝ ላሚቱ የለችም። ያገራችንን ትልቁን ጋራ ወጥቼ ከጫፉ ላይ ያለውን ትልቅ ጥድ ወጥቼ ዙሪያውን ብመለከትም አጣሁዋት

"ተስፋ ከመቁረጤ በፊት አንድ ቦታ ልሞክር" አልኩና፣ ከሁሉ ዝቅተኛ ሸለቆ ወርጄ፣ እዚያ አንድ እጅግ የጠለቀ ጉድጓድ አለ፣ እጉድጓዱ ገባሁና በመርፌ ቀዳዳ አሻግሬ እመለከታለሁ

ላሚቱን ስምንት ሌቦች ነድተው ወስደዋት ኖሮ፣ እጉንደር ገብተው አርደው ሲቀራመቱዋት ወለል ብለው ታዩኝ

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ። ዛሬ ማክሰኞ ነው"

"አርብ ነው'ንጂ" አሉት አጋፋሪ

"ለናንተማ አርብ ነው። ለኔ ግን ማክሰኞ ነው። ከማክሰኞ ሳልወጣ ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ተንከራተትኩ"

"ይህ እንዴት ይሆናል?" አሉት አጋፋሪ

"ልንገርዎት አደል? ሌቦቹ ሳይበታተኑ ልድረስባቸው አልኩና በፍጥነት ፈረሴ ላይ ወጥቼ እንደ ደራሽ ወንዝ ስጋልብ እንደ ነፋስ ስሽመጥጥ፣ ከፊት ለፊቴ አንድ ገደል እንደ መቀመቅ አፉን ከፍቶ ሊውጠኝ ተዘጋጅቶ ታየኝ። ፈረሴን እየኮረኮርኩትና ባለንጋ ሾጥ እያደረግኩት ከዚህኛው አፋፍ ተወረወርን። ፈረስ እንደዚያ ዘሎ ያውቅ አይመስለኝም። ግን አልሆነለትም። ገደል ገባና ተንኮታኮተ - ኮርቻው ይዞኝ ተሻገረ

ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"ብጄ" አሉት አጋፋሪ

ሌቦቹን ደረስኩባቸውና "ላሜን ውለዱ" አልኳቸው

"እንክፈልህ" አሉኝ

"ክፍያ አላውቅም። የምፈልገው ላሜን ነው" አልኳቸው

"መቶ ብር እንክፈልህ፣ ሃያ ላም ይገዛል" አሉኝ

"ሃያ ላም አልፈልግም፣ ላሜን አምጡ"

"እንግድያው ይኸው ቆዳዋን ውሰድ። በስጋዋ ምትክ ስምንታችን ስምንት ስምንት ፍሪ ጤፍ እንሰጥህ" አሉኝ።

እሺ አልኩና በቆዳዋ ከበሮ ሰራሁ። እውስጡ አንድ ዝምብ ከትቼበት ዛፍ ላይ ሰቀልኩት። ዝምቡ ከውስጥ ከበሮውን እየመታ፣ ዙሪያውን እስከ ሰባት ወንዝ የሚኖሩ ሰዎች ሰባት አመት ሙሉ እስክስታ ወረዱበት።

ዋሸቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"እሺ" አሉት አጋፋሪ

ሌቦቹን ተሰናበትኩና ጤፌን በስልቻ ተሸክሜ ወዳገሬ ጉዞ ጀመርኩ። ልክ አገሬ ልገባ የስምንት ቀን መንገድ ሲቀረኝ ሀይለኛ ዝናብ ወረደ። አብረውኝ ይጓዙ የነበሩ መንገደኞች ጉፈሬዬ ስር ተጠልለው ዝናቡን አሳለፉ። ግን ሳላስበው በልማድ ውሃውን ከጠጉሬ አራገፍኩትና ወንዝ ሆኖ ጠራርጎ ወሰዳቸው

ዋሸቱ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"ከዚያስ?" አሉት አጋፋሪ

ከዚያ ስልቻዬን ተሸክሜ መንገዴን ስቀጥል፣ ስዎች ከኋላዬ "ሰውዬ ጤፍህ ፈሰሰ" ሲሉ ሰማሁ

ዞወር እላለሁ፣ ጤፉ ድንቅ ሆኖ በቅሏል። እዚያው በዚያው እያየሁት አሸተና እዚያው ለአጨዳ ደረሰ። ታድያ በሰላ ማጭድ ብለው ብለው፣ ጨርሶ አልታጨድ አለኝ። በምን ልጨደው ይሆን? እያልኩ ሳስብ፣ ከሩቅ ሁለት አሞራዎች ወደኔ በኩል እየበረሩ ሲመጡ አየሁ

ጠመንጃዬን አቀባበልኩና አነጣጥሬ ተኩስኩ፣ አንደኛውን አሞራ ደረቱን መታሁት። እሱ መብረሩን ቀጠለ። ሁለተኛው አሞራ ግን የዚያኛው ደም ተፈናጥሮ መታውና ከርብት ብሎ አጠገቤ ወደቀ። አንድ ላባ ነጭቼ ጤፉን በሱ አጨድኩና ከመርኩት። አቤት ክምር!

ስምንት በሬ አፈላለግኩና ላሄደው ብሞክር፣ በጭራሽ አልተቻለም። እንግዲያው እሺ አልኩና፣ ስምንት ቁሀን ጠምጄ ሀይ ብለው፣ ስምንት ስልቻ ጤፍ

ስምንት ወደል አህያ አምጥቼ ልጭናቸው ብል አልቻሉትም፣ ወገባቸው ሊሰበር ሆን። ዳውላዎቻቸውን አራገፍኩና ስምንት ጉንዳን ፈላልጌ፣ ስምንት ስልቻ ጤፌን እነሱ ላይ ጭኜ መንገዴን ቀጠልኩ

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"በጀ" አሉ አጋፋሪ እንደሻው

የስምንት ቀን ጉዞ አልነበረም የቀረኝ? ስምንት ቀን ተጉዤ የት እንደደረስኩ እጠይቃለሁ ታዲያ፣ ካገሬ የአስራ ስድስት ቀን ጉዞ ርቀት ላይ ነው ያለሁት።

ይህ ሁሉ - እና ብዙ ሌላ ተገላቢጦሽ ነገር - ሲደርስብኝ አስራ አንድ አመት አለፈ። በመጨረሻም ስምንቱን ጉንዳን እየነዳሁ አገሬ ገባሁ። ቤት እደርሳለሁ ታድያ፣ ዳሱም እንዳለ ነው፣ ዘፈኑም ያው "ብራ-ምባር ሰበረልም" ነው፣ የማን ሰርግ ነው ብዬ ብጠይቅም ያው የወላጆቼ ሰርግ ነው

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"በጀ" አሉ አጋፋሪ እንደሻው

ተመልሼ ሸሸሁ

ከዚያ በኋላ የደረሰብኝ አንድ ባንድ ብነግርም ማስልቸትም ይሆናል ብዙ ስለሆነ ከጉዳይም ማስተጓጎልም ይሆናል፣ ያው ሁሉም ተገላቢጦሽ ነው። ስለዚህ ተረቴ እውነቱ እንዲታይም ያህል ዋና ዋናውን ልንገርም።

"እሺ" አሉ አጋፋሪ እንደሻው

ነፋስን መንገድ ላይ አገኘሁትና፣ ውሰደኝ አሰምን አዙረኝ አልኩት። ግዙፎችን አልሸከምም አለኝ።

"የእናቴና የአባቴ ሰርግ ገና እየተደገሰ ነው። ገና ብራምባር ሰበረልዎ እየተዘፈነ ነው። ስለዚህ ገና አልተወለድ ኩም። እንኳን ልወለድ ገና አልተረገዝኩ። ግዙፍ ብመስልም ገና ረቂቅ ነኝ" አልኩት። እሺ እንግዲያው፣ አለኝና አሰምን አዞረኝ። ለአስራ አንድ አመት ብዙ ተገላቢጦሽ ነገር ከደረሰብኝ በኋላ፣ በግብፅ አርገን ተመለስንና፣ ነፋስ ካነሳኝ መልሶ አስቀምጦኝ፣ መንገዱን መንፈሱን ቀጠለ

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"እስቾጋሪ እጣ ነው ያንተስ" አሉ አጋፋሪነታቸው በልባቸው። "ከዚያስ" አሉ ባንደበታቸው፣ ባንድ በኩል "ሰውዬው" እያሳዘናቸው፣ በሌላ በኩል ነገሩን ማመን እያስቸገራቸው

ከዚያማ አዛውንቱን ተሰናብቼ ወጣሁ። እሁንም ካገሬ መውጣት አለብኝ ብዬ ስሄድ፣ ልክ ካስራ አንድ አመት በፊት ነፋስን አገኘሁበት ቦታ፣ ከዚያ በፊት ደግሞ አስራ አንድ አመት አስቀድሞ እረኛችን ላሚቱ ጠፋኝ ያለኝ ቦታ ስደርስ፣ ሞትን ፊት ለፊት አገኘሁት።

(አሁንማ ልባቸው ይመታ ጀመር ያጋፋሪነታቸው! "ሰውዬው" ከበሮ በተዘጋበት ዝምቡ የመታውን ያህል፣ ወይም ደብልጥ ይመታ ጀመር) "በጀ" አሉት

እሁንም ወደ ቤታችን ብመጣ፣ እሁንም ዳሱ ያው እንዳለ ነው ቅጠሎቹ እንኳ አልጠወለጉም፣ ብራምባር ሰበረልዎ እየተዘፈነ ነው፣ ሰርጉም ያው ያባቴና የናቴ ነው።

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ እሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"በጀ፣ ቀጥል" አሉ አጋፋሪነታቸው

በልቤ "አይ አሁንስ ውስጡን ማየት አለብኝ" እያልኩ ወደ ዳሱ ብገባ፣ በዚህ በኩል ጕረምሳው እየጨፈረ ብራምባር ይዘፍናል፣ በዚህ በኩል አዛውንቱ ጠላ በዋንጫ ፉት እያሉ ያወጋሉ

ወደ አዛውንቱ ሄድኩና እጅ ብነሳ

"አንተ ሰው ማነህ?" አሉኝ

"እኔ" አልኳቸው

"ከየት መጣህ?"

"ከግብጥ"

"በምን መጣህ?"

"በፍልጥ"

"ምን ይዘህ መጣህ?"

"ጭብጥ ጥጥ"

"በምን አስረህ?"

"በድንጋይ ልጥ"

"ትቀልዳለህ?"

"የምትቀልዱስ እናንተ፣ ሃያ ሁለት አመት ሙሉ አንድ ሰርግ ድግስ ላይ የምትቀመጡ።"

"እና ምን እንጥበስ?"

"ምንም አትጥበሱ። ብቻ ዘፈኑ ሲያበቃ ድግሱ ሲያልቅ፣ ይህንን ጥጥ ለሙሽሪት ስጡልኝ። ለሷም ለባሏም ለአማቾቿም ለልጅ ልጆቿም ትፍተልላቸው" አልኩና፣ ከግብጥ በድንጋይ ልጥ ታስሮ በነፋስ ተጭኖ የመጣውን ጭብጥ ጥጥ ሰጥቻቸው ወጣሁ

ያገሬ ጉረምሳ እየጨፈረ አሁንም "ብራምባር ሰበረልም!" እያለ ይዘፍናል

ዋሽቼ አላውቅም ከተፈጠርኩ፣ አሁድ ተወልጄ ሰኞ በግሬ ሄድኩ

"ከዚያስ?" አሉ አጋፋሪ

ከዚያማ አዛውንቱን ተሰናብቼ ወጣሁ። አሁንም ካገሬ መውጣት አለብኝ ብዬ ስሄድ፣ ልክ ካስራ አንድ አመት በፊት ነፋስን አገኘሁበት ቦታ፣ ከዚያ በፊት ደግሞ አስራ አንድ አመት አስቀድሞ እረኛችን ላሚቱ ጠፋች ያለኝ ቦታ ስደርስ፣ ሞትን ፊት ለፊት አገኘሁት

ሳየው ሞት ግራ የገባው ወይም የጨነቀው መሰለኝ። ምክንያቱን ብጠይቀው ነገረኝ።

"ምን ነበር ምክንያቱ?" አሉት አጋፋሪ እየተጣደፉ

ለካ እሱ አጋፋሪ እንደሻው የተባሉ ሰውዬ ወደ ሰማይ ቤት ለመውሰድ ከላይ ታዞ ኖሮ --

"እህ?" አሉ እሳቸው፣ ዝም ብሎ መስማቱ ስላልተቻላቸው

ሰውዬው ለገዛ ምክንያታቸው ሞትን እምቢ ብለውት ኖሮ--

"እህ?"

በእምቢተኝነታቸው በልዩ ልዩ ምክንያት... ለኔ ባልተነገረኝና በማላውቀው ምክንያት... አሸንፈውት ኖሮ--

"በጆ ቀጥል" አሉ አጋፋሪነታቸው፣ ኮራ እንደማለት ብለው

ፈርቶና አፍሮ ባዶ እጁን ወደ ሰማይ ቤት ሊመለስ ኖሯል

"እህ" አሉ አጋፋሪ

እንግዲህ ምን ልበልም? የጨነቀውና የጨነቀው ሲገናኙ፣ የቸገረውም እርጉዝ ያገባል፣ የቸገራትም ስልብ ታገባለች

"እሺ፣ ከዚያስ?" አሉ አጋፋሪ

ከዚያማ እኔም በነፋስ ታዝዬ አለምን አይቻለሁ፣ ሰማይ ነው የቀረኝ፣ ሞትም አጋፋሪን አምጣ ተብሎ ታዟልና ሰማይ ቤት አጋፋሪን ይዞ መግባት አለበት

"በጆ" አሉ አጋፋሪ፣ ድንጋጤው እያገረሸባቸው

ተስማማን! ሞትም ሰማይ ቤት ሊያደርሰኝ፣ እኔም የእምቢተኛውን የአጋፋሪን መልክና ስም ይዤ ልገባ

ምን ቸገረኝ? ምናልባት በኋላ ቢታወቅብኝ እንኳ፣ ገና ባለመወለዴ፣ የክርስትና ስምም የለኝ፣ ከተወለዱ ሰዎች ቁጥርም አልገባሁ

"እሺ" አሉ በትዝብት እያዩት አጋፋሪ

"በኋላ ግን ወደ ምድር ትመልሰኛለህ" አልኩት - ሞትን።

"ወደ ላይ ስመለስ የታዘዝኩትን ሰው ይዤ መሄድ አለብኝ እንጂ፣ ወደታች ስመጣማ ስረገላዬ ሁልጊዜም ባዶውን ነው:: ስለዚህ በፈለግከው ጊዜ ወደ ምድር እመልስሀለሁ" አለኝ

በዚህ ተስማምተን ወደ ሰማይ ቤት ሄድኩ:: ባጋፋሪ እንደሻው ስምና መልክ ሰማይ ቤትን አስራ አንድ አመት ሙሉ እየዞርኩ ካየሁና ካጠናሁ በኋላ፣ ሞት አንዱን ለመውሰድ ባዶ ሰረገላውን እየነዳ ሲወርድ አንድ ድብቅ ቦታ ጠበቅኩትና ውስደኝ አልኩት:: ወደ ምድር ማምጣት ብቻ ሳይሆን እተገናኘንበት መንደሬ ዳር አደረሰኝና ወደ ጉዳዩ ሄደ

እንግዲህ አስራ አንድ አመት አለፈ ካገሬ ከወጣሁ:: በጠቅላላው ሰላሳ ሶስት አመት መሆኑ ነው

"ብፎ" አሉ አጋፋሪ፣ ብዙ ምኞት በልባቸው እየተገላበጠ፣ ብዙ ብልሀት በሀሳባቸው እየተሰለፈ

ሰማይ ቤትንም ጉብኘቼና አጥንቼ ከሰላሳ ሶስት አመት በኋላ ወደ አገሬ ወደ መንደሬ ስመለስ፣ አሁንም ዳሱ ያው ነው፣ "ብራምባር ሰበረልዎም" ይዘፈናል፣ ቀኑም ማክሰኞ ነው፣ ሰርጉም የናቴና ያባቴ ነው

"እዬ!" አሉ አጋፋሪነታቸው፣ ለተገላቢጦሹ ሰውዬ ከልባቸው አዝነው:: (ይህም ከፅድቅ ተቆጠረላቸው፣ መልአኩም ይህን በሰማያዊ መዝገብ አሰፈረላቸው:: እሳቸው ግን ፅድቁ ወደ አለማዊ ኑሮ ቢመነዘርላቸው ነበር ፅኑ ፈቃዳቸው)

"ከዚያስ?" አሉት ተገላቢጦሹን "ሰውዬ" አጋፋሪነታቸው

ከዚያማ የመጣው ይምጣ ብዬ ወደ ዳሱ ገባሁ:: አዛውንቱ መሰቦቹ በነበሩባቸው ዙሪያዎች ጠላ በዋንጫ ፉት እያሉ ያወጋሉ:: አደግድጌ ወደ አዛውንቱ ሄጄ እጅ ብነሳ

"ከየት መጣህ?" አሉኝ

"ከሰማይ ቤት" አልኳቸው

"እንደምን እዚያ ደረስክ?"

"በሞት ሰረገላ"

"ከሆነስ ሆነና፣ እግዜርን አይተኸዋል?"

"እምና!"

"ቀይ ነው ጥቁር?"

"ተከናንቦ ነበር"

"ረጅም ነው አጭር?"

"ተቀምጦ ነበር"

"አሁን ምን ትፈልጋለህ?" አሉኝ

"የሰርገኞቹ ልጅ እንዲወለድ" አልኳቸው

"እሱማ ጊዜውን ጠብቆ ነው" አሉኝ

"እና ጊዜው መቼ ነው?" አልኳቸው

"እንጃ!"

"በሉ ደህና ሁኑ" አልኳቸውና ወጣሁ

በመጀመሪያ እረኛውን፣ በኋላ ነፋስን፣ ከዚያም ሞትን ካገኘሁበት ስፍራ ስደርስ፣ ተረትን አገኘሁት:: ወደዚህ እመጣኝ፣ አውርዳኝ ሄደ:: እርስዎ በበቅሎ በእጀብ መጡና፣ እንዴት ዋላችሁ? አሉኝ:: ይኸው እንግዲህ፣ እውነቴም ተረቴም አበቃ" ሲል ደመደመ ተገላቢጦሹ ሰውዬ

አጋፋሪ ጥቂት ሲያስቡ ከቆዩ በኋላ እንዲህ አሉት

"ስማኝ ወዳጄ፣ የሞት መድሀኒት ወይም ድግምት ፍለጋ ወደ አባ ሸንኩርት መሄዴ ነው:: አንተም አብረኸኝ ብትመጣ ጥሩ መሰለኝ:: አባ ሸንኩርት ከቻሉና ከፈቀዱ፣ ለኔም የሞት መድሀኒት፣ ላንተም የልደት መድሀኒት ይሰጡናል:: እስዚያም እሳቸው ጋ ከደረስን በኋላ ሌላ ብልሀት እንፈልጋለን"

"አሁን ገና ተናገሩ!"

"እሱሱ በፊትም ስናገር ነበር" አሉት ሳቅ እያሉ "ብቻ ተነስ፣ ነጠላህን አገልድምና ገብሬ ሌላ ልብስ ይፈልግልሀል፣ ወደ መግደላይት ጓሮ እንሂድ"

ተነሳ አቶ ተገላቢጦሽ፣ መጋረጃ ሆኖት የነበረውን ነጠላ አሸረጠ፣ አጋፋሪም ተነሱ አብረውት:: ወደ አባ ሸንኩርት ሊሄዱ ሆነ

(መልአኩ ይህን ሲመዘግብ አጋፋሪ ከፅድቅ ተቆጠረላቸው:: እሳቸው ግን የሚመርጡት ሺ ፅድቅ ወደ አንድ አመት ወይም ወደ አንድ ሰአት አለማዊ ደስታ ቢመነዘርላቸው ነበር)

"ወዳጄ፣ አገርህ መንደርህ የት ነው?" አሉት "ሰውዬውን"

"ልክ በትግራይና በጐንደር ድንበር ላይ ነው:: ስለዚህ ባንድ ጐኔ ትግሬ ባንድ ጐኔ ጐንደሬ ነኝ:: በትግራይ ዘፈን በጐንደር ተረት ነኝ"

"እህ..." አሉ አጋፋሪ፣ ራሳቸውን በአዎንታ እየነቀነቁ "መቼና የት እንደሆነ ተረስቶኝ እንጂ፣ በጉዞዬ ላይ ከተረት ጎንህ ጋር ካንድም ሁለቴ ተገናኝተናል"

"እርስዎ ተረት ነዎታ!"

"ወይድ! ባለጌ!" አሉት እየገረመሙት "ተረት ነኝ ብለህ መዋሸትህ አነሰና፣ እኔንም ተረት ልታረገኝ?"

"እኔማ ተረት ነኝ አልኩዎት'ኮ፣ ጌታዬ"

"ኧረ ይጉትጉትህ እዚያው! ደሞ ጌታዬ ይለኛል?! ተረት ከሆንክ፣ እኔ ለብርቱ ጉዳይ ስሄድ በባዶ ተረት ጊዜዬን 'ምታጠፋብኝ ለምን?"

"አይቆጡኝና፣ እርስዎም እንደኔ ተረት ነዎት። ልዩነታችን፣ እኔ የቆየሁ ቅርስ ስሆን፣ እርስዎ አዲስ አዝመራ ነዎት። እንጂ ተረት ነዎት"

"ኧረ ተረት ሁነህ ቅር እዚያው!"

"እኔማ ተረት ሆኜ ቀርቻለሁ!"

"ብል ዝም በል አትልከፈኝ። እኔ ሰው ነኝ'ንጂ ተረት 'ማይደለሁ"

"እንግዲያው ተረት ስፈር ምን ይሰራሉ?"

"እኔማ የሞት መድሀኒት ፍለጋ ስጓዝ ሳጠያይቅ ወደዚህ ስላመላከቱኝ መጥቼ ነው። ይልቅ በንትርክ የሰው ጊዜ አታጥፋ። ትሄድ እንደሆነ ተነስ እንሂድ አባ ሽንኩርት ዘንድ"

አጋፋሪ እንደሻው በቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው ሲሄዱ፣ ከጉናቸው የሚራመደውን ተገላቢጦሽ ሰውዬ እየተመለከቱ በሀሳባቸው እንዲህ አሉ "እውነት ተረት እሆን እንዴ? ከሆንኩማ ጉድ ተሰርቻለኊ!!... እንግድያው ሁሉም ተረት ነዋ!... ብቻ

ደሞ'ኮ፣ ተረት ከሆንኩ ከሞት ማምለጥ እችላለሁ ማለት ነው። ለተረት ምን ተስኖት!?... ከሞት ላምልጥ እንጂ ታድያ፣ እንኳን ተረት ለምን ቀልድ አልሆንም? እንደሻው ግድ አለው?... ዘራፍ! እንደሻው አባ መከት! ሽሽት ጋሻው ከሞት ይመከት!..."

***

አጋፋሪ እንደሻው ከአቶ ተገላቢጦሽ ጋር አባ ሸንኩርትን ፍለጋ ወደ መግደላይት ቤተስክያን ሲሄዱ አያ ድቡልቡሌን መንገድ ላይ አገኙት። ተሸከማቸው ከምትሰግረው ጠጂቱ ጋር በሀሳባቸው እያወሩ ሲሄዱ፣ አዩት ከፊት ለፊታቸው፣ ካንገቱ በላይ ሰው፣ ካንገቱ በታች ጋን! ራሱ ላይ ሽክና ደፍቷል እንደ መነኩሴ ቆብ

እያማተቡ "ስአሊለነ ቅድስት!" እያሉ፣ ልጓም ስበው ከጠጂቱ ወረዱ። (ሀሳብ ጨረፍ አርጓቸው አለፈ፣ እንዲህ እያለ - - እሳቸው ሲያስኛቸው በሁለት እግራቸው፣ ሲፈልጋቸው በጠጂቱ አራት እግር እየተዘዋወሩ ምድረ ሀበሻን ደጋግመው ሲያዳርሱ፣ ምድሪቱ ያው ሆናም ሺ ጊዜ ውበቷን እየለዋወጠች ስታስደስታቸው፣ በበኩሉ ይኸ ሰው-ጋን ነገር እንዴት ይሆነው ይሆን? አቤት አምላኬ፣ ምንኛ ትጨክናለህ! ወይስ ብልሀት ያልከው ይሆን?)

"ጤና ይስጥልኝ" አሉት እጅ እየነሱት ሰው-ጋኑን፣ ባለሽክና ቆቡን

"እግዚአብሔር ይመስገን" ሲል ድንግጥ አሉ፤ ፈሩት ድምፁን "እጅ እንዳልነሳ እንደሚያዩኝ ነኝ።"

"እረ ግድ የለም" አሉት በደህና ድምፅ፣ ውስጡን ግን በፍርሀት ብርድ ብርድ እያላቸው

"እርስዎማ ግድ የለዎትም!" አለ፡፡ የተናደደ ይመስላል፡፡ "ለመሆኑ ማን እንደሆንኩ አውቀውኛል?"

ከድምፁ ወጥቶ ይህ ነው የማይባል ፍርሀት ነብሳቸውን ወረራት፡፡ መናገር ተሳናቸው፡፡

"'መፍርሀ ወመደንግፅ ወመርአድ ድምፁ ፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ" አለ ሰው-ጋንየው "ይበሉ'ንጂ፣ ማን እንደሆንኩ አውቀውኛል?"

አጋፋሪ ቢፈሩም ቢርዱም፣ እንደ ምንም ወኔያቸውን እየቀሰቀሱ "ተገናኝተን እናውው፡፡ እንዴት ልወቅህ?" አሉት

"'ወኢአመሩም አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ፣ እያ ድቡልቡሌ ነኝኮ"

ድንገት ፍርሀታቸው እርግፍ አርጎ ተዋቸው፡፡ ሰው-ጋን ጉድየውን በስም ስላወቁት ይሆን?

"ተው'ንጂ" አሉት "እያ ድቡልቡሌ'ኮ ድሮ ጥንት ልጆች ሆነን የምንሰማው ተረት ነው"

"እኮ! እሱ ራሱ ነኝ እኔ፡፡ እኔ ራሴ ነው እሱ ማለቴ፡፡ አዩት፣ ስጋና ገል አርጎ ፈጥሮ እንዲህ ሲጫወትብኝ? በሱ ቤት እንግዲህ ቅኔ መፍጠሩ ነው - ሰምና ወርቅ ሳይሆን፣ ስጋና ገል፡፡ 'ወአድበልበልኩም ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ"

"ተው'ንጂ፡፡ ባይኔ እያየሁህ በጆሮየ እየሰማሁህ፣ ተረት ነኝ ትለኛለህ?"

"እርስዎ ራስዎ ምን ሆኑና?"

"ምን ማለትህ ነው? ገልጠህ ተናገር"

"ይህ ያለንበት መንደር ምን ይባላል?"

"ተረት ሰፈር" ·

"እኮ!"

"እኮ ምን?"

"የተረት ሰፈር ሰዎች'ኮ ተረቶች ነን። 'ወተረኩም አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ"

"አንተ ተረትም ጋንም ትሆናለህ እንጂ፣ እኔ ግን እንደሻው ነኝ። እንደሻው በልሁ፣ በልሁ ድልነሳው። በል ምን ትሆን?"

"እኔማ ምን እሆናለሁ? እርስዎ'ንጂ። ተረት ባይሆኑ፣ ተረት ሰፈር ውስጥ ካያ ድቡልቡሌ ጋር እንዴት ብለህ ታወራ ነበረ? ይቅርታ፣ ግማሽ ገልነቴ አንቱታ አያውቅም። 'ወኢየአምር አንቱታ ፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ።"

"ለመሆኑ፣ ተረት ከሆንክ ምን አይነቱ ተረት ነህ?"

"ሁለት አይነቱ። 'ወክሌኤቱ ፍጥረቱ ልቡ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ።"

የጋን ጆሮ እሚሆንበት ቦታ የሰው እጅ አለው እያ ድቡልቡሌ። በጣቶቹ እየቆጠረ "አንደኛው፣ ውጭኛው ተረት ነው - ያ እርስዎ ልጅ ሆነው የሰሙት። ሁለተኛው ውስጠኛው ተረት ነኝ - ያ እኔ የማውቀኝ"

"እኔ ሁለቱንም አላውቃቸው። ንገረኝ እስቲ"

"እሱማ እውነቴን ተረቴን ለመስማት እዚች ለምለም ሳር ላይ ቁጭ ብትልስ" አለ በእጁ እያመለከተ "ወነበረ በባቢሎን ፍቁር

ወልድየ እንዲል መፅሀፉ:: ወድያውም ሽቅብና ቁልቁል ከመነጋገር--"

"መልካም:: መጀመሪያ ይህን ሰው ላስተዋውቅህ:: አቶ ተገላቢጦሽ ይባላል::"

ከተዋወቁ በኋላ ቁጭ ተባለና፣ አያ ድቡልቡሌ ውጭኛውን ተረት እንዲህ ሲል በማታ እሳት ዳር የተረት ዜማ ጀመረላቸው:-

እንጉዳይ እምትባል ውቢት ነበረች፣ እግዜር እጁን ታጥቦ የፈጠራት:: ግና ሳይጣላ አይደግስምና፣ ይህ ውበቷ ሌሎቹ አብረዋት የሚውሉት ሴት ልጆች ልብ ውስጥ የጠቆረ የከረረ ቅናት አሳደረ:: አንድ ቀን እንጉዳይ ውቢቱ በሌለችበት፣ ሌሎቹ ተማከሩና ጨሌዎቻቸውን ካንገታቸው አውልቀው ደበቁ:: በአጃቸው እፍኝ ጠጠር ጨብጠው ሀይቁ ዳር ቆዩዋት:: እሷ ስትመጣ "ልጆችዬ ዶቃዎቻችንን ውሀው ውስጥ እንወርውር!" ተባባሉ "አንድ - ሁለት - ሶስት!" ብለው ፈጥነው ጠጠሮቹን ሀይቁ ውስጥ ወረወሯቸው::

እና "እንጉዳይ፣ አንቺስ ጨሌዎችሽን አውልቀሽ ውሀው ውስጥ አትጥይም?" አሉዋት "እኛ እንኳን ሁላችን ጥለን? እንግዲያው ሂጂ ለብቻሽ፣ ከኛ ጋር አትጫወቺም በቃ:: እ? እኛ ደሞ ብትፈልጊ 'አይጥ የት ከርማ መጣች?' እንጫወታለን:: ከኛ ጋር አትጫወቺም? እንደኛ ዶቃዎችሽን ውሀው ውስጥ ጣይና!" ብለው ጨሌዎችዋን አስወልቀው ባህሩ ውስጥ አስወረወሩዋት፣ ራቁት አንገቷን ቀረች

ይኸኔ ሌሎች እየተሳሳቁ ዶቃዎቻቸውን ከየደበቁበት አውጥተው እፊቷ እያወዛወዙ "እንቅልልጭ! እኛ ዶቃችን ይኸው!

እኛ ዶቃችን ይኸው!" እያሉ ጨሌዎቻቸውን አንገታቸው ላይ አሰሩ።

አለቀሰች እንጉዳይ ውቢቱ፣ ተንሰቀሰቀች። ሳትደርስባቸው ሳትበድላቸው እነሱ ይህን ያህል እንደጠሉዋት ድንገት በማየቷ እጅጉን ተከፋች። አንገቷን ደፍታ ስታለቅስ እየተሳሳቁ ትተዋት ሄዱ

ስታለቅስ ሰምቷት አያ ድቡልቡሌ መጣና "ምን ሆነሽ ታለቅሻለሽ፣ እንጉዳይ ውቢት?" አላት። ነገረችው።

"ዶቃዎችሽን አውጥቼ ብሰጥሽ ሚስት ትሆኝኛለሽ ወይ?" አላት

ያ የሀዘን ለቅሶዋ ወደ እልህ ተለወጠ። እሺ አለችው።

አያ ድቡልቡሌ ባሀሩን ጭው አድርጎ ጠጣው፣ ጉድጓዱ ባዶውን ቀረ። እዚያ ታዩ ዶቃዎቿ የ'ንጉዳይ ውቢቱ። አያ ድቡልቡሌ አንስቶ ዶቃዎቹን አንገቷ ላይ አሰረላት።

ፈገግ አለች፣ እንደ አበባ ፈካች

አያ ድቡልቡሌ ልብ ውስጥ ደስታው እንደ ፀሀይ በራ

ዳሩ ምን ይሆናል፣ አያ ድቡልቡሌ እንጉዳይ ውቢቱ ቤቶች ዘንድ ልጃችሁን ስጡኝ ብሎ ሽማግሌዎች ቢልክ "እንኳን ልጃችንን ልንድርልህ ቀርቶ፣ እዚች ድርሽ ብትል በነብስህ አወቅበት" አሉና ቤታቸውን በሰባት ዙር አጥር ከበቡት

መቸስ "ፍቅር ውእቱ" እንዲል መፅሀፉ፣ አያ ድቡልቡሌ እንጉዳይ ውቢትን ፍለጋ እየተድቦለበለ መጣ

መጣና ውጭኛው ሰባተኛው አጥር ጋ ሆኖ ተጣራ

"እንጉዳይ ውቢቱ፣ እንጉዳይ ውቢቱ--

መጣሁልሽ አንቱ!" አላት:: (ለግጥሙ ሲባል እና ግማሽ አማርኛው ስለሚማታበት "አንቱ" አለ፣ እንጂ "መጣሁልሽ እኔ" ማለቱ ነበር)

እሷም ወጥተው ይቀበሉታል መስሏት

"አባዬ ተነሳ፣ ነጠላህን አንሳ" ስትል፣ አባቷ ጋሻ ጦራቸውን አንስተው ወጡ

እዚያ ላይ አያ ድቡልቡሌ የተረት ዜማውን ተወውና በቁጣ ለነአጋፋሪ ተናገረ "ሊወጉኝ መጡ አባትየው:: አይ ግፍ! ባፈቀርኩ በጦር ሊወጉኝ?! ተናደድኩ"

አያ ድቡልቡሌ ተናደደ፣ ድቡልቡል አይኑ ተንቦለቦለ!!

ጭስስ አለ፣ ካፍንጫው ጪሱ ቡልቅ ቡልቅ አለ!!

መጨሱም መናደዱም እስኪያልፍ ትንሽ በዝምታ ተቆየ

"ምነው አልጨስ፣ ምነው አልናደድ!?" ሲል ቀጠለ አያ ድቡልቡሌ፣ በእሳት ዳር ተረት ዜማ "ምነው አልጨስ፣ ምነው አልናደድ!? ምነው አልጨስ፣ ምነው አልናደድ?! ምነው አል---"

"በል በቃህ ወዳጄ፣ ጨስክ ተናደድክ" ብለውት፣ ዝም ሊሉ ሊስሙት እየፈለጉ፣ እሳቸውም በተረት ዜማ ቀጠሉ "ምን አጨሰህ ምን አና-ደደህ? ምን ያጨሳል ምን ያናድዳል?! ለምን መጨስ ለምንስ መ-ናደድ?! ምነው መጨስህ መ---"

"አዩት አይደል የመደጋገምን ነገር?" ብሎ ሲያቋርጣቸው እፎይ ብለው ተነፈሱ "የኔም የርስዎም የተረታችን እንዱ ምልክት ነው::"

"ወዲያ ባክህ! አትድበልበልብን እዚህ!"

"እሺ ይተዉት በቃ። ተረቴን ልቀጥልልዎት?"

"እሱ'ንኳ ይሻላል"

"አባትየው ባልወለደ አንጀታቸው ጨክነው ጦሩን ወረወሩብኝ። ጋኔ ውስጥ ገብቶ ቀረ፣ ጠፋ። ጋኔ እንኳን ሊሰበር ንቃትም አልታየበት። እኔን ፊቴን ያያሉ ደሞ፣ ምንም አልሆንኩም! ደንግጠው ጋሻቸውን ጣሉ። 'ወፈርሁም አህዛብ ለፍቁር ወልድየ' እንዲል መፅሀፉ"

"የቱ መፅሀፍ ነው ግን?"

"ያ ያልተፃፈው"

"ብዙ ነገር ይላል እሱ መፅሀፍ"

"አስተዋይ ነዎት"

"እሺ፣ በል ቀጥልልኝ"

"ስድስቱንም አጥር እያፈራረስኩ ደረስኩ። ሰባተኛውን ውስጠኛውን አጥር አፍርሼ ስገባ፣ እንጉዳይ ውቢቱ ቆማ ትንቀጠቀጣለች።

"እዩኝ እስቲ ፊቴን" አልኳት። ፈርታ አቀርቅራ ቀረች። ባገጭዋ ይዤ ጠምዝዤ አይን ለአይን እንድንተያይ አስገደድኳት። እንደ መፍዘዝ አለች። ተያየን። በፍቅር አይን ያየችኝ መሰለኝ። ድፈር ድፈር አለኝ

"ካንገቴ በታች እዩኝ" አልኩና በፍቅር እጅ፣ በተስፋ እጅ፣ በፍርሀት እጅ ራሷን ከኋላ ይዤ አይኗን አሽቀለቀልኩት

"አይ!!" ብላ ጮኸችና አይኗን በጂ ሸፍና እየተርበተበተች ተንበርክካ ተጣጠፈች፡፡ መሬቱቱን የሙጥኝ አለች፡፡

ለሷም አዝኜላት፣ በእድሌም እያዘንኩ፣ እዚያ ትቻት ወጣሁ - ኮበለልኩ፡፡ ሰላሳ ሶስት አመት ሙሉ ስንከባለል፣ ስኮበልል ይኸው እዚህ ደረስኩ፡፡ ከመንደር ቂሉ ቀጥሎ ያጋጠሙኝ እስዎ ነዎት"

("ዳኛቸው ጓዴ እንደሚለኝ፣ እኔ ደሞ የመንደር እብድ መሆኔ ይሆን'ዴ?" አለች ሀሳባቸው ያጋፋሪ)

"እዩኝ'ስቲ በፈጠራችሁ ጌታ" አለ አያ ድቡልቡሌ "መልኬ ለሴት ልጅ ያንሳታል?"

አዩት፡፡ ሰውየው መልኩ እንከን አይወጣለትም

"እኮ ይናገሩ"

"ጓንገት በላይ ሲያዩህ እግዜሩ እጁን ታጥቦ ሲሰራህ የዋለ ነህ"

"እንግዲያው ለምን አልፈለገችኝም?" ጥልቅ ሀዘንና ቁጭት ተሰማቸው እዚያ ድምፅ ውስጥ "ለምን? ለምን?" አለ

አጋፋሪ በጣም አሳዘናቸውና "ስማኝ ወዳጀ" አሉት "ይኸ አቶ ተገላቢጦሽ የቸገረው ሰው ነው፡፡ መወለድን ፍለጋ ሲንከራተት ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነው"

"ወይ አጋጣሚ! እኔ ደሞ በ'ንጉዳይ ውቢቱ ፍቅር ስንከራተት ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነኝ"

"ሶስተኛ አጋጣሚ ይኸውልህ፡፡ እኔ ደሞ የሞት መድሀኒት ፍለጋ ስዞር ይኸው ሰላሳ ሶስት አመት ሆነኝ"

"አጋጣሚው አልበዛም?" አለ አያ ድቡልቡሌ

"ይብዛ ግድ የለህም:: አባ ሽንኩርትን ታውቃቸዋለህ?"

"ማናቸው?"

"መግደላይት ጓሮ መቃብር ቤት የሚኖሩ የበቁ ባህታዊ ናቸው:: ከመብቃቱም አልፊው፣ ከዝጌሩ ጋር ቡና ይጠጣሉ ይባላል:: እኔና አቶ ተገላቢጦሽ እሳቸው ዘንድ መሄዳችን ነው:: እኔ ምናልባት የሞት መድሀኒት ቢያገኙልኝ ብዬ በተስፋ፣ እሱ መወለድ ቢያስችሉት ምናልባት ብሎ በተስፋ:: አንተ ደሞ አብረኸን እንሂድና ሙሉ ሰው ያድርጉኝ ብለህ ለምናቸው::"

"እሺ ይሉኛል?"

"በተስፋ:: ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም" አሉት

"እንዲሁም አያ ድቡልቡሌ!" አለ አያ ድቡልቡሌ

"እንዲያ ነው እንጂ! በሉ እንሂዳ:: ሁለተኛውን ተረትህን እየሄድን ትነግረናለህ"

"እሱስ ጥሩ ነበር:: እኔ ግን ብቻየን ስሆን ተሽከርክሬ እሄዳለሁ 'ንጂ ከሰው ጋር ለመሄድ አልችልም:: ጋን ገላዬ አይንቀሳቀስም ከሰው ጋር ልሂድ ካልኩ"

አጋፋሪ ትንሽ አሰቡና "ግድ የለም" አሉ "በጠጂቱ እንጭንሀለን"

"እርስዎስ?"

"እኔማ በእግሬ 'ሄዳለሁ" አሉ አጋፋሪ እንደሻው (ይህም በሰማይ ቤት ፅድቅ ሆኖ ተፃፈላቸው:: ወደ ምድራዊ እድሜ የሚመነዘር ካልሆነ ግን፣ እሳቸው ምን ተዳቸው?)

እንዲህ ሆነው አምስቱም ወደ መግደላይት አመሩ፡- አንዱ የሞት መድሀኒት ፍለጋ - አንዱ የልደት መድሀኒት ፍለጋ - አንዱ ፍቅርን ፍለጋ - ሁለቱ ለማገልገል ብቻ


@amharicbooks24 click here
@amharicbooks24 ይሄን ይጫኑ
መጽሐፍት
የተመረጡ አማርኛ ና እንግሊዝኛ
መጽሐፍትን ,ትረካዎችን,ወጎች ያገኛሉ
...



የነፋን ስዕል -በ ማቲያስ ሱሉ

ዋጋው ብር 25.00

ህትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር 0111565352